# ታጠቅ

አለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር
የቲዎሪ መፅሄት

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የተዘጋጀ

## ፋሺዝም ?

የመፅሄት አዘጋጅ ቦርድ፡
P.O.BOX 3198
103 64 STOCKHOLM 3
SWEDEN

ቁጥር፡ 1
ጥር 1969

# ፋሺዝም

ይዘት


መግቢያ .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. 1

I- ስጠቃላይ የካፒታሊዝም እድገትና ቀውስ

1- የካፒታሊስት ሥርዓተ ማህበር መሠረታዊ ቅራኔ .. .. .. .. 3

2- ካፒታሊዝም ያለፋቸው አጠቃላይ ደረጃዎችና የመንግሥት ሚና.. .. 4

3- ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ውስጥ በአርባታ ሃይሎችና በአርባታ ግንኙነቶች መሃል ያለው ቅራኔ ትርጉም.. .. .. .. .. .. 7

II- የፋሺዝም ቅድመ ሁኔታዎች፣ የመደብ ይዘቱና ህዝባዊ መሠረቱ .. .. .. ..10

1- በመደቦች ውስጥ የተካሄደ ለውጥና አጠቃላይ እድገት .. .. ..11

2- የከበርቴ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት .. .. .. .. .. .. ..14

3- የካፒታሊስት ሥርዓት ከፍተኛ የኢኮኖሚ ቀውስ ውስጥ ሲዋጥ የመደቦች አሰላለፍና የሥርዓቱ "ዲሞክራሲያዊ አሠራር" ከጥቅም ውጭ መሆን. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. ..16

4- የፋሺዝም የመደብ ይዘትና ህዝባዊ መሠረት .. .. .. .. ..19

ማጠቃለያ . .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. ..27

III- የፋሺዝም በጀርመን ሃገር ድል መምታት ታሪካዊ ሥር መሠረትና ምንጩ

መግቢያ .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. ..28

የጀርመን ፋሺዝም ታሪካዊ ቅድመ ሁኔታዎች .. .. .. .. .. ..28

1- በጀርመን የዘውድ አገዛዝ ታሪካዊ ወዘተ ቀርስ .. .. .. ..29

ሀ/ በፊሳዊ ቁራጭ የዘውድ አገዛዝ ጊዜ የነበረው የሃይል አሰላለፍ.. .. .. .. .. .. .. .. .. .. ..29

ለ/ የመንግሥት መዋቅር /ስቴት ማሺነሪ/ ሚና .. .. .. ..32

ሐ/ የጀርመን ግዛት አመሠራረት ርዕዮተ ዓለማዊ ውጤት. .. ..32

2- ፀረ አብዮት በ"ቫይማር" ሪፐብሊክ ውስጥ.. .. .. .. ..33

ሀ/ የፀረ አብዮት ሃይል መጠናከርና አንደገና መስፋፋት .. ..33

ለ/ የ"ህጋዊ" ተቃውሞ ጊዜ .. .. .. .. .. .. ..38

3- የተከተለው ጠቅላላ ቀውስ .. .. .. .. .. .. .. ..38

ተጨማሪ


* ቦናፓርቲዝም ምንድን ነው? .. .. .. .. .. .. .. .. .. . 40

* ስለ ጊዜያዊ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሁኔታና ፋሺዝም
  የውይይት ነጥቦች:: /ወደፊት በሚዘጋጅ ጽሑፍ
  አጠቃላይ ሃሳቦች በመመሥረት/ . .. .. .. .. .. .. .. .. . 54


——— xxx ———

ማሳሰቢያ

ስለ ፋሺዝም ለማቅረብ የታቀደው ጥናት በሁለት ትላልቅ ክፍሎች የተከፈለ ነው::ይህ በዚህ ጽሑፍ የሚቀርበው የመጀመሪያው ክፍል ስለ ፋሺዝም በአጠቃላይ ከካፒታሊዝምና ኢምፔሪያሊዝም ዕድገት ጋር በማያያዝ — ስለ ክላሲካል ፋሺዝም ምንነትና እንዲሁም ስለ "ፋሺስታዊ" አገዛዝ ምንነት — የከበርቴ ዲሞክራቲክ አብዮት ባልተደረገባቸው ሃገሮች ውስጥ::ከዚያም ከኢትዮጵያ ሁኔታ ጋር በማያያዝ ነው:: ክፍል ሁለት በጊዜ ምክንያት አሁን ሊቀርብ አልቻለም:: ነገር ግን እስኪቀርብ ድረስ ለጊዜው በዚህ ጥናት መጨረሻ ላይ ለውይይት የሚያገለግሉ አንዳንድ ነጥቦች ቀርበዋል::

——— xxx ———

ማረሚያ

በትግላችን ዜና ቁጥር 1 — መስከረም 1969 እትም ላይ ለ16ኛው የኢ/ሊ/ተ/ማህበር ጠቅላላ ጉባዔ የድጋፍ መግለጫ ከሰጡ ድርጅቶች ውስጥ በአውሮፓ የአርሞ ተማሪዎች የጥናት ክበብ ሳይጠቀስ ስለተረሳ አንባቢያን አስፈላጊውን እርማት እንዲያደርጉ እናሳስባለን::



መግቢያ :

ስለ ፋሺዝም ምንነት የከበርቴ ሶሽዮሎጂስቶች / sociologists / ሲጽፉ በሂትለር ወይንም በአንድ የፋሺስታዊ እንቅስቃሴ መሪ ጠባይ፣ አስተዳደግ፣ የሃይል ጥማት ወዘተ ላይ ትንተናቸውን ይመሠርታሉ:: ጥረታቸው ፋሺዝም ከራሱ ከካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ ካለው ቅራኔ የመነጨ መሆኑን ለማሳት ነው:: ወይንም ባጠቃላይ የጦር መሣሪያ ይዞ በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ ያሉትን መደቦችንና ክፍሎች አንበርክኮ የሚገዛ በማለት ፍሬ ነገሩን በዚህም ለመሸፈን ይሞክራሉ:: ከዚህ ጥቂት ራቅ ያሉት ደግሞ ለፀረ ኮምኒስት መርዛቸው መነሻ "ፋሺዝም ማለት የፖርላማ ዲሞክራሲ የሌለበት /"ቶታሊተርያን ስቴት"/ ያንድ ፓርቲ አገዛዝ የሰፈነበት ሥርዓት ነው በሚል "ፍልስፍና" ለማለፍ ይሞክራሉ::

ብዙ የንዑስ ከበርቴ ምሁራን፣ ሪፎርሚስቶችና አድርባይ ሶሽያል ዲሞክራቶች፣ ፋሺዝምን ካፒታሊዝም ውስጥ ካለው ቅራኔ ጋር በመጠኑ በማያያዝ ትንተና አድርገው የንዑስ ከበርቴው መደብ ጥቅም የሚጠበቅበት አገዛዝ ነው በማለት ይደመድማሉ:: ወይንም ጠቅላላውን "ዲሞክራሲ የተነፈገበት" የማንም ጥቅም የማይጠበቅበት፣ ከመደቦች በላይ የተንጠለጠለ፣ የገዥ መደብ ቅራኔ ለማስታረቅ የፖለቲካ ሃይል የጨበጠ የህብረተሰብ ክፍል ነው ይላሉ::

ስለ ፋሺዝም ብዙ ጽሑፎች ተደርሰዋል:: ከከበርቴው ወገኖች ብቻ ሳይሆን፣ በአብዮታውያንም ብዙ ትንተናዎች ቀርበዋል:: በአብዮታውያን ዘንድ በፋሺዝም ጥያቄ በመሠረታዊ ነገሮች ላይ፣ ለምሳሌ ካፒታሊዝም ውስጥ ያለ መሠረታዊ ቅራኔ ውጤት ለመሆኑ፣ ፋሺዝም የትልቁ ከበርቴ አገዛዝ ለመሆኑ ወዘተ... ልዩነት ባይታይም፣ አመጣጡን፣ ዕድገቱን፣ ደጋፊዎቹን ወዘተ...በሚመለከት የተለያዩ አስተያየቶች ይታያሉ::

ፋሺዝም በካፒታሊስት ዕድገት ውስጥ እንዲያውም ካፒታሊዝም ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ደረጃ በደረሰበት ጊዜ የመጣና የሚመጣ፣ ከኢኮኖሚ፣ የሶሽያልና የፖለቲካ ቀውስ ጋር የተያያዘ መሆኑ ላይ ያልተስማሙ አብዮታውያን አልነበሩም:: የሚባለው " ስለ ካፒታሊዝም የማያወራ ስለ ፋሺዝም ባይናገር ይሻለዋል" ከዚህም አልፎ በትክክል " ስለ ኢምፔሪያሊዝም የማያወራ ስለፋሺዝም አገዛዝ አፉን ቢዘጋ ይሻለዋል" ነበር::

ስለ ኢትዮጵያ ጊዜያዊ ሁኔታ በሚነገርበት ወቅት፣ ስለፋሺዝም በኢትዮጵያ የሚቀባጥሩት የነ አበፋወወሰን ወጣት ድርጅቶች ግን ይህችን መሠረታዊ ፍሬ ነገር የሚዘሉት፣ አንደኛ የካፒታሊዝምን ዕድገት በኢትዮጵያ፣ ሁለተኛ የፋሺዝምንና የሞኖፖሊ ካፒታሊዝምን ግንኙነት መያያዝ ጨርሶ በመካድ ነው::

አስፋውወሰንና ወጣት ድርጅቶቻቸው ስለ ፋሺዝም ባሁኑ ጊዜ የሚቀባጥሩት በውነቱ አደጋው ከየትና እንዴት እንደሚመጣ ለመሸፈን በሚያደርጉት ጥረት ነው:: በሰፊው ወደፊት እናያለን::

በኢትዮጵያ አብዮታዊው የየካቲት እንቅስቃሴ ከፈነዳበት ጊዜ አንስቶ በተለይ ደርግ የፖለቲካ ሃይል ከጨበጠበት ጊዜ ጀምሮ፣ ከነአስፋወሰንና ወጣት ድርጅቶቻቸው ዘንድ በኢትዮጵያ ውስጥ ፋሺዝም ስለመምጣት የሆነ ያልሆነው ተቀባጥሯል:: ደርግ ፖርላማ አጠፋ፣ ፋሺዝም ነገሠ፣ ደርግ ዲሞክራሲ ነፈገ፣ ፋሺዝም ተንሠራፋ፣ ህዝብ ተጨፈጨፈ ፋሽስታዊ ሥርዐት ተገነባ፣መሬት ተከፋፈለ ገበሬ ንዑስ ከበርቴ ሆነ፣ የፋሺዝም አደጋ በገጠር መጣ፣ ወዘተ...
እነዚህን የመሳሰሉት ስለፋሺዝም የተነዙት ፍሬ ከርስኪዎች የብዙ ተራማጆችን ጆሮ አደንቁረዋል::አንዳንዶቹንም ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ በትክክል እንዳያዩ ጋርደዋቸዋል::

እንደ እውነቱ ከሆነ ስለዚህ ጥያቄ በአሁኑ ጊዜ በመጻፍ ጊዜ ማጥፋት ባልተገባ ነበር:: ብዙ አንገብጋቢ ጥያቄዎች፣ አብዮቱን ሊያራምዱ የሚችሉ ብዙ አብዮታዊ ተግባሮች እንደዚህ በገፍ በአሉበት ወቅት ለነዚህ ጊዜ መስጠቱ ባላስፈለገ ነበር:: ስለ ፋሺዝም በአንዱ ተራማጅ የተጻፈ ማንኛውም ጽሑፍ ያነበበና ስለ ታሪካዊ ማቴሪያሊዝም ሀ ሁ የቆጠረ ሰው ኢትዮጵያ አሁን ያለችበት ሁኔታና የነሙሶሊኒና ሂትለር ፋሺዝም እንደ ሰማይና ምድር የተራራቁ መሆናቸውን በቀላሉ በተረዳ ነበር::

ሆኖም ይህ ውዥንብር መቼም እንዴ ተነዝቷል:: የዚህ ዓይነት ውዥንብር ልዩ ልዩ ቀለሞች ባላቸው አድሃሪዎች ሲነሰነስ አብዮታውያን ዝም ብለው ሊመለከቱ አይችሉም:: ስለሆነም ስለ ፋሺዝም ምንነት ከየትና እንዴት እንደ ሚመጣ፣ ከዚህ ውዥንብር የሰፊው ሕዝብ ዓይን እንዳይጋረድ ይህችን ጽሑፍ ማቀረብ እንገደዳለን::
የፋሽስታዊ አገዛዝ አደጋ /የነሂትለሩ ዓይነት ባይሆን ለዚህ ታሪካዊ ሶሺያል ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሁኔታ ፍጹም የለምና/ ኢትዮጵያ ውስጥ እንዴት መታየት እንዳለበት በመጨረሻ እናሳያለን:: በመጀመሪያ ግን በአድሃሪዎች የተነሰነሰውን ውዥንብር መልክ ለማስያዝ ስለ ክላሲካል ፋሺዝም ምንነት እንረዳ ዘንድ ከሥር መሠረቱ ሰፋ ያለ ትንተና ማቀረብ ያስፈልጋል እንላለን::

አንዱ ህብረተሰብ ያለበትን ሥርዓተ ማህበር በታሪካዊና ዲያሌክቲካዊ ማቴሪያሊዝም በመመርመር የፋሺዝምን አመጣጥ፣ የየትኛው መደብ ጥቅምን እንደ ሚጠብቅ ወዘተ... ለማየት ስለፋሺዝም በአጠቃላይ ከካፒታሊዝም ዕድገትና ከኢምፔሪያሊዝም ጋር በማያያዝ ከሥረመሠረቱ እናስረዳለን::



## I- አጠቃላይ የካፒታሊዝም ዕድገትና ቀውስ

### 1./ የካፒታሊስት ሥርዐተ ማህበር መሠረታዊ ቅራኔ

በፊውዳል ሥርዓተ ማህበር ውስጥ የነበሩት የዐርባታ መሣሪያዎች በተሻሻሉና በዘመናዊ የዐርባታ መሣሪያዎች ሲተኩ፣ በህብረተሰቡ ውስጥ ያለው ማንኛውም የሰው ተሰው ግንኙነት በካፒታል ሲወሰን፣ ላብ አደሮች ከመሬት ወይንም ከነበራቸው መጠነኛ የዐርባታ መሣሪያ ተላቀው የሥራ ኃይላቸውን ብቻ ይዘው ለካፒታል ባለቤት ለመሸጥ ገበያ መቅረብ ሲጀምሩ፣ የሰው ተሰው ግንኙነት ገበያ መቅረብ ሲጀምር፣ የሰው ተሰው ግንኙነት ገበያ ላይ በሚከሄደው የዕቃ ልውውጥ ሲወሰን፣ በ"ጉልበት ሥራና በጭሌና ሥራ" ያለው የሥራ ክፍፍል ሲፈጸም፣ በገንዘብ ላይ ብቻ የተመሠረተ ግንኙነት ጠቅላላ ህብረተሰቡ ውስጥ ሥር ሲገባ፣ ጥንት ከነበረው ከ"ተፈጥሮዋዊ" የሥራ ክፍፍል ዕድገት አልፎ በኢንዱስትሪ ውስጥ በህብተረተሰቡ ውስጥ ያለው የሥራ ክፍፍል ሙሉ በሙሉ ሲጸድቅ፣ አንዱ ህብረተሰብ በካፒታሊስት የኢኮኖሚ ህጎች መንቀሳቀስ ይጀምራል::በዚህ ህብረተሰብ ውስጥ የተፈጠሩት ሁለት ዋና ዋና መደቦች፣ ወዝ አደሩ፣ የጉልበት ኃይሉን ብቻ ሽጦ የሚኖር ባንዱ በኩል፣ ጠቅላላ የህብረተሰቡ የዐርባታ መሣሪያን በዐጁ ያደረገው የከበርቴው መደብ በሌላ በኩል ናቸው::

የካፒታሊዝም ማደግና ፊውዳሊዝምን መተካት ያስከተለው አንዱ ዋና ነገር በፊውዳሊዝም ታፍነው የነበሩት የዐርባታ ሃይሎች ማደግና ወደኋላ ቀርቶ የነበረው የዐርባታ ግንኙነት መሠባበር ነው:: ሌላው ደግሞ የተከተለው ሰፊ ህብረተሰባዊ የሥራ ክፍፍል ነው:: ከዚህ የሥራ ክፍፍል ጋር የመጣው እራሱ ሥራም ህብረተሰባዊ ጠባይ ማግኘቱ ነው::

ሥራ በካፒታሊዝም ውስጥ ህብረተሰባዊ ጠባይ እንዲኖረው ያደረጉት ዋና ዋና ነገሮች፣ የማምረቻ ኃይሎች ባንዱ ላይ መሰብሰብና መከማቸት፣ ሰፊ የህብረተሰባዊ የሥራ ክፍፍል ዕድገትና የተለያዩ የሥራ መስኮች ላይ በየረድፉ ማተኮር /እስፔሺያላይዜሽን/ ጥንቱ፣ በገበሬና በባለመሬት መሃል የነበረው ግለሰባዊ ተጽዕኖና ግንኙነት በ'ነፃ' የሥራ ጉልበት መተካት፣ በዐርሻ ላይ የተሰማራው የህዝብ ክፍል መቀነስና እንደዚሁም በየኢንዱስትሪና ትላልቅ ፋብሪካዎች ወደ አሉበት የሥራ ጉልበት ለመሸጥ መፍለስ መጠራቀም የወዝ አደሩን ቁጥር መብዛት በካፒታል እንቅስቃሴና ፍላጎት ላይ የተመሠረተ የህዝብ መንቀሳቀስ መፈጠር ናቸው:: በካፒታሊዝም ዕድገት ባሩያና ተያይዞ የመጣው ሰፊ የህብረተሰባዊ የሥራ ክፍፍል ሥራ ሙሉ በሙሉ ህብረተሰባዊ ጠባይ እንዲኖረውና የዐርባታ ኃይሎችን በፍጥነት እንዲያድጉ አድርጓል::

ካፒታሊዝም ውስጥ ይህ ዓይነት ከፍተኛ የሥራ ክፍፍል መኖሩ፣ የሥራ ኃይሉን በቀላሉ ዋጋ ለመሸጥ ወዝ አደሩ ሥራ ወደአለበት የተሳለቀ አንዱስትሪ አካባቢ በነፃ መፍለሱና መገኘቱ ለባለ ካፒታሉ ዋና ዓላማ ማለት በተቻለ መጠን ያለውን ካፒታል በብዛት ለማራባት አመቺ የሆነ ሁኔታ ይፈጥራል:: ወዝ አደሩን በዝብዞ ትርፍን ለማሳደግ ያስቻለዋል:: ከዚያም ዕርባታን በበፊው ያሳድጋል:: ካፒታሊቶችን በዚህ መንገድ የሚያደርጉት ካፒታሊስቶች በሙሉ የተሠራውን ዕቃ ገበያ ላይ ለመሸጥ መቻል አለባቸው:: እያንዳንዱ ከሌሎቹ ካፒታሊስቶች ጋር መወዳደርና ለዕቃው ገዥ ማግኘት አለበት:: ሁሉም በየፊናው ይህን ስለሚያደርግ ምንም ቢሆን ብቻውን የገበያውን ሁኔታ ሊያረጋግጥ ስለማይችል፣ የሚያመርተው ሸቀጥ ገዢ ይኑረው አይኑረው ሁልጊዜ በጥያቄ የሚቆም ነው:: ማለትም የገበ ያውን ተቀባይነትና ችሎታ አስቀድሞ ሊያውቅ ስለማይችል የሚያመርተው ገበያው ሊወስደው ከሚችለው በላይ ወይ በታች ሊሆን ይችላል:: ይህ ሁኔታ ራሱን በከ ንሳምሽንና በምርት መሐል ባለው ቀራኔ ራሱን ይገልጣል:: እንዲሁም በህብረተ ሰቡ ውስጥ በገበያ አናርኪና በግለሰቡ ከበርቴ የተደራጀ ምርት ስለት መካከል ያለውን ቀራኔ ያንፀባርቃል:: ይህ የሚታይበት መልኩ ይሁን እንጂ፣ የነዚህ ሁሉ መሠረታዊ ቀራኔ እራሱ የካፒታሊስት ሥርዓተ ማህበር ውስጥ ያለው፣ በሥራ ወይንም በዕርባታ ኅብረተሰባዊ ጠባይና በግላዊ ምርት ውጤት መሰብሰብ ላይ የተ መሠረተ ነው:: ወዝ አደር በጋራ ይሠራል፣ ትርፍ ያረባል፣ የሥራ ውጤቱን ግን ለጋራ ጥቅሙ አይደርግም:: ከበርቴው የዕርባታ ሃይሎች ባለቤት ስለሆነ የዕርባ ታውን፣ የወዝ አደሩን የጋራ ውጤት ለራሱ ያደርገዋል::

በጋራ ህብረሰባዊ የዕርባታ ጠባይና በግላዊ የዕርባታ ውጤት ባለቤት ነት መካከል ያለው በየጊዜው በሰዱ ሰዱ መልክ የሚታይ የካፒታሊዝም መሠረታዊ ቀራኔ ነው:: በካፒታሊዝም ውስጥ የሚታየው የኢኮኖሚ ቀውስ መሠረት ነው::

2./ <u>ካፒታሊዝም ያለፋቸው አጠቃላይ ደረጃዎችና የመንግሥት ሚና</u>

የካፒታሊዝም የመጀመሪያ ደረጃ /ገና ከፊውዳሊዝም ሙሉ በሙሉ ሳይ ላቀቅ ያደረጋቸውን ዕድገት፣ የሸቀጥ የካፒታሊዝም ዕርባታ ሙሉ በሙሉ ስርጉ ሳይገባ ያለፋቸውን ወደጉን ከተውን/ የውድድር ካፒታሊዝም የሚባለው ነው:: በከበርቴው የኢኮኖሚ መሠረትና /በዝበ/ በፊውዳል ሱፐር ስትራክቸር መሃል ያለው ቀራኔ ፈንድቶ የከበርቴው አብዮት ከተካሄደ በኋላና በከበርቴው ሱፐር ስትራክቸር ከተተካ ወዲህ የነበረው ሥርዓተ ማህበር በውድድር ላይ የተመሠረተ የካፒታሊስት ሥርዓት ነው::
ከበርቴው የፖለቲካ ሃይልን ከፊውዳሉ ካላቀቀ በኋላ የርሱ መንግሥት ሥርዓቱን እንዲጠብቀለትና ካፒታል ያለምንም ተጽዕኖ በየአቅጣጫው በጉኝ ሆነ በቁጥ የሚችለውን ያህል የካፒታል ህጉችን በመከተል ለማርባት እንዲችል የሆነበት ነው::



ለወዝአደሩ ለመኖሪያ የሚሆነውን ያህል እየከፈለ ከሌሎች ካፒታሊስቶች ጋር እየተወዳደረ ካፒታሉን የሚችለውን ያህል ለማርባት የዕርባታ ሃይሎችን እያ ሳደገ፣ ያልቻለው እየወደቀ በሌላው እየተተካ የተገበገበት ጊዜ ነበር::

በውድድር ካፒታሊዝም ውስጥ ይካሄድ የነበረው ዕድገት ወዝአደሩን ወደ አስቃቂ ኑሮ እየወረወረው በሌላ በኩል ደግሞ የካፒታልን በጥቂት ከበር ቴዎች እጅ ውስጥ መከማቸትን አስከትሏል:: የካፒታል እንቅስቃሴ የውድድር ካፒታሊዝም የሚሠራበትን የውድድር መስክ እያጣበበ መሄድ የካፒታል እንቅስ ቃሴ ባጠቃላይ የሚከተለው ህግ ነው:: ይህ የካፒታል እንቅስቃሴ አቅጣጫ እራሱ የካፒታሊስት ህብረተሰብ የሚሠራበትን የኢኮኖሚ ህግ ጥያቄ ውስጥ የሚ ያስገባና የካፒታል ህብረተሰባዊ ጠባይን የሚያሳይ፣ የዕርባታ መሣሪያዎች ግለ ሰባዊ ባለቤትነትን የሚፃረር፣ ካፒታሊዝም ውስጥ ያለውን መሠረታዊ ቀራኔ በዕ ርባታ ህብረተሰባዊነትና በዕርባታ ውጤቶች ግላዊ ስብሳቢነት መካከል በይበልጥ የሚያንፀባርቅ ነው::

የካፒታል እንቅስቃሴ አቅጣጫ፣ የውድድር ካፒታሊዝም ቀስ በቀስ በሞኖፖሊ ካፒታሊዝም እየተተካ እንዲመጣ አደረገው:: በመሸጋገሪያው ወቅት ብዙ ትግሎች ተካሄደዋል:: የውድድር ካፒታሊዝም በነፃ መልኩ እንዲሠራ ከበርቴው መከራ አይደርጓል:: ይህ ሁሉ ግን የካፒታሊዝም የዕድገት አቅጣ ጫን ነባራዊ ህግ ሊሽረውና እድገቱን ሊያግደው አልቻለም:: የውድድር ካፒ ታሊዝም ወደ ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም እየተቀየረ ሲሄድ በተለይ የመንግሥት ሚና እንዴትም አበርቶ እየተቀየረ እንደመጣ ማየት ይጠቅማል::

መንግሥት /አስተት/ በመሠረቱ የአንድ የተወሰነ መደብ የጭቆና መሣ ሪያ ነው:: የከበርቴው መንግሥትም የከበርቴውን አገዛዝ ለማቆየት፣ የወዝ አደሩን መበዝበዝ ለመጠበቅ የሚያገለግል የከበርቴው ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ የሰ ፈነበት መሣሪያ ነው:: ፍርድ ቤቱ፣ ቢሮክራሲው፣ ፖሊሱ፣ የወታደር ሃይሉ ወዘተ... የዚህ ፈላጭ ቆራጭነት መሣሪያ ናቸው:: በአንድ በተወሰነ ደረጃ ላይ የከበርቴ መንግሥት፣ በተለይም ያለውን የህብረተሰብ፣ የኢኮኖሚ ዕድገትና እን ቅስቃሴ በሚመለከተው በኩል ካፒታሊዝም እያደገ ወደ ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም እየ ተቀየረ በመጣበት ወቅት መሠረታዊ ይዘቱ ሳይቀየር፣ ግን ሰዱ ሰዱ መልክ እየ ያዘ ሚናው እየተቀየረ መጥቷል:: የውድድር ካፒታሊዝም በነበረበት ጊዜና የሞ ኖፖሊ ካፒታሊዝም ደረጃ ላይ የደረሰ ሥርዓት ውስጥ መንግሥት ባለው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ህይወት ውስጥ የሚጫወተው ሚና የተለየ ነው:: የውድድር ካፒታ ሊዝም፣ የካፒታል መጠራቀም እያስከተለ ካፒታል እራሱን ለማርባት የሞኖፖሊ ጠባቂ ሠርጉ እየገባ መሄዱንና ትናንሽ ከበርቴዎች እየቀረቀሩ ትላልቆቹ እየጠነከሩ

በህብረተሰቡ ውስጥ የሚንቀሳቀሰውን ካፒታል ሙሉ በሙሉ በእጃቸው እያስገቡ ሲሄዱ ይህ ደግሞ በሥርዓቱ ውስጥ ያለውን መሠረታዊ ቅራኔ እያከረረ ሲሄድ ልዩ ልዩ ቀውሶችን እያስከተለ ሲመጣና፣ እራሱ ካፒታሊዝም የተገነባበትን ኢኮኖሚ አደጋ ላይ እየጣለ ሲመጣ፣ የመንግሥትም ሚና እንዴት እየተቀየረ እንደሄደ በሚከተለው ለማሳየት እንሞክራለን::

የውድድር ካፒታሊዝም የፊውዳሉን ስርዓተ ማህበር እንዲተካ መንግሥት በሥርዓቱ ኢኮኖሚ ውስጥ የሚጫወተው ሚና በጣም አነስተኛ ነበር:: የከበርቴው መንግሥት ዋና ተግባር የካፒታሊዝም የኢኮኖሚ ህጎች ተጠብቀው ካፒታል በራሱ ህጎች እንዲንቀሳቀስ ሁሉም ከበርቴ በየፊናው የተቻለውን እየበዘበዘ የዕርባታ ኃይሎችን እያሳደገ ካፒታሉን በተቻለ መጠን እንዲያጠራቅም እንዲወዳደር እያደረገ የበዝባዥ ሥርዓቱን ከበላይ ሆኖ መጠበቅ ነበር:: ማርክስ በተናገረው መሠረት የከበርቴው መንግሥት ሚና የከበርቴውን የጋራ ጉዳይ ማስተዳደር ነበር:: እርግጥ የፖለቲካ ኃይሉ የጨበጠው ሃይል፣ ህግ አስፈጻሚው አካልም ሆነ ህግ አውጪው መሃል ይካሄዱ የነበሩ ትግሎች የልዩ ልዩ ካፒታሊስቶች የጥቅም ግጭትን ያንፀባርቁ ነበር:: ይህ ግን መንግሥቱ እንዳለ በሥርዓቱ የኢኮኖሚ ህይወት ውስጥ ተዋናይ፣ በአጠቃላይ የካፒታል እንቅስቃሴ ላይ ተጽዕኖ እንዲፍር ገና አላደረገውም:: በተጠባባቂ ሚና /ዘበኛ/ የሚጫወትበት ጊዜ ነበር:: የመንግሥቱ ዋና ሥራ የበዝባዡ ሥርዓት በተቻለ መጠን ያለመሰናከል የሚካሄድበትን አካባቢ መፍጠር፣ የወዝአደር እንቅስቃሴን መጨቆን ሲሆን፣ሌላው ደግሞ የሚያተኩረው በዓለም አቀፍ ደረጃ የሀገሩ ከበርቴ ካፒታል በነፃ ድንበር ሳይወሰን /የካፒታል አገዛዝ ድንበር አያውቅምና/ ለመበዝበዝ የሚያስችለውን ምቹ የሃገር ከሃገር ግንኙነት መፍጠር፣ የራሱን ካፒታል ደግሞ ከሌላው ከውጭው ካፒታል መከላከል ነበር::

በካፒታሊዝም ሥርዓት ውስጥ የመንግሥት በኢኮኖሚ እንቅስቃሴው ውስጥ "የተመልካች" ሚና መጫወትና የካፒታል እንቅስቃሴ በራሱ የኢኮኖሚያዊ ህጎች እንዲያድግ መፍቀድ በመጀመሪያው የካፒታሊዝም የዕድገት ደረጃ ብቻ የነበረ ነው:: የካፒታል እንቅስቃሴ እራሳቸውን የቻሉ ገባራዊ ህጎች አሉት:: ካፒታል እራሱን ለማርባት የሚከተለው መንገድ ወደ ከፍተኛ የካፒታል መጠራቀም ውድድርን የሚፃረርና ሥርዓቱ የሚሠራበትን ኢኮኖሚክ ህጎች የሚበረብር ሲሆን በሌላ በኩል ግን ለካፒታል መጠራቀም መሠረቱ ደግሞ እራሱ ውድድር ነው:: ሞኖፖል ካፒታሊዝም ያደገው ውድድርን እየተፃረረ ውድድርን እየተጠቀመ ነው ለማለት ይቻላል:: በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ የመንግሥት በ"ተመልካች" ሚና መወሰን እየቀረ መሄዱን አስከትሏል:: ይህም የካፒታሊዝም ዕድገት በሥርዓቱ ውስጥ ያለውን መሠረታዊ ቅራኔ እያጎላ እያወጣው መቀበሪያውን እያዘጋጀ ይሄዳል:: የዕርባታ ህብረተሰባዊ ጠባይ እየጎላ፣ የካፒታል ህብረተሰባዊ ጠባይ እያደገ መምጣት፣ ከፍተኛ ህብረተሰባዊ የዕርባታ መደራጀትን ይጠይቃል:: ይህ ግን በካፒታሊዝም ውስጥ አይሆንም ሊሆን አይችልምም::



ባጠቃላይ ህብረተሰቡ ውስጥ ባለው የገበያ አናርኪና በእያንዳንዱ የማምረቻ ድርጅት ውስጥ ባለው ዲሲፕሊን መሃል ያለው ቅራኔ ጎልቶ ይታያል:: ከበርቴው ሊሸጥ ከሚችለው በላይ ዕርባታ ያውጋል፣ ወዝአደሩ ኑሮው እየቀዘቀዘ ስለሚሄድ ለመኖር ከሚያሻው በላይ ሊገዛ አይችልም:: ቀውስ ይከተላል፣ የመደብ ትግሉ በከበርቴውና በወዝአደሩ መሃል ይጠነክራል:: በራሱ በከበርቴው ውስጥ በቀርጃሽና በአቀርጃፉ መካከል ቅራኔው ይከራል::

እንግዲህ በዚህ ሁኔታና በዚህ ሂደት የመንግሥት ሚና የ"ተመልካች" ሊሆን አይችልም:: ካፒታሊዝም በራሱ የኢኮኖሚ ህጎች አደጋ ላይ እየወደቀ ነውና:: የመንግሥት በኢኮኖሚው እንቅስቃሴ ላይ ቀጥተኛ ቁጥጥር ማድረግና "ጣልቃ መግባትን" ይጠይቃል:: ለዚህ "ጣልቃ መግባት" ጠቀሳሳው የከበርቴው መደብ ፍላጎት አለው:: የመንግሥት በኢኮኖሚው ህይወት ላይ ያለው ሚና፣ ለጥቀሳሳው የበዝባዥ ሥርዓት መቀየት ከበርቴው አስፈላጊ ሆኖ ስላገኘው ይቀየራል ማለት ነው::
መንግሥት ከዚህ ዕድገት ውስጥ ልዩ ልዩ መሰከን እየወሰደ ከመምጣቱ በላይ የበዝባዡ ሥርዓት በሚገባ እንዲንቀሳቀስ ልዩ ልዩ መሣሪያዎች /ፖለቲካል ኢኮኖሚካል ወዘተ.../እያበጀ መጥቷል:: የካፒታሊስት ህብረተሰብ የኢኮኖሚ አናርኪን በከበርቴው መንግሥት ሙሉ ቁጥጥር ሥር ለማድረግ ከፍተኛ ሙከራ የተደረገው በፋሺዝም ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ውስጥ ነው::

### 3./ ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ውስጥ በዕርባታ ሃይሎችና በዕርባታ ግንኙነቶች መሃል ያለው ቅራኔ ትርጉም

የውድድር ካፒታሊዝም እንዴት በሞኖፖሊ ካፒታሊዝም እየተተካ እንደመጣ፣ የካፒታል እንቅስቃሴ ዕድገት ወደዚሁ እንዴት እንደሚያመራ፣ ባጭሩም ቢሆን አይተናል:: በዚህን ጊዜ መንግሥት በኢኮኖሚ ውስጥ የሚኖረው ሚናም በገዱ መቀየርና እየተቀየረም እንዲመጣ ተመልክተናል:: የፋሺዝም ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካል መሠረት ምን እንደሆነ ለማየት ግን በሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ውስጥ በዕርባታ ሃይሎችና በዕርባታ ግንኙነቶች መካከል ያለው ቅራኔን ምንነት መመልከት፣ ወደፊት ለምናደርገው ትንተና፣ ይጠቅመናል:: ይህ ቅራኔ መቼ ማርክስ የዛሬ 120 ዓመት ገደማ ያለውን የማንኛውንም ህብረተሰብ ዕድገት የሚያንቀሳቅሰው መሠረታዊ ህግ "... At a certain stage of their development, the material productive forces of society come in conflict with the existing relations of production ... From forms of development of the productive forces these relations turn into their fetters ... then comes a period of social revolution."

የሚያንፀባርቅ ለመሆኑ ጥርጥር የለውም:: በሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ውስጥ ይህ ቅራኔ ፈንድቶ ከበርቴው እንዴት አድርጐ ከዚህ ማርከበ ከሚለው ለውጥ በፋሽዝም አማካይነት ሥርዓቱን እንዳዳነ ለማየት ይህን ቅራኔ ጠለቅ ብሎ ማየት ይጠይቃል::

ካፒታሊዝም የዐርባታ ሃይሎች እንዲያድጉ የተጠቀሙት ታሪካዊ ተራማጅ ዐርምጃ አበቃቶ በሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ውስጥ የነዚሁ የዐርባታ ሃይሎች ዕድገት የታፈነበት ሥርዓት፣ የዐርባታ ሃይሉን ለማሳደግ ከፍተኛ የህብረተሰባዊ የዐርባታ መደራጀት የሚጠይቅበት ደረጃ ይደርሳል:: የሞኖፖሊ ካፒታሊዝም መምጣት፣ ከካፒታል ከምችት ሂደት ጋር የሚስማማና የርሱም ውጤት ነው:: ይህ የካፒታል መጠራቀም በውድድር ውስጥ የሚመጣ ነው:: ለመጠራቀም የሚወዳደረው ይፈለጋል፣ ግን ሲጠራቀም ደግሞ ውድድርን ይጻረራል:: ሁለት ገጽ አለው ማለት ነው:: በዚህ ቅራኔ ውስጥ ነው ካፒታል በሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ውስጥ የሚንቀሳቀሰው:: አጠቃላይ አቀጣጫው ግን ካፒታል ያው በጥቂት ካፒታሊስቶች እየተጠራቀመ ሌላው እየወደቀ እየቀረ ቁዝ ነው የሚሄደው:: ሌኒን

" Monopoly which has grown out of capitalism and exists in general environment of capitalism,commodity production and composition,in permanent and insoluble contradiction to this general environment"

ይለዋል:: የካፒታል መጠራቀም ባንድ በኩል የዐርባታ ሃይሎችን እድገት ማፋጠንን ያስከትላል፣ ማለትም ካፒታል እራሱን የበለጠ የሚያረባው መጠኑ ትልቅ በሚሆንበት ወቅት ነው:: ነገር ግን በሌላ በኩል የካፒታል ሞኖፖሊ የዚህን ዕድገት የማፈን ጠባይ አለው:: ካፒታል ባንድ በኩል ያለወሰን ለመርባት ይፈልጋል፣ ሆኖም ነባራዊ ወሰን አለው:: እዚህ ቅራኔ ውስጥ ያለው ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም በየጊዜው የኢኮኖሚ ቀውስ ላይ ይወድቃል:: በገዥ መደብ ውስጥ ሃይለኛ የፖለቲካ ቀውስ ይፋፋማል:: የመደብ ትግሉ ይጠነክራል፣ ጦርነት ወዘተ... ይከተላል::

በሞኖፖሊ ካፒታሊዝም የዐርባታ ጥቅም በጥቂት ሞኖፖሊስቶች እጅ እየተጠራቀመ፣ የሰፊው ሕዝብ ኑሮ እያሽቆለቆለ፣ በከበርቴው መደብ ውስጥ ያለው ትናንሽ ባለንብረት እየወደቀ፣ ወዝአደሩ ከመቼውም ይበልጥ እየተበዘበዘ ይሄዳል:: በዐርባታ ግንኙነትና በታዳጊው የዐርባታ ሃይል መሃል ያለው ቅራኔ ገለጥለጥ ብሎ የሚታይበት ነው:: ከእንግዲህ የዐርባታ ሃይሉን ለማሳደግ የዐርባታው ግንኙነት መቀየርን፣ ከፍተኛ ህብረተሰባዊ መደራጀትን ይጠይቃል:: ይህ ከፍተኛ ህብረተሰባዊ መደራጀትና በካፒታሊዝም ውስጥ ያለውን መሠረታዊ ቅራኔ መፍታት የላአላይ መዋቅሩን/ሱፐር ስትራክቸር/ ጠቅላላ መቀየር ይጠይቃል:: በዐርባታ ህብረሰባዊ ጠባይና በዐርባታ ውጤት ግላዊ ተጠቃሚነት መሃል ያለውን ቅራኔ ለመፍታት ጠቅላላ ህብረተሰባዊ አብዮትና፣ የተለቀ ካፒታል አገዛዝ ሞኖፖሊ ካፒታሊዝምን በወዝአደሩ መሪነት መደምሰስ ያስፈልጋል::



ይህን ለማድረግ ቁስ አካላዊ መሠረቱ ተሟልቷል/ማለት በአጠቃላይ ነባራዊ ሁኔታው አለ/: ቅራኔው ተፋፍሟል፣ የወዝአደሩ መደብ ከፍተኛ በዝበዛ ይደርስበታል ወዘተ...ይህ ግን ድርጅታዊና የፖለቲካ ንቃት መሟላትን ይጠይቃል:: ህብረተሰባዊ ለውጡ ሊደረግ ባልቻለበት ሁኔታና የፖለቲካ ሀይል በሞኖፖሊ ካፒታሊስት እጅ ውስጥ እንዳለ በሚቆይበት ጊዜ፣ እንግዲህ የተፋፋመው ቅራኔ በተለቀ ከበርቴ በምን ዓይነት መልክ "መፍትሄ" ሊሰጠው ይሞከራል? ይህ ጥያቄ የፋሽዝም ምንነትን ለመረዳት መሠረታዊ ይሆናል::ፓለመ ዱትን ባጭሩ እንጥቀስና እንለፍ በሌላ በታ በአጠቃላይ እንደርስበታለን::

" Two alternatives,and only two,confront existing society at the present stage of development of the productive forces and of social organisation.

One is to throttle the development of the productive forces in order to save class-society,to destroy material wealth,to destroy millions of 'superfluous' human beings in the slow rot of starvation and the quick furnace of war,to crush down the working-class movement with limitless violence,to arrest the development of science and culture and education and technique, to revert the more primitive forms of limited,isolated societes, and thus to save for a while the rule of the possessing classes at the expense of a return to barbarism and spreading decay.This is the path which finds its most complete and organised expression in Fascism.The other is to organise the productive forces for the whole society by abolishing the class ownership of the means of production,and building up the classless communist society which can alone utilise and organise the modern productive forces.This is the path of Communism,of the revolutionary working class."

እስካሁን ለማሳየት የሞከርነው የፋሽዝም ሥረ መሠረት፣ እንዲሁም የሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ዕድገትና በካፒታሊዝም ውስጥ ያለውን መሠረታዊ ቅራኔ ነው:: ይህም በአጠቃላይ ደረጃ ሲሆን፣ ወደ ልዩ ልዩ ሁኔታ በሚገባበት ወቅት ግን ልዩ ልዩ መልክ ሊኖረው የሚችል መሆኑን መዘንጋት አያሻም::ቢሆንም ከዚህ አጠቃላይ ሳይንሳዊ ዕውነት ግን ሊወጣ አይችልም::

ቀደም ብለን የመንግሥት ሚና በሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ውስጥ እንዴት በኢኮኖሚ ህይወት ውስጥ ቀጥተኛ ቁጥጥርና ተፅዕኖ ማድረግ እንደጀመረ፣ እንዴትም ያለው ቅራኔ አስፈላጊ እንዳደረገው አይተናል ::ፋሽዝምን ለመረዳት ግን ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ታላቅ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የሶሽያል ቀውስ ውስጥ ሲገባና ሥርዐቱ የመንኮታኮት አደጋ ላይ ሲወድቅ፣ የከበርቴው መንግሥት በሞኖፖሊ ካፒታሊዝም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ ከሚኖረው የተለወጠ ሚና የሚመነጭ ነው ብቻ ማለቱ አይበቃም ዋና ዋና ጥያቄዎችን በተለይም የመደብ ትግሉን፣ የመደብ አሰላለፉን፣የ"ኢጣሉ"ን ሥርዓት ተሸከሚ፣ የመደብ ይዘቱን፣

በህብረተሰቡ ውስጥ የነበረው የመደብ መንሸራሸር፣ ከበርቴው በጥንት መሰሎ ለመገዛት ለቃን እንዳልቻለ፣ መመርመር አስፈላጊ ስለሚሆን ወደዚህ ክፍል እናልፋለን:: እስከአሁን ያየነው የሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ቀውስ የፋሽዝም መምጣት ሥር መሠረትና ታሪካዊ ቅድመ ሁኔታ /ፕሪከንዲሽን/ መሆኑን ነው::

## II- የፋሽዝም ቅድመ ሁኔታዎች፣ የመደብ ይዘቱና ህዝባዊ መሠረቱ

ፋሽዝም የሞኖፖሊ ካፒታሊዝም መሠረታዊ ቅራኔ ውጤት፣ የፖለቲካ የኢኮኖሚና የሶሺያል ቀውስ ውጤት ለመሆኑ፣ ስለፋሽዝም የጻፉ ተራማጆች በሙሉ የተስማሙበት ነው:: ስለፋሽዝም ብዙ ጸሁፎች ተጽፈዋል:: በተለይም በጣሊያንና በጀርመን ከታዩት ታሪካዊ ተጨባጭ ሁኔታዎች በመነሳት የየትኛው መደብ አገዛዝ እንደሆነ ከትልቁ ካፒታል ጋር ያለው ግንኙነት ምንድነው? የትልቁ ካፒታል፣ የፋይናንስ ካፒታል "ቀጥተኛ አገልጋይ" ነበር ወይ? ምን ዓይነት የፖለቲካና የኢኮኖሚ ቅድመ ሁኔታዎች ነበሩ? ወዘተ... ለምን ወዝአደሩ የሶሺያሊስት አብዮትን አውርጐ በህብረሰቡ ውስጥ የነበረውን መሠረታዊ ቅራኔ አልፈታም? የሚሉትን ጥያቄዎች በማንሳት ብዙ ጥናቶች ተደርገዋል::

እነዚህ ጥያቄዎች ላይ የተሰጡትን የተለያዩ አስተያየቶችን ሁሉ እየተነተንን ማስተባበያ ወዘተ. ለመስጠት አንነሳም:: ነገር ግን በእኛ አስተያየት ትክክለኛውን አጠቃላይ መሠረት ለመጣልና እንዴት የ7ተኛው የኮምኒስት ኢንተርናሽናል ጉባኤ የሰጠው ትርጉም ማለትም ፋሽዝም የፍጹም አውሃሪው፣ ተምክህተኛና ኢምፔሪያሊስታዊ የሆነው የፋይናንስ ካፒታል አንዱ ክንፍ አገዛዝ እንደሆነ ለማሳየት እንሞክራለን:: ይህን ለማድረግ ብዙ ማንሳት ያለብን ጥያቄዎች አሉ::

በሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ውስጥ ያለው የኢኮኖሚ ሁኔታ ምን እንደሆነና ያለው ህብረተሰባዊ መደርደት እንዴት ወደኋላ እንደቀረና ይህ ደግሞ ቀጥታ ከካፒታሊዝም መሠረታዊ ቅራኔ ጋር እንደተያያዘ አይተናል:: ይህ መሠረታዊ መፍትሔ የሚያገኘው በሶሺያሊስት አብዮት መሆኑ ግልጽ ነው:: እንዴት በፋሽዝም የካፒታሊስት የዕርባታ ዘዴን በማቆየት ሥርዐቱን ከመንኮታኮት ለማዳን ትልቁ ከበርቴ ቻለ? የሚለውን ለመመለስ ጠለቅ ያለ የመደብ ትግል ትንተና ያስፈልጋል:: ይህ ብቻ አይደለም የከበርቴው "ዲሞክራሲያዊ" ሥርዓት ባለበት ሁኔታ የካፒታሊዝም አሠራር መካኒክን መመርመርና ከበርቴው ቀውስ ውስጥ ሲዋጥ ለቀራኔው በተለየ የመንግሥት አይነት መፍትሄ እንዴት እንዳገኘለት፣ ምንስ መለክ እንደሚይዝ ማየት ያሻል:: ከዚያ የፋሽዝም የመደብ ይዘት፣ ህዝባዊ መሠረት ምን እንደሆነ ማየት አስፈላጊ ነው::



### 1./ በመደቦች ውስጥ የተካሄደ ለውጥና አጠቃላይ ዕድገት

በሞኖፖሊ ካፒታሊዝም እያደገ በመጣበትና የከበርቴ ዲሞክራሲ አበቦትም በነበረበት ወቅት፣ በየህብረሰቡ ውስጥ ያሉት መደቦችና የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ ያስከተለውን ለውጥ እንመለከት::

ካፒታሊዝም እያደገ በሚሄድበት ወቅት አንዱ የማያጠራጥር የዕድገት አቀጣጫ አለ:: የተናንሽ የዕርባታ መሣሪያ ባለቤቶች ዕርባታቸው እየቀረ ቀዝ ወደ ወዝአደርነት እየተቀየረ መሄድ ነው:: በሌላ በኩል ደግሞ የተሳለቀ የዕርባታ መሣሪያ ባለቤቶች ትናንሾን እያቀረ ቀዙ ቁጥራቸው እያነሰ፣ በእጃቸው የሚያከማቹት የእርባታ መሣሪያ እያደገ ይሄዳል:: ይህ ሂደት የከበርቴውን መደብ በውስጥ መስነጣጠቅና መከፋፈል ያመጣል:: ትልቅ፣ መካከለኛ፣ አነስተኛ ከበርቴ:: ከዚህ ውስጥ ትልቁ ከበርቴ ወደ ሞኖፖሊ ከበርቴ እየተቀየረ ይሄዳል:: ይህ ያለችግር ሊከናወን የሚችለው የካፒታል መጠራቀም ወሰን በማይጠበበት ጊዜ ነው:: የካፒታል መጠራቀም ወሰን የፈለገውን ያህል ሊሰፋ ስለማይችል /የውስጥም ሆነ የውጭ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ምክንያቶች አሉት/ አንዱ ሥርዓተ ማህበር የሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ደረጃ ሲደርስ የካፒታል መጠራቀም ወሰን በሶስት ዋና ዋና ነገሮች ይጠበላ:: 1./ የካፒታል ማባከን /ሥራ ላይ ለዕርባታ በቀጥታ አለማዋል/ ለምሳሌ ባንዱ በተወሰነ ሁኔታ የኢምፔሪያሊስቶች የዓለም ክፍፍል ለአንዱ ለተወሰነው ኢምፔሪያሊስት ነገ የሚፈልገውን ያህል ካፒታል ኤክስፖርት ለማድረግ አይቸለም/ 2./ ቀጥታ ለዕርባታ የማይውል ህብረሰባዊ ወጭ ማድረግ /አስቤሲዎሪ ስስት/ 3./ የዕርባታ ዕድገት መጠን ባንዱ በተወሰነ ደረጃ ከሚፈቅደው ቴክኒካዊ ዕድገት በታች መሆን:: እነዚህ ሶስት ሁኔታዎች በህብረሰቡ ውስጥ አዳዲስ የህብረሰብ ክፍሎች መፈጠርን ያስከትላሉ:: በህብረተሰቡ ውስጥ ያሉት መደቦች ውስጥ አዲስ ንዑስ ክፍፍሎች ይከተላሉ ማለት ነው:: በህብረተሰቡ ውስጥ የተፈጠረውን አዲስ የመደቦች መንሸራሸር ዳይናሚክ እንመለከት::

ሀ/ በሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ሥርዓተ ማህበር ውስጥ ያለው መሠረታዊ ቅራኔ ካስከተላቸው ነገሮች ውስጥ አንደኛው በዕርባታ ውስጥ በቀጥታ የማይሳተፉ የህብረሰብ ክፍሎች ማደግ ነው:: ለምሳሌ የሥራ አጥ ማደግ፣ የጡረተኛ መብዛት፣ የነዚህ ማደግና በመንግሥቱ ዕርዳታ መተዳደር /ዕርዳታ በሚሰጥበት ቦታ/ እንደ ዕርዳታ መታየት ያለበት ነገር ባይሆን እራሱ ሥርዓቱ ውስጥ ያለው የኢኮኖሚ ሁኔታ የሚጠይቀው ነው:: የካፒታል የዕርባታ እድገት ወሰን በሚጠበበት ወቅት የካፒታል ማባከንን የግዴ ስለሚያስከትልና የተወሰነ ካፒታል ደግሞ ከዕርባታ ውጭ መሆን ስለአስፈለገ ለዚህ ይውላል:: የሥራ ፈት ቁጥር ማደግና ምን ጊዜም ቢሆን የተወሰነ ቁጥር የግዴ መገኘት ከካፒታል ማባከን ጋር የተያያዘ ነው:: በጡረታ የሚተዳደሩ የህብረሰብ ክፍሎች እያደጉ መምጣት የካፒታሊዝም ዕድገት ያስከተለው ነው::

ለ/ በዕርባታ ውስጥ በቀጥታ የማይሳተፉ በማከፋፈያና በማስተዳደሪያ መሣሪያ /አፓራተስ/ ውስጥ የሚሳተፈው የህብረተሰብ ክፍል እያደገ መምጣት ሌላው የካፒታል መጠራቀም ውጤት ነው:: የዚህ ህብረሰብ ክፍል ለካፒታሊስቱ የሚያስፈልገው ስለሆነ የግዱ እያደገ መምጣቱና መስፋፋቱ አልቀረም:: ለምሳሌ በንግዱ፣ በባንክ አስተዳደር ከዚያም የመንግሥቱ አስተዳደርና የጦር ኃይል ማደግ፣ የነዚህ የህብረተብ ክፍሎች ገቢ የወዝአደሩ የሥራ ኃይል የሚያደርገው ትርፍ ሥራ መሆኑ ግልጽ ነው::

ከላይ በሀ/ እና በለ/ ያየነው በዕርባታ ውስጥ በቀጥታ የማይሳተፈው የህብረሰብ ክፍል እየበዛ መምጣት በሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ውስጥ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሷል:: "The decline in the industrial productive workers was to be'compensated' by the increase of auxiliary 'services' and luxury occupations(clerical,distributive,advertising,commercial and luxury services).Certainly a very considerable increase in the auxiliary and in the main non-productive occupations is to be traced in the U.S.,Britain and other countries /ሞኖፖሊ ካፒታሊስትአገሮች/during the post-war period,then providing the basis of the rapid expansion of the so-called 'new middle class',which became one of the breeding grounds of Fascism;just as the growth of <u>permanent</u> unemployment army provided a further breeding ground.<u>The expansion of the rentrer class on the one side and of luxury services and endlessly multiplied</u> 'salesmenship' services on the other,<u>is a measure of the degeneration of capitalism</u>."

እነዚህ የህብረሰብ ክፍሎች ኑሮአቸው ከከበርቴው መንግሥት ጋር በቀጥታ የተያያዘ /ዲፔንዲንት/ ነው::

ጠ/ በወዝአደሩ መደብ ውስጥ የተፈጠሩ ንዑስ ክፍፍሎች እንደሚታወቀው ካፒታሊዝም በተወለደ ዘመኑ የዕርባታ ኃይሎችን በፍጥነት አሳድጓል:: የዕርባታ ኃይል እያደገ ሲመጣ ሚካናይዜሽን እየሰፋ ሲሄድ ከዕርባታ ጋር ቀጥተኛና ቀጥታ ያልሆነ ግንኙነት ያላቸው በወዝአደሩ ውስጥ ልዩ ልዩ ንዑስ ክፍሎች ተፈጥረዋል:: 1ኛ/ ከዕርባታ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው ትርፍ ዋጋ /ሰርፕለስ ቫሉ/ የሚፈጥረው ወዝአደር፣ 2ኛ/ ፋብሪካውን የሚያስተዳድር ተቀጣሪ የቢሮ ሠራተኛ፣ እንጂነርና ቴክኒሽያን የመሳሰሉት ክፍሎች አሉ::



ይኸኛው ክፍል ያለበት የኤኮኖሚ ደረጃ ሲታይ ከወዝአደሩ በመጀመሪያ በብዙም አይለይም ነበር:: ሆኖም ባለው አስተሳሰብና በህብረሰቡ ውስጥ በሚሰጠው ቦታ /ስታተስ/ ወደ ከበርቴው ለመጠጋት ይሻል:: ንዑስ ከበርቴው መደብ ውስጥ ለማጠቃለል ይቻላል:: 3ኛ/ የሥራ ፈቱ እና የሥራ አጡ ክፍል ናቸው:: የሥራ አጡ /ዕርዳታ የሚያገኘው/ የሚኖረው ጠቅላላ በዕርባታ ላይ በሚሳተፈው ወዝአደሩ በሚሰራው ሥራ ነው:: ስለዚህም ይኸኛው ክፍል ከመንግሥቱ ቀጥተኛ ጥቅም ሊኖረው ይችላል:: ይህ እንግዲህ የሥራ አጥነት ዕርዳታ የሚያገኝ እንደሆነ ነው:: ስለሆነም ከወዝአደሩ የተለየ "ፓራሳይት" /ጥገኛ/ ጥቅም ሊኖረው ይችላል:: በመሠረቱ ግን ያው ከወዝአደሩ ጋር ተመሳሳይ ፍላጎት ሥራ ፈቱም ሆነ ሥራ አጡ እንዳለው ግልጽ ነው:: ሆኖም የቀውስ ሁኔታ ባለበት ጊዜ የ"ፓራሳይት/ ጥቅሙ ያመዝናል:: ባጠቃላይ ለማለት የሚቻለው ወላዋይ አቋም እንዳለው ብቻ ነው:: ከከበርቴው መንግሥት ጋር በጥቅም የተያያዘው፣ መንግሥቱ ፋሽስታዊ ሲሆን ህዝባዊ መሠረቱን ከሚፈጥሩት አንደኛው ክፍል ነው::

መ/ ትናንሽ ባለሃብቶች አየወደቁ፣ የኤኮኖሚ መሠረታቸው እየተደመሰሰ ብዙው ወደ ወዝአደርነት ያሽቆለቁላል:: ግን በዕርባታ ውስጥ በቋሚ ጊዜ ቦታ ሊያገኝ ስለማይችል፣ በዕርባታ ውስጥ የሚካፈል "ወዝአደር" ሊሆን አይችልም:: ስለዚህ ያለው ምርጫ የኑሮውን ዋጋ በጣም እየቀነሰ በአስቃቂ ሁኔታ እየኖረ እንደምንም ብሎ ለመንቀሳቀስ መጣር ነው:: ዕጣ ውስጥ መግባት ነው:: ወይንም ሥራ ፈት በዘኑ ክፍል ውስጥ መደባለቅ ነው::

በአጠቃላይ በመደቦች ውስጥ ከሚኖረው የመንሸራሸር ዳይናሚክ ጋር ባንዱ በኩል የልዩ ልዩ የዕርባታ ክፍሎች መስፋፋትን ሲመጣ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የዕርባታ ዕድገት መታፈን ተከትሏል::መሃከለኛ ሀብት ያለው የተወሰነው የከበርቴ ክፍል በየጊዜው በዙ ዕጣ ውስጥ እንዲገባና ዕርባታውን ለመቀጠል በየጊዜው ከመንግሥቱ ዕርዳታ /ሰብቬንሽን/ የሚያስፈልገው ደረጃ ላይ እንዲወድቅ አድርጎታል:: ይህ ሁኔታ በብዛት የሚመለከተው ባለትናንሽ ሃብትን ንዑስ ከበርቴውን ነው::

ይህ የንዑስ ከበርቴ ክፍል በትልቁ ካፒታል መቆርቆዝ የተነሳ ሥርዓቱን በመቃወም ይነሳል:: ተቃውሞው ግን ወሰን አለው:: ከትልቁ ካፒታል "የሚከላከልለትን መንግሥት" የኑሮውን ዋስትና ሊሰጠው የሚችል የሚመስለውን ሃይል ይደግፋል:: ንዑስ ከበርቴው የሚሻው ለውጥ፣ ያለውን ህብረሰብ ለኑሮው አስከተወሰነ ደረጃ ድረስ ምቹ የሚያደርግለት ደረጃ ድረስ ነው:: የትንሽ ካፒታል በትልቁ መጨቆኑን ሊያነሳለት የሚችል "መንግሥት" ይሻል::

ወዝአደሩ ጠቅላላ ሃይል ስላሆነ ከንዑስ ከበርቴው ጋር ቅራኔ አለው፣ ፋሽስታዊ እንቅስቃሴዎች ግን በሚያደርጉት መለኪያ /ለፍርም/ ፀረ ትልቅ ካፒታል ቀስቃሽና ፕሮፖጋንዳ፣ ከዚያም ብሄራዊና ሶሽያል ዴማጎጂ በዚህ ክፍል/ከንዑስ ከበርቴው/ ውስጥ ህዝባዊ መሠረት ያገኙበት ነው::

## 2./ <u>የከበርቴ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት</u>

ካፒታሊዝም ሲንሰራራ መደቦች በየረድፋቸው በየመለክ መለኪያቸው እየተራቆ በፍጥነት መምጣት በሰፊው የታየ ነው:: የወዝአደሩ መደብ በመጀመሪያ በሙያ ማህበሩ፣ ከዚያም የፖለቲካ ንቃት እያገኘ ሲሄድ በፖለቲካ ድርጅቱ ሲደራጅ፣ የከበርቴው መደብም እንዲሁ በ"አሠሪ" ማህበርና የመሳሰሉ የበዝባዥ ድርጅቶች እየተደራጀ መጣ:: ትናንሽ ባለሃብቶችም/ንዑስ ከበርቴው/ በየሙያቸው ገበሬውም እንዲሁ የድርጅት ይዘታው ከካፒታሊዝም ጋር ዕያደገ መጣ::

የከበርቴ ዴሞክራሲ በህብረተሰቡ ውስጥ ከሰፈነ በኋላ የምርጫ መብት እና ሌሎች ዴሞክራሲያዊ መብቶች የፖለቲካ ፖርቲ መቋቋም ወዘተ.. ሁሉም በየፖለቲካ ድርጅቱ መደራጀት ጀመረ:: እርግጥ ከዚያም በፊት የፖለቲካ ድርጅቶች ነበሩ ጠቅላላ መልካቸው ግን ብዙውን ጊዜ በፊውዳል አስተሳሰብ የተመረዘ ስለነበር የከበርቴው ድርጅቶች በልዩ ልዩ ቤተሰብ ላይ የተመሠረተ ነበሩ:: የምርጫ መብት ሲመጣና የካፒታል አገዛዝ ሠርጎ ሲገባ ግን ዋናው የካፒታል ባለቤትነት ስለሆነ ቤተሰብና አጥንት ቆጠራ የሚጫወተው ሚና እየጠፋ መጣ::

ከበርቴው በልዩ ልዩ የፖለቲካ ፖርቲዎች ሲደራጅ የአጠቃላይ የሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ጥቅም ጠባቂ መስሎ ነበር የሚቀርበው:: በአጠቃላይ "የህዝብ ለህዝብ"፣ ለሁሉም የቆምኩ ነኝ በማለት ይቀርብ ነበር:: ከወዝአደሩ የፖለቲካ ድርጅት በስተቀር የመደብ ይዘቱን ገልጥልጥ አድርጎ፣ የካፒታል አገዛዝን ለማጥፋት የተነሳ፣ የከበርቴ ሥርዓትን ለማውደምና የራሱን አገዛዝ መመሥረት እንደሚያስፈልግ አቋሙን የሚናገር ሌላ የፖለቲካ ድርጅት አልነበረም::

የፖለቲካ ሃይል ጥያቄ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍልና መደቦች በቀጥታ የሚመለከት ዋና ጉዳይ ነው:: ሁሉም በ"መንግሥት" ደረጃ እራሱን ለማስወከልና ጥቅሙን ለማስተጋባት የሚችል እንዲሆን ይሻል:: የወዝአደሩ መደብ ብቻ፣ ያለው ሥርዓት ካልተደመሰሰ የፖለቲካም ሆነ የኢኮኖሚና የሶሻል ዘላቂ ጥቅሙን ሊያስጠብቅ ስለማይችል የፖለቲካ ሃይል በመሠረታዊ



ለውጥ በአብዮት እጁ ማስገባት እንደሚያስፈልገው ያውቃል:: የካፒታል ሥርዓት እያለ ግን ንዑስ ጥቅሙን ለማስጠበቅ እንደመታገያ መድረክ ፖርላማ የመሳሰሉትን የከበርቴውን ኢንስቲቱሽኖች በተለያየ ጊዜ ሊጠቀምባቸው ይችላል:: የከበርቴው መደብ ግን በፖርላማው አማካይነት አጠቃላይ የሥርዓቱን ህጎች የሚያስጠብቅለት ይሻል:: ልዩ ልዩ የከበርቴው መደብ ረድፎች ከልዩ ልዩ የፖለቲካ ድርጅቶች ሊወከሉ ይችላሉ ዋናውን ሚና የሚጫወቱና የሚጠበቀው ዋና ጥቅም ግን ያም ሆነ ይህ በተወሰነ የካፒታሊዝም ዕድገት ደረጃ የሚያይለው የከበርቴ ክፍል ነው:: ለምሳሌ በሞኖፖል ካፒታሊዝም ጊዜ የፋይናንስ ካፒታሊስት ጥቅም የተጠበቀ ይሆናል::

የፖርላመንታሪ መንግሥት ለከበርቴው የመረጠው ከፍተኛ የዴሞክራሲ ዓይነት ነው:: የከበርቴው ልዩ ልዩ ክፍሎች በፖርላማው ውስጥ ይወከላሉ:: በየአራት ዓመት /እንደየቦታው ሊለያይ ይችላል/ ህዝቡን እንወክላለን በለው እንዲገዙ "ይመረጣሉ":: በፖርላማው ውስጥ መሃከለኛው ከበርቴም ሊወከል ይችላል:: ግን በዚያው በከበርቴው ሥርዓት መካከል መወሰን አለበት:: የከበርቴው የመደብ አገዛዝ የሚረጋገጠው ሁሉም በዚህ በከበርቴው ሥርዓት ማህበር እንዲወሰን ከተደረገ ስለሆነ የሌላው መወከል ችግር እንደማይፈጥር የታወቀ ነው:: በእንደዚህ ሁኔታ ልዩ ልዩ የመደብ ክፍሎች በፖርላማው ውስጥ ይወከሉና ይሠራሉ::

በከበርቴው ዴሞክራሲ የተመሠረተ የከበርቴ አገዛዝ ሁለት አካል "የህግ አስፈጻሚው" እና "የህግ አውጭው" የአሠራር ግንኙነትና ልዩነት ሥርዓቱን ያቀየዋል:: "ህግ አስፈጻሚው" ባለው አጠቃላይ ቢሮክራሲና የጦር ኃይል ወዘተ. አማካይነት ለከበርቴው በዝበዛ "ሥነ ሥርዐት" ያስጠብቅለታል:: "ህግ አውጭው" አካልም በፊናው ለበዝባዡ ከጠቅላላ የከበርቴው መሠረታዊ የአሠራር ደንብ ጋር ሊጻረር የማይችል ልዩ ልዩ ደንቦች ያወጣል:: የሁለቱ አንድነትና ልዩነት የከበርቴው ሥርዓት ማህበርና መካከል እንዲሠራ ያደርጋል:: የነዚህ ሁለት አካሎች አሠራር መካከል የሚቃወሰው ኢኮኖሚ ቀውስ ሲመጣና በገዢው መደብ ውስጥ ከፍተኛ የፖለቲካ ቀውስ ሲያስከትል፣ የመደብ ትግል በህብረተሰቡ ውስጥ ሲፋፋም፣ በስምምነት አንድነታቸውንና ልዩነታቸውን ይዘው መንቀሳቀስ፣ መሥራት ያቅታቸዋል:: በሁለቱ አካሎች መሃከል ሃይለኛ ቅራኔ ይፈጠራል፣ የክራይሲሱ ነፀብራቅ ልዩነታቸው እንዲያመዝን ያደርገዋል::

ፋሽዝም ሲመሠረት፣ የከበርቴ ዴሞክራሲ መደምሰስ "ህግ አውጪውን" አካል ከሥራ ውጭ ማድረግ ከዚህ ጋር የተያያዘ ነው:: ሌላው በህብረተሰቡ ውስጥ ያለው የልዩ ልዩ መደቦችና የህብረተሰብ ክፍሎች በነፃ መንቀሳቀስ በፋሽዝም ፍጹም ይጠፋል::

እንግዲህ ከዚህ በቀውስ ሁኔታ የከበርቴው ዲሞክራሲ እንዴት ከጥቅም ውጭ እንደሚሆንና ምን መልክ እንደሚኖረው ማየት ይጠቅማል:: የፋሽዝም እንቅስቃሴ በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ መንሰራራት እንዴት የከበርቴው አገዛዝን ከውድቀት የማዳን ሚና እንደሚጫወት ለማየት ይረዳል::

3./ <u>የካፒታሊስት ሥርዓት ከፍተኛ የኤኮኖሚ ቀውስ ውስጥ ሲዋጥ የመደቦች አሰላለፍና የሥርዓቱ "ዲሞክራሲያዊ" አሠራር ከጥቅም ውጭ መሆን</u>

ካፒታሊዝም ከፍተኛ ቀውስ ውስጥ ሲገባ ለወዝአደሩ መደብ በነባር አብዮታዊ ሁኔታ ይኖረዋል:: የወዝአደሩ መደብ ባደረገው የነቃ የተደራጀ ትግል አጠቃላይ ህሊናዊ ሁኔታውንም አሟልቶ ሊሆን ይችላል:: በዚህ አብዮታዊ ሁኔታ የወዝአደሩ መደብ የነቃ የተደራጀና የታጠቀ አብዮታዊ ሃይል ለማሰለፍ ከቻለ በሚያደርገው የመደብ ጦርነት የፖለቲካ ሃይል ይጨብጣል:: ካልተሳካለት ግን ከበርቴው በተለይ ፋይናንስ ካፒታል ሥርዓቱን እንደምንም ያድናል::

በከበርቴው ሥርዓተ ማህበር ውስጥ ቀውስ በሌለበት ወቅት የከበርቴው ዲሞክራሲ ሥራ ላይ በሚውልበት ጊዜ ከበርቴው ሠራተኛውን እየበዘበዘ ከሞላ ጎደል በ"ሰላም" ይገዛዋል:: አብዮታዊ ሁኔታ የሌለበት ወቅት ነው:: ስለሆነም አገዛዙ በእጁ ውስጥ ነው:: በፓርላማው ውስጥ የሚወከሉት የከበርቴው የተለያዩ የፖለቲካ ቡድኖች ከሞላ ጎደል ያላቸው ሀይልና ድጋፍ ከፍተኛ ነው:: ከትልቁ ከበርቴ እንስቶ እስከ "የመደብ ንቃቱን ያላገኘው" የወዝአደር ክፍል ድረስ ድጋፍ አላቸው፤ ሁሉም በተደራጀበት መልክና የሚወክለው በሚመስለው የፖለቲካ ሃይል ዘንድ ይሰለፋል:: ሥርዓቱ ከፍተኛ ቀውስ ውስጥ ሲገባ ይህ አሰላለፍ መቀያየር ይጀምራል:: የደጋፊዎቹ መንሸራሸር ይኖራል::

ላብአደሩ የኑሮው ዋስትና በዚህ ሥርዓት ውስጥ እንደሌለው ይመለከታል፤ ያለበትን ብዝበዛ በሚገባ ይረዳል:: ንዑስ ከበርቴው ኑሮው እየቀረቀዘ እንደሚሄድ፤ ትላልቁ ከበርቴ ይበልጥ እየባለገ እንደሚሄድና ንዑስ ከበርቴው ከፍ ለማለት የሚያደርገው ምኞት በምኞት ዓለም ላይ ብቻ እንደሚቀር ያየዋል:: ንዑስ ከበርቴው ባንዱ በኩል ከፍ ለማለት አይችልም በሌላ በኩል ወደ ላብአደርነት ዝቅ ያለእንዲሆን ሳይውን እንኳን ሸጠ ለመተዳደርና የማይችልበት ሁኔታ ይፈጠራል:: ገበሬውም የካፒታል ብዝበዛ ምን ያህል እንዳሆነ መመልከት ይጀምራል::



ገዥ መደብ ውስጥ በህብረተሰቡ ውስጥ ያለው ቅራኔ በየረድፍ በየረድፉ ይከፋፍሏቸውና ታላቅ ቅራኔ ውስጥ እርስ በርሳቸው ይገባሉ:: አንዱ የሚያደርጋቸው መሠረታዊ ጉዳይ በኖር የሥርዓቱን መደምሰስ መከላከል ከመንከተከት ማዳን ነው:: ቀውሱ ግን የኤኮኖሚክ መሠረት ያለው በመሆኑ ባንዱ በኩል ከቀውሱ ውስጥ ጠንከር የሚወጣው ትልቅ ከበርቴ በሌላ በኩል ደግሞ ሆኖ የሚገኘው የትልቅ ከበርቴ ክንፍ አለ:: ባጠቃላይ ያው በሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ውስጥ የሚገዛው የፋይናንስ ካፒታል አንደኛው ክፍል ዘንድ የበዝባዡው ውጤት ይጠራቀማል:: ከፍተኛ የኤኮኖሚ ቀውስ በህብረተሰቡ ውስጥ ያለው መሠረታዊ ቅራኔ የሚንፀባረቅበት ስለሆነ የዐርባታ ኃይሉ ዕድገት ከፍተኛ የፖለቲካ ሥርዓተ ማህበርን ለውጥ ይጠይቃል:: ይህን ግን ለማድረግ የሚችለው የወዝአደሩ መደብ ሶሺያሊዝምን መሠረተ እንደሆነ ነው:: የሚቀረው የከበርቴው ሥርዓተ ማህበር ውስጥ ኤኮኖሚው የሚጠይቀውን የካፒታል መጠራቀም በከበርቴው መንግሥት ማካሄድ ነው:: ይህ ሊሆን የሚችለው የሞኖፖሊ ከበርቴው መደብ የፖለቲካ ሥልጣን በእጁ ያላስወጣ እንደሆነ ነው::

የገዥ መደብ በተለይም በአገዛዝ ውስጥ የሚሳተፉት ፓርቲያቸና የፖለቲካ ቡድኖች የድጋፍ መሠረት በጣም ይቀንሳል:: በሥርዓቱ ውስጥ ካለው ነባራዊና ህሊናዊ ሁኔታ የመነጨ አብዮታዊ እንቅስቃሴ ይጠነክራል:: ጭቁን መደቦችና የህብረተሰብ ክፍሎች ባለው አስቃቂ ነባራዊ ሁኔታ፤ ሥራ ፈትነት መብዛት፤ የንዑስ ከበርቴው የኑሮ መቀርቀዝ ጠቅላላ የኤኮኖሚ ቀውስ የሚያስከትለው የዋጋ መጨመር ወዘተ.. በሥራቱ ላይ ይነሳሉ:: የከበርቴው ፓርላማ ትርጉም የለሽ መሆኑን ጭቁን የህብተሰብ ክፍሎች ይረዳሉ:: የከበርቴው "ዲሞክራሲያዊ" ሥርዓት ትርጉም የለሽ እንዲሆን ሰፊው ህዝብ ይረዳል:: ይህ በአጠቃላይ ሲሆን በዝርዝር እንመልከተው::

1ኛ/ የነቃው አብዮታዊ ወዝአደር ሥርዓቱን በሶሺያሊስት አብዮት ደምስሶ ከፍተኛ የፖለቲካ ሥርዐተ ማህበርን፤ ሶሺያሊዝምን ለመመሥረት ይታገላል:: የቀውሱ ምንጭ የካፒታሊስት ሥርዓተ ማህበር ውስጥ ያለው መሠረታዊ ቅራኔ እንደሆነ በመረዳት ከሞኖፖል ከበርቴው መደብ የፖለቲካ ሥልጣን ለመንጠቅ ይታገላል::

2ኛ/ ኑሮው እየቀረቀዘ የኑሮ ዋስትና እያጣ የሄደው መሃከላዊ መደብ፤ ንዑስ ከበርቴው ባጠቃላይ በሥርዓቱ ላይ እምነት ማጣትና የዚህን ለውጥ ይሻል:: የከበርቴው ሥርዓተ ማህበር እንዲደመሰስ፤ ነገር ግን በከበርቴነቱ ደግሞ የሶሺያሊዝም ፍራቻ አለው:: በትልቁና በእራሱ መሃከል ባለው ቅራኔ፤ የካፒታሊስት መሠረትባይነካ የትልቁን መወገድ ብቻ ይሻል:: ትልቁ ከበርቴ የፖለቲካ ሥልጣኑን እንደያዘ ንዑስ ከበርቴው ስለሚያውቅ፤ እየቀረቀዘ እንዳይሄድ አንዳች ዓይነት ለውጥ ይፈልጋል:: ስለዚህም በፓርላማው ላይ ጥላቻ ይኖረዋል:: ሆኖም ባጠቃላይ "ጠንካራ መንግሥት፤ የኑሮ ዋስትና የሚሰጠው" ወዘተ... ከመጠየቅ አያልፍም::

3ኛ/ በሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ውስጥ አዳዲስ የህብረሰብ ክፍሎች ፣
ረዷዎች እንደተፈጠሩ ከፍ ብለን ገልጸናል:: የመንግሥቱ ቢሮክራሲ ውስጥ ያሉ
ቢሮ ከበርቴዎች፣ ንዑስ ከበርቴዎች ሠራተኞች ወይንም በአጠቃላይ በዕርባታ
ውስጥ በቀጥታ የማይሳተፉ በአስተዳደርና በማከፋፈያ ድርጅቶች ውስጥ የሚሳተፉ
የህብረሰብ ክፍሎች፣ የኑሮ ሁኔታቸው የሚወሰነው በመንግሥቱ በሚገባ መንቀ
ሳቀስ፣ በመንግሥቱ የገንዘብ ሃይል ስለሆነ "ጠንካራ መንግሥት" ለኑሮአቸው
ዋስትና የሚሰጣቸው ይፈልጋሉ::

4ኛ/ በከበርቴው "መንግሥት" ዕርዳታ የሚተዳደሩ ባለፋብሪካዎች
በቀውሱ ወቅት ዕርዳታው ስለሚጎደልባቸው ለውጥ ይፈልጋሉ:: የሚፈልጉትን ለውጥ
የተዛባውን ኢኮኖሚ ለመመለስ ለማቃናት ይቻላቸው ዘንድ ባንዱ በኩል አገዛዙ
የበለጠ እንዲረዳቸው በሌላ በኩል ደግሞ በተለያዩ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ዕርም
ጃዎች "መንግሥት" ከትልቁ ካፒታል እንዲከላከላቸው ይፈልጋሉ::
በዚህ ሁሉ የተነሳ፣ በሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ውስጥ፣ ፋይናንስ ካፒታል በተፈጠረው
የኢኮኖሚ የሶሺያልና የፖለቲካ ሁኔታዎች ምክንያት በከበርቴ ዲሞክራቲክ ሥር
ዓት አማካይነት ሊገዛ አይችልም:: ሥርዓቱን ሊደመስስ የሚታገል አብዮታዊ እን
ቅስቃሴ ባንዱ በኩል አለ:: በተጨማሪ ጥንት በዚሁ ሥርዓተ ማህበር ውስጥ በሥ
ልጣን እንዲቀይሏቸው የሚሹት ከነበሩት መደቦችና የህብረሰብ ክፍሎች ጋር ፋይ
ናንስ ካፒታል ከፍተኛ ቅራኔ አለው:: በራሱ በፋይናንስ ካፒታል ውስጥ በገዥው
መደብ ውስጥ ከፍተኛ ቅራኔ አለ:: ለአገዛዙ ፍጹም የጥንት መሠረቱን አጥቷል::
በዚህ ሁኔታ በከበርቴው ዲሞክራሲ ውስጥ የሚሠራው የአገዛዝ መካኒክ ከጥቅም
ውጭ ይሆናል::

በ"ህግ አስፈጻሚና" በ"ህግ አውጭው" መካከል የነበረው ሚዛኑ
/ስምምነት/ ይዛባል:: ያለው ሁኔታ የ"ህግ አስፈጻሚውን" ሚና ከፍ ያደ
ርገዋል:: ሥርዓቱን በፋይናንስ ካፒታል አገዛዝ ሥር ለማቆየት እንዲቻል፣
ፋይናንስ ካፒታል በቴረር መገዛትን ይመርጣል፣ ጥንት የነበረውን መለካዊ የከ
በርቴ ዲሞክራሲ ማጥፋትና የፋይናንስ ካፒታል ግልጽ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ማስ
ፈር አለበት::

ፋይናንስ ካፒታል አገዛዙን ሊያድነው የሚችለው ፋሽስታዊ እንቅስቃሴ
ብቻ እንደሆነ በመረዳት ከፈሰያው የአስቶበር ሶሺያሊስት አብዮት አንስቶ በየ
በታው መንሰራራት ላይ ያለውን ፋሽስታዊ እንቅስቃሴ አቅፍ ደገፍ አቋቁሟል::

ፋሽስታዊ እንቅስቃሴው የከበርቴው አገዛዝ ካለበት ሁኔታ ለመውጣት
የሚያስፈልጉትን ሁሉ ያሟላል::



1ኛ/ ትላልቅ የከበርቴ የፖለቲካ ሃይሎች ያጡትን ህዝባዊ መሠ
ረት ፋሽስታዊው እንቅስቃሴ ሊያገኝ ችሏል:: በዕርባታ ውስጥ በቀጥታ የማ
ይሳተፉት የህብረሰብ ክፍሎችን በአስተዳደርና በማከፋፈያ የሚሳተፉት፣ በዕ
ርባታ ውስጥ ጥገኛ ሚና የሚጫወቱትን ቴክኒካዊ ምሁር ኑሮው እየቀረቀዘ
የሄደው ንዑስ ከበርቴ ውስጥ መሠረት አገኝቷል::

2ኛ/ የካፒታሊስት የኢኮኖሚ መሠረትን የማይጻረር እንቅስቃሴ
ነው::

3ኛ/ የወዛአደር እንቅስቃሴን ለመደምሰስ የተጠነሰሰና ፋጹም የሚ
ጻረረው በፋይናንስ ካፒታል ዕርዳታ ሊያድግ የቻለ እንቅስቃሴ ነው::

4ኛ/ የፋሽስት እንቅስቃሴ በከበርቴ የፖርላማ ሥርዓት ላይ በማመጽ
የተገነባ ነው:: ስለዚህ ለከበርቴው የሚያስፈልገውን ጊዜአዊ ሁኔታዎች በሙሉ
ያሟላል::

በከበርቴ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ሊገዛ ያልቻለው ትልቁ ከበርቴ፣
አገዛዙን ለማቆየት በከበርቴ ዲሞክራሲ ላይ የተመሠረተን የከበርቴ መንግሥት
በፋሽስታዊው ይተካዋል::

ለማጠቃለል፣ በከበርቴው ዲሞክራሲ ላይ የተመሠረተው መንግሥት ዓይ
ነት፣ ወሳኝ ቀውስ ውስጥ ሲገባና በጠቅላላው በህብረሰቡ ውስጥ ባሉት ጭቁን
መደቦችና የህብረሰብ ክፍሎች ጥያቄ ውስጥ ሲገባ፣ ሁሉም በመንግሥቱ ላይ ያም
ጹሉ፣ በሶሺያሊስት አብዮት ወዛአደሩ ሥርዓቱን ለመቀየር ሳይችል ሲቀር፣ ፋይ
ናንስ ካፒታል ፋሽስታዊ የከበርቴው አገዛዝ ዓይነትን ይመሠርታል:: የከበርቴው
ዲሞክራሲን ደምስሶ ፋሽዝም በቦታው ይተካል:: ትልቁ ከበርቴ በተለይ በቀጥታ
በቀውሱ የተነሳ የመንግሥት ሚና በኢኮኖሚው ውስጥ የበለጠ ከፍ እንዲልና የሞ
ኖፖሊ አገዛዝ እውነተኛ ገጹን እንዲያገኝ የሚጥረው፣ ፋሽዝም ሃይል ላይ ሲወጣ፣
አውሃሪው የፋይናንስ ካፒታል ክፍል አመራሩን በእጁ ያስገባል::

4./ የፋሺዝም የመደብ ይዘትና "ሕዝባዊ መሠረት"

ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ውስጥ ስላለው መሠረታዊ ቅራኔ ፣ ስለ ካፒታል
እንቅስቃሴና በአጠቃላይ ያለው ቅራኔ እንዴት የግድ በሶሺያሊስት አብዮት መፈታት
እንዳለበት አይተናል::ስለ ፋሺዝም የመደብ ይዘት ለመረዳት በዚህ ስርአት ውስጥ
ስላለው መሠረታዊ ቅራኔ መረዳት አስፈላጊ ነው::ይህን ካየን ዘንድ ፋይናንስ
ካፒታል በሚገዛበት ሥርዓት፣ፋሺዝም ሃይል ሲጠነክር ወይንም ሃይል ከመጨበጡ በፊ
ትም ቢሆን የአንድ ፋሺስታዊ እንቅስቃሴ የመደብ ይዘት በአጠቃላይ ትልቁ ከበርቴ

እንደሆነ ከዚያም ደግሞ አልፎ ጠለቅ ለማለት ሲፈለግ የፋይናንስ ካፒታል አንደ
ኛው ክፍል እንደሆነ መረዳት አያስቸግርም።

እዚህ ላይ ከመጀመሪያው መለየት ያለበት አንዱ ጉዳይ የመደብ ይዘት
ሲባል ፣ አንዱ እንቅስቃሴን የሚደግፉ የመደብ ረድፎችና የህብረተሰብ ክፍሎች
ምን ምን እንደሆኑ ማሳየት ፍጹም እንዳልሆነ ነው።ስለዚህም በፋሺስታዊ እንቅ
ስቃሴ የመደብ ይዘትና "ህዝባዊ መሠረት"/ቤዝስ/ ትልቅ ልዩነት ማድረግ ያስ
ፈልጋል።የመደብ ይዘት ሲባል አንድ እንቅስቃሴ የፖለቲካ ስልጣን ዕጅ ያስገባ
የየትኛውን የመደብ ጥቅም የሚጠብቅ፣መንግሥቱ የየትኛው መደብ እንደሚሆን ማወቅ
ነው።በፋሺታዊ ሥርዓት ደግሞ በአጠቃላይ የከበርቴው መደብ አገዛዝ ነው ማለትም
ብቻ በቂ ስላልሆነ የየትኛው ክፍል እንደሆነ ማወቅ ያስፈልጋል።

በካፒታሊስት ሃገሮች ፣ ምንም እንኳን በእያንዳንዱ ታሪካዊ የበሻለ
የኢኮኖሚና የፖለቲካ እድገት የተለያየ ቢሆንም ፣ ፋሺስታዊ እንቅስቃሴዎች መለከ
በያዘ መንገድ መንሰራራት የጀመረት ታላቅ የአክቶበር ሶሻሊስት አብዮት በሩሲያ
ከተደረገ በኋላና ላብ አደሩ የፖለቲካ ስልጣን ከጨበጠ ወዲህ ነው። የአክቶበር
አብዮት በዓለም ሕዝቦች ታሪክ ውስጥ ታላቅ ምዕራፍና ዓለምንም የሶሻሊስት ዘመን
/ኤራ/ ውስጥ እንዳስገባት የታወቀ ነው።በካፒታሊስት ሃገሮች ውስጥ ላብ አደሩ
ከፍተኛ ተጋድሎ በሚያደርግበት ፣የላብ አደሩ አብዮታዊ እንቅስቃሴ በተፋፋመበት
ወቅት ይህን አብዮታዊ እንቅስቃሴ ለማገድና የታሪክን እርምጃ ወደኋላ ለመመለስ
ከበርቴው የሚያደርገው ጥረት ፣ የፋሺስታዊ እንቅስቃሴ እንዲሰራራ ማድረግ አንደ
ኛው ክፍል ነው።ይህን ለማወቅ የፋሺስታዊ እንቅስቃሴዎች እድገት በጣልያን ሆነ
በጀርመን እንዴት እንደጀመረ፣በማን እንዲያድጉ፣እንዲለመልሙ እንደተደረገ ወዘተ፣
ታሪካዊ ተጨባጭ ጥናቶችን ማድረግ ይጠቀማል።ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ሥርዓትን ከመን
ኮታኮት ለማዳን በማደግ ላይ ያለውን የወዝ አደር እንቅስቃሴ ለመግታት የተነሳሳ
እንደሆነ ለመለየት የሚያስችሉ ታሪካዊ ተጨባጭ ዶኩሜንቶች አሉ።

የፋሺዝምን የመደብ ይዘት ለመረዳት የሚያስቸግር ነገር ቢኖር እርግጥ
መንሰራራት ላይ በነበረበት ጊዜና ገና የፖለቲካ ሥልጣን ባልጨበጠበት ወቅት፣
1ኛ/ የፋሺስታዊ እንቅስቃሴዎች ደጋፊዎች — ህዝባዊ መሠረቱ ከዝቅተኛ የህብረ
ሰብ ክፍሎች መሆኑ፣
2ኛ/ የእንቅስቃሴው "ርዕዮተዓለም" ብሎ የሚቀርበው አጠቃላይ ዲማጎጂ የተ
መላበት መለካዊ "ፀረ ካፒታሊስት"ና "ፀረ ገዥ መደብ" ይዘቱ ወዘተ፣
3ኛ/ በከበርቴው ዲሞክራሲ ላይ የተመሠረተውን የመንግሥት አይነት 'ለማጥፋት'
የሚታገል መምሰሉ ናቸው።
በዚህም የተነሳ የፋሺዝምን ምንነት ፣ የመደብ ይዘቱን በመረዳት በኩል ብዙ ስህ
ተቶችና ግምቶች ተሰጥተው ነበር።በተለይም በሶሺያል ዲሞክራቶች ምሁራን ወዘተ፣
ፋሺዝም ፀረ ፋይናንስ ካፒታል ወይንም በአጠቃላይ ፀረ ሞኖፖሊ ካፒታል የሆነ
የንዑስ ከበርቴ አገዛዝ ነው የሚሉና የመሳሰሉ ግምቶች ተሰጥተው ነበር።



ትክክለኛው የፋሺዝምን የመደብ ጠባይ ይዘት ለመረዳትና ምንነቱን ለመ
ግለጽ የቻለው ግን 7ኛው የኮምኒስት ኢንተርናሽናል የዓለም ጉባዔ ነው።ፋሺስ
ታዊ እንቅስቃሴ በተንሰራሩ ቦታዎች ሆነ ሃይል በጨበጡባቸው ሃገሮች ላብ አደሩ
ባደረገው ትግልና ከአገኘው ትምህርት ፣ በዲያሌክቲካዊና ታሪካዊ ማቴሪያሊዝም
ላይ በመመስረት ትልቅ ጥናት ከተደረገ በኋላ ጆርጅ ዲሚትሮቭ ስለፋሺዝም ምንን
ነት የሰጠው ትርጉም መሠረታዊና ትክክለኛ ነው።

**" Fascism is not a form of state power 'standing above both classes - the proletariat and the bourgeoisie,'...Fascism is the power of finance capital itself."**

**(The United Front - Proletarian P. p11)**

"ፋሺዝም በግልጽ ቴሮሪስቲክ የሆነው፣ከሁሉም በላይ አድሃሪ የሆነ፣
እምባገነንና ከሁሉም በላይ ኢምፔሪያሊስት የሆነው የፋይናንስ ካፒታል አንደኛው
ክፍል አገዛዝ ነው" የመደብ ይዘቱ ይህ ነው።

ከላይ እንዳየነው እዚህ ትክክለኛ የመደብ ይዘቱ ላይ 7ኛው የኮምኒስት
ኢንተርናሽናል የዓለም ጉባዔ የደረሰው ባለፉት ዓመታት በተለይም ከ6ኛው ኢንተ
ርናሽናል ጉባዔ በኋላና በዚህ መካከል ከተካሄደው የከረረ የመደብ ትግል የተገ
ኘውን ትምህርት በመውሰድና ከዚያም በጀርመን ፋሺዝም ሃይል ከመጨበጥ በኋላ
ምንነቱን ከምን ጊዜም የበለጠ ለመረዳት ስለተቻለ ነው።ፋሺዝም፣ ሞኖፖሊ ካፒ
ታሊዝም ደረጃ በደረሰችው ጀርመን ውስጥ ሃይል መጨበጡ የፋሺዝምን የመደብ ይዘት
የበለጠ ለመረዳት አስችሏል።ከፍተኛ የኢኮኖሚ መዋቅር ላይ የደረሰችው ጀርመን
ውስጥ ፋሺዝም ሃይል ላይ መውጣቱ ፣ በሌሎች ቦታዎች የሞኖፖሉ ካፒታል አገዛዝ
በሰፈነባቸው ነገር ግን በአጠቃላይ ሲታይ ወደ ኋላ በቀሩ ሃገሮች ውስጥም የፋ
ሺዝም እንቅስቃሴ አንቀሳቃሹና መሪ ማን እንደሆነ ለመረዳት አስችሏል።

በ1928 የ6ኛ ኮምኒስት ኢንተርናሽናል ጉባዔ ስለፋሺዝም ምንነት ት
ክክለኛውን አቋሟ፣እንዴት ከኢምፔሪያሊዝም ጋር እንደተያያዘ ለማሳየት ቢችልም
ምንነቱን የበለጠ በትክክል ለማስረዳትና ሙሉ በሙሉ መልስ ያገኘው በ7ኛው
ጉባዔ ላይ በተደረገው ምርምር ነው።በተለይም ፋሺስታዊ መንግሥት ምን አይነት
የከበርቴ መንግሥት እንደሆነ?በከበርቴ ዲሞክራሲ ላይ ከተመሠረተ የከበርቴ አገ
ዛዝ በምን እንደሚለይ!ከዚያም ከፋይናንስ ካፒታል ውስጥ የትኛው የፖለቲካ ስል
ጣን በእጁ እንደሚያስገባና ቴሮሪስት የሆነ አገዛዝ እነደሚመሰርት ? ወዘተ።
ስለ ፋሺዝም ፣ በ1928 የተላለፈው የኮሙኒስት ኢንተርናሽናል ፕሮግ
ራም የሚከተለውን ይዟል ነበር።

**"Under certain special historical conditions the progress of the bourgeois,imperialist, reactionary offensive assumes the form of**

**Fascism. These conditions are: instability of capitalist relationships; the existence of considerable declassed social elements, the pauperisation of broad strata of the urban petit-bourgeoisie and of the intelligentsia; discontent ... In periods of acute crisis for the bourgeoisie, Fascism resorts to anti-capitalist phraseology, but, after it has established itself at the helm of state, it casts aside its anti-capitalist rattle, and discloses itself as a terrorist dictatorship of big capital."**

**(Fascism and Social Revolution - Palme Dutt Proletarian Publishers p.108)**
/ሥርዝ የተጨመረ/

በመሠረቱ የፋሺዝም አጠቃላይ ትክክለኛ ትርጓሜ የመደብ ይዘቱን 6ኛው የኮምኒስት ኢንተርናሽናል ጉባዔ በሚገባ አሳይቷል፡፡በ6ኛና በ7ኛ ኢንተርናሽናል መካከል ባለው ጊዜ ከነበረው ትግል ውስጥ የተገኘው ትምህርትና ምርምር ግን የበለጠ የመደብ ይዘቱን ለመረዳት አስችሏል፡፡

የፋሺዝም የመደብ ይዘት በአጠቃላይ ብቻ ከሞኖፖሊ ካፒታሊዝም የሚመጣ አደጋ መሆኑን መግለጽ በቂ እንዳልሆነ ሊደረስበት የተቻለው በ7ኛው ኢንተርናሽናል ዐለም ጉባዔ ላይ ነው፡፡በሞኖፖሊ ካፒታሊስት መደብ ውስጥ ቀራኙ እንደሚኖር አንደኛው ክፍል በሌላው አይነት አገዛዝ ለመቀጠል እንደሚፈልግ ሌላው ግን ፋሺስታዊ የአገዛዝ አይነት ለመመሥረት እንደሚፈልግ ማወቅ ይሻል፡፡ስለዚህም ነው ከብዙ ሳይንሳዊ ምርምር በኋላ "ፋሺዝም በመጨረሻ አድሃሪው አምባገነንና ኢምፔሪያሊስት የሆነው የፋይናንስ ካፒታል አንደኛው ክፍል አገዛዝ" መሆኑን የ7ኛው ኢንተርናሽናል ዓለም ጉባዔ የደረሰበት፡፡ስለፋሺዝም የመደብ ይዘት ምርምር ሲደረግ ስለፋሺስታዊ መንግሥት ምንነትም ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ፋሺዝም — የመጨረሻ አድሃሪው የፋይናንስ ካፒታል አገዛዝ — በከበርቴ ዲሞክራሲ ውስጥ ካለው የፋይናንስ ካፒታል መንግሥት ጋር ያለውን ልዩነትም በትክክል ያስቀመጠው የ7ኛው ኢንተርናሽናል ኮንግሬስ ነው፡፡ የፋሺስታዊ መንግሥትን ትክክለኛ ምንነት መረዳት ፋሺዝም በሰፈነበት ሥርዓት ውስጥ ለሚደረገው የመደብ ትግል ፣ አንድ ተራማጅ ሃይል በአጠቃላይ በተለይ ደግሞ የወዝ አደሩ መደብ መከተል ያለበትን ታክቲክና ስትራቴጂ ስለሚያሳይ ፣ የ7ኛው ኢንተርናሽናል ጉባዔ የፋሺዝም መንግሥት ከኢምፔሪያሊዝም ጋር ያለውን ግንኙነት ከማሳየት አልፎ ታሪካዊ ቦታውንም አስቀምጧል፡፡

ጆርጅ ዲሚትሮፍ **" The accession to power of fascism is not an ordinary succession of one bourgeois government by another, but a substitution of one state form of class domination of the bourgeoisie - bourgeois democracy - by another form - open terrorist dictatorship."** (p.12) ይላል፡፡



በከበርቴ ዲሞክራሲ ላይ የተመሠረተ የከበርቴ የመንግሥት ዓይነትና ፋሺስታዊ የመንግሥት ዓይነት ልዩነት እንዳላቸው የሚያብራራ ነው፡፡ፋሺዝም የመጨረሻው አድሃሪ የፋይናንስ ካፒታል ግልጽ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ነው፡፡ከከበርቴ የዲሞክራሲ አገዛዝ ይለያል፡፡ፋሺዝም በደፈናው የሞኖፖሊ ካፒታል አገዛዝ ነው ማለት አይበቃም ፣ ፋሺስታዊ አገዛዝ ከማንኛውም አድሃሪ መንግሥት ጋር ማማታት ትልቅ ስህተት ነው፡፡

መሠረታዊ ነገር ስለ ፋሺዝም ፣ከኢምፔሪያሊዝም ጋር ያለው ግንኙነት— አንድ ኢምፔሪያሊስት አገር ውስጥ የሞኖፖሊ ካፒታል ትልቅ የኢኮኖሚ ቀውስ ውስጥ ሲገባ የፋይናንስ ካፒታል አንደኛው ክፍል የሚመሠርተው የከበርቴው ግልጽ ፈላጭ ቆራጭ የከበርቴ መንግሥት አይነት መሆኑ ነው፡፡በተለያዩ አገሮች ግን ባላቸው የተለየ የኢኮኖሚ የሶሻልና ብሔራዊ መዋቅር /ስትራክቸር/ አንዳንድ ልዩ መልክ ሊይዝ ይችላል፡፡መሠረታዊውን ነገር ግን ሊቀይረው አይችልም፡፡

**"Fascism may be in fact a reactionary dictatorship. But not every reactionary dictatorship is Fascism... The specific character of Fascism can only be defined by laying bare its class basis, the system of class-relations within which it develops and functions, and the class role which it performs. Only so can Fascism be seen in its concrete reality, corresponding to a given historical stage of capitalist development and decay." (Palme Dutt - p.96)**

የፋሺዝም የመደብ ይዘት ፋይናንስ ካፒታል እንደሆነ አይተናል፡፡

<u>የፋሺዝም "ሕዝባዊ መሠረት"</u>

የፋሺዝም የመደብ ይዘትንና ሕዝባዊ መሠረቱን ማማታት ፣ የመደብ ይዘቱን አለመረዳት ከዚያም የፋሺዝም ሥርዓት ምንነት ላይ ስህተተኛ አቋም ያስደርሳል ብለናል፡፡ የፋሺዝም ሕዝባዊ መሠረት /በአንዳንድ ቦታዎች የተለያዩ ሊሆን ይችላል/ በአጠቃላይ አንድ የካፒታሊስት ህብረሰብ ውስጥ "ዲክላሰድ" (declassed) የሆኑ የህብረሰብ ክፍሎችን ግለሰቦችን በሙሉ ያጠቃልላል፡፡ ዋናው መሠረት ግን በካፒታሊዝም ቀውስ ኑሮው እየቀረቀዘ የሄደው ንዑስ ከበርቴው ነው፡፡በአጠቃላይ ፣ ወደኋላ ከቀረው ካልነቃው ወዝ አደር አንስቶ በካፒታሊዝም ቀውስ የተመታው ፣ የኑሮ ዋስትና ያጣው ንዑስ ከበርቴ ፣ ሥራ አጡ ፣ ሥራ ፈቱ ከዚያም

ቀጥታ የመንግሥት አስተዳደርና ማከፋፈያ ተግባር ውስጥ የሚሳተፈውን ሁሉ ያጠቃልላል::

ፋሺስታዊ እንቅስቃሴዎች በየቦታው ከመጀመሪያውም እንዲፈለፈሉ የተደረጉት ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ከፍተኛ ቀውስ ውስጥ እየገባ በሄደበት ወቅትና ሞኖፖሊ ካፒታሊስት ተላላቅ የፖለቲካ ቡድኖች በሕዝቡ ዘንድ ተቀባይነት እያጡ ሲሄዱና የወዝ አደሩ እንቅስቃሴ እየጠነከረ በሄደበት ወቅት ነው::በተለይም ደግሞ ከታላቁ የሩሲያ የሶሺያሊስት አብዮት በኋላ የአብዮቱ ንፋስ ጠቅላላ የካፒታሊስት ዓለምን ሲያናወጠ ፣ በፋሺስታዊ እንቅስቃሴ አማካይነት የወዝ አደሩን እንቅስቃሴ ለመቋቋም የተደረገ ነው::ማንኛውም ፋሺስታዊ እንቅስቃሴ በነፃ በራሱ በግንፈሉ የወጣ እንቅስቃሴ አይደለም /ለምሳሌ ስለ ጀርመን ፋሺዝም መጠንሰስ ታሪካዊ ምንጭ በሰፊው እንመጣበታለን/::

ፋሺስታዊ እንቅስቃሴዎች የፖለቲካ ስልጣን ከመጨበጣቸው በፊት በቀላሉ ሕዝባዊ መሠረት ሊያገኙ የቻሉት ፣ በሞኖፖሊ ካፒታሊዝም እድገት ውስጥ የተፈጠረት ፣ በተለይም በመንግሥቱ በሚገባ መንቀሳቀስ ላይ የኑሮ ሁኔታቸው የተወሰነው ክፍሎች ውስጥ ነው::

ሀ/ በዕርባታ ውስጥ በቀጥታ የማይሳተፈው የማከፋፈያ የማስተዳደሪያ አፓራተስ ውስጥ የሚሰራው የህብረሰብ ክፍል ውስጥ ፣

ለ/ ኢንዱስትሪ ውስጥ የተፈጠረት አዳዲስ የህብረሰብ ክፍሎች ፣ ቴክኒካዊ ኢንተሊጀንሲያ ፣ ተቀጣሪ የቢሮ ሠራተኞች ወዘተ ፣

ሐ/በካፒታሊዝም ውስጥ ምንጊዜም የሚኖረው በዕርባታ ውስጥ ፍጹም የማይሳተፈው የተወሰነ ሥራ አጥ ክፍል ናቸው::

ከዚያም ፣

ሀ/ በካፒታሊዝም ቀውስ የተነሳ ወደ ወዝአደርነት ለመቀየር ያሰቻሉት /በሥራ አጠት/ እየቀረቀዙ የሄዱት ትናንሽ ባለሃብቶችና ጠቅላላ ሥራ ፈት የሆኑት ውስጥ፣

ለ/ ያው በከበርቴው ውስጥ የፋይናንስ ካፒታል አንደኛው ክፍል በተለይም "እየከሰረ" የሄደውና ለመንቀሳቀስ ፣ ለማደግ ኢምፔሪያሊስት ዘረፋውን ለማስፋፋት የግድ "ከመንግሥቱ እርዳታ" ያስፈለገው ክፍል ናቸው::

በተጨማሪ ከራሱ ከወዝአደሩ ውስጥ ያልነቃው ክፍል በተለያዩ በሰራዊ ዲማጎጊና "ሶሰካዊ" "ፀረ ኢምፔሪያሊስት" ዘዴዎች ወደ ፋሺስታዊ እንቅስቃሴዎች ሊሳቡ ችለዋል::በተለይ በሪፎርሚስቶችና በሶሺያሊ ዴሞክራት መሪዎች አድርባይነት "ንዴት" "ክስረት" ወደፋሺስታዊ እንቅስቃሴ የሄዱ ብዙ ወዝአደሮች ነበሩ::

ፋሺዝም የፖለቲካ ስልጣን ከጨበጠ በኋላ ፣ይህ ሕዝባዊ መሠረቱ እየተሰባበረ እየተበሰጣጠረ ይሄዳል::እርግጥ በበሰራዊ "ሄስቴርያ" በዲማጎጊ ለፋሺዝም ድጋፍ የሰጡት ዝቅተኛ መደቦችና የህብረሰብ ክፍሎችን በተሰፋ ለማቀየት ይሞክራል::ሆኖም መሰበጣጠሩ አይቀርም::የፋሺስቱ ጋርቱ ደጋፊያቸዎ ሆኑ አባሎች



ከዚያም አጠቃላይ ሕዝባዊ መሠረቱ እየተቀየረ ይሄዳል::ይበልጡን የቢሮ ከበርቴው ላይና የኑሮአቸው ሁኔታ ከመንግሥቱ ጋር የተያያዘው ፣ አስተዳደርና ማከፋፈያ ተግባር ውስጥ የሚሳተፈት ፣ የጦር ሃይሉ ከዚያም ቀጥር ቡዘኒያች ይሆናሉ:: ቢሮክራሲውና የፋሺስቱ ጋርቱ በፋሺስቱ መንግሥት ስር ሙሉ አንድነት እንዲያገኙ ከተደረጉ በኋላ የዚህ መንግሥት አሻንጉሊት "ሕዝባዊ" ድርጅቶች በመመሥረቱ መቀያውን ለማራዘምና ሕዝባዊ መሠረቱን ለማቀየት ጥረት ይደረጋል::እንግዲህ የፋሺዝም የመደብ ይዘትን መረዳት በመሠረቱ ሁለት ዋና ዋና ጉዳዮችን ያጠቃልላል::

1ኛ/ የፋሺዝም ሕዝባዊ መሠረትን ከመደብ ይዘቱ ጋር አለማደበለቅ::የመደብ ይዘቱ ላይ ለመድረስ የተናውን መደብ እንደሚያገለገል መርምሮ ፋሺዝም ከሁሉም በላይ አድሃሪ ፣ አምባገነንና ኢምፔሪያሊስት የሆነው የፋይናንስ ካፒታል አገዛዝ እንደሆነ ማወቅ::

2ኛ/ ፋሺዝም በአጠቃላይና በደፈናው የሞኖፖል ካፒታል አገዛዝ ብቻ መሆኑን ማወቅ በቂ አይደለም::የፋሺዝም ሥርዓት በከበርቴ ዲሞክራሲ ላይ የተመሠረተ የከበርቴ የመንግሥት አይነትን —በከፍተኛ ቀውስ ውስጥ— የሚተካ አዲስ የከበርቴ መንግሥት ዓይነት መሆኑን፣ፋይናንስ ካፒታል በቴሮር የሚገዛበት ግልጽ አምባገነንነት—ፈለጥ ቀራጭነት የሚነግሥበት የከበርቴ የመንግሥት ዓየነት እንደሆነ መረዳት ያስፈልጋል::

ስለ ፋሺዝም ያለንን እውቀት ሙሉ የሚያደርገው መሠረታዊ ጉዳይ ግን — በጽሑፋችን የመጀመሪያ ክፍል ውስጥ ለማሳየት የሞከርነው — ፋሺዝም ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ውስጥ ካለው መሠረታዊ ቅራኔ የወጣ መሆኑን መረዳት ነው::ለዚህ ፣ የ"ዝመናዊ" ካፒታሊዝምና የፋሺዝም የጋራ ጠባዮች የሆኑትን ዋና ዋና ፍሬ ነገሮች ፓልመ ዱት ይዘረዝራል፣ ( p.92 )

"1./The basic aim of the maintenance of capitalism in the face of the revolution which the advance of productive technique and of class antagonisms threatens.

2./The consequent intensification of the capitalist dictatorship.

3./The limitation and repression of the independent working-class movement,and builing up of a system of organised class-co-operation.

4./The revolt against,and increasing supersession of,parliamentary democracy.

5./The extending State monopolist organisation of industry and finance.

6./The closer concentration of each imperialist bloc into a single economic-political unit.

7./The advance to war as the necessity accompaniment of the increasing imperialist antagonisms."

እነዚህ 7 ጠባዮች በጠቅላላው በመበስበስ ላይ ባለው የካፒታሊዝም ሥርዓት ውስጥ ይታያሉ:: "In this wider sens it is possible to speak of the development towards Fascism of all modern capitalist states." (Palme Dutt p.93) እነዚህን 7 አጠቃላይ ጠባዮች የሚያሟሉ ሁሉ ግን የፋሽዝም ሥርዓት ሰፈነባቸው አያሰኝም::ሞኖፖሊካፒታሊዝም ውስጥ ያለው መሠረታዊ ቅራኔ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ሲደርስ፣ ጠቅላላው ህብረሰብ የኢኮኖሚ የሶሻልና የፖለቲካ ቀውስ ውስጥ ሲገባ ፋይናንስ ካፒታል በፕንቱ የከበርቴ ዲሞክራሲ አገዛዝ መቀጠል አቅቶት፣ የፋይናንስ ካፒታል አደገኛው ክፍል በግልጽ ቴሮር የሚገዛበት ፋሺስታዊ የከበርቴ የመንግሥት ዓይነት ሲመሠርት ፋሺስታዊ ሥርዓት ይባላል::ይህ ነው የ7ኛው ኢንተርናሽናል ታላቅ ሳይንሳዊ ምርምር ውጤት::

——— xxx ———

በዚህ ጽሑፋችን ክፍል መጨረሻ፣ 1/ፋሽዝም ስመሠረተ — ሃይል ላይ ሲወጣ — እድሚውን ለማራዘም የመንግሥቱን ቢሮክራሲ እንዴት እንደሚያገለግልና 2/ ከኢምፔሪያሊዝም ጋር ያለውን ግንኙነት /ቀደም ብለን ያላነሳነውን/ ባጭር ባጭሩ ጠቅሰን እናበቃለን::

1. ፋሺስታዊ መንግሥትን እንደ አንድ የከበርቴ ታሪካዊ አገዛዝ ዓይነት መመልከት እንደሚያስፈልግ አይተናል::ፋሺስታዊ መንግሥት ከማንኛውም የፋይናንስ ከበርቴ መንግሥት ጋር አንድ የሚያደርገው አጠቃላይ የመደብ ይዘቱ ሲሆን፣በመለከ የሚለየው ደግሞ ግልጽ በሆነ ጭፍጨፋ የሚገዛ አንደኛው የፋይናንስ ካፒታል ክፍል አገዛዙን በሃይል ብቻ በፈላጭ ቆራጭነት ማካሄዱ ነው::ይህን አገዛዙን የሚያካሄደው በመንግሥቱ ቢሮክራሲና በአንድ የፋሺስት ፓርቲ የአሠራር መካኒክ ሙሉ በሙሉ አንድነት በመፍጠር ነው::የመንግሥቱ የፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ እንዲሠምርና የመንግሥቱን መሣሪያ ሙሉ በሙሉ በርሱ ትዕዛዝ ውስጥ ለማድረግ የመንግሥቱንና የፓርቲውን ቢሮክራሲ ሙሉ አንድነት ይፈጥራል::ቢሮክራሲውን ከህብረሰቡ ይገነጥለዋል:: የመንግሥቱን የአገዛዝ መሣሪያ — ያለ ችግር ይገለገልበት ዘንድ — በማደስ "ፌውዳል ሄራርኪ" መሰል የያዘ ማህከላዊነትን ያጎበራል::

2. ፋሽዝምና ኢምፔሪያሊዝም በቅርብ የተያያዙ ለመሆናቸው ምንም ማብራሪያ አያስፈልገውም::በሰፊው እስካሁን አይተነዋል:: የማንኛውም ኢምፔሪያሊስት ሃገር ዋና ዓላማ ካፒታል ወደውጭ በመላክ ህዝቦችን መዝረፍና መበዝበዝ ነው::ኢምፔሪያሊስቶች ለብዝበዛቸው ዓለምን ተከፋፍለውታል::በዚህ ክፍፍልም በውስጣቸው ብዙ ቅራኔና ከዚያም ጦርነቶች እንደተከተሉ የታወቀ ነው::በተለይ ግን ፋሽዝም ዘረፋውን ለማካሄድ ከሁሉም የበለጠ እንዳበደቸ ውሻ ይሯሯጣል::ፋሽዝምን ከሁሉ የበለጠ ጠብ ፈላጊ /አግሬሲቭ/ የሚያደርገው፣ዓለምን ለብዝበዛ ኢምፔሪያሊስቶች ሲከፋፈሉ "ድርሻዬ አነስ" በማለት ሌላ የዓለም መከፋፈል እንዲኖር ባለው ፍላ



ጎት ነው::ፋሽዝም የሰፈነባቸው ሃገሮች በዛውን ጊዜ በዘረፋው ድርሻቸው "አነስተኛ" የሆነው ነበር::ይህ አንዱ አመለካከት ሲሆን ሌላው ደግሞ እነዚህ በዘረፋው ላይ "ትንሽ" ድርሻ የነበራቸው ሃገሮች የካፒታል አገዛዛቸው ከፍተኛ ቀውስ ውስጥ ሲገባና ካፒታል እርሱን ለማራባት በፈለገው አቅጣጫ እንደልብ ሊስፋፋ አለመቻሉ እንቅፋት ስለሆነበት ነው::ስለዚህም በሥርዓቱ ውስጥ ያለው የፖለቲካ የኢኮኖሚና የሶሻል ቀውስ እየጠነከረ ሲሄድ፣ ፋሽዝም ከዚህ ለመውጣት አዲስ የብዝበዛ ክፍፍል እንዲደረግለት ወዛት፣ ከሁሉም የበለጠ የጦርነት ቀስቃሽ፣ ጠብ ፈላጊ ነበር::የ7ኛው ኢንተርናሽናል ጉባዔ ውሳኔ "ፋሽዝም የአዲስ ኢምፔሪያሊስት ጦርነት ዐነኛው ቀስቃሽ ነው" ያለው በዚህ የተነሳ ነው::

——— xxx ———

<u>ማጠቃለያ</u>

1. የፋሺስታዊ ሥርዓት መመሥረት ምንጭ በሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ውስጥ ያለው መሠረታዊ ቅራኔ — በዐርባታ ህብረሰባዊ ጠባይና በአርባታ ውጤት ግላዊ ስበሳቢነት፣ ተጠቃሚነት መሃከል — መፈንዳት ነው::

2. ላብ አደሩ ይህን መሠረታዊ ቅራኔ በሶሺያሊስት አብዮት አማካይነት የዐርባታ መሣሪያዎችን የህብረሰቡ በማድረግ ከፍተኛ የአርባታ ግንኙነት ለመመሥረት ሳይሳካለት ሲቀር፣ ፋይናንስ ካፒታል ካለበት ቀውስ ለጊዜው ለመውጣትና ሥርዓቱን ለማዳን የሚመሠርተው አገዛዝ ፋሺዝም ነው::

3. በሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ውስጥ እንደፕንቱ በከበርቴው ዲሞክራሲ የመንግሥት ዓይነት ከበርቴው መግዛት ሲያቅተው፣ የፋይናንስ ካፒታል አንደኛው ክፍል — ከሁሉም በላይ አድሃሪ፣ ኢምፔሪያሊስትና ሸቪኒስት የሆነው — የሚዘረጋው ፈላጭ ቆራጭ የመንግሥት አይነት ፋሺስታዊ ነው::

4. የፋሽዝም የመደብ ይዘት ከፋሽዝም "ሕዝባዊ መሠረት" ፍጹም የተለየ ነው:: ፋሽዝም "ከህብረሰቡ በላይ ያለ" ወይንም "የንዑስ ከበርቴ አገዛዝ" ወይንም "ከአጠቃላይ ፀረ ከበርቴና ፀረ ወዝአደር አገዛዝ" ሳይሆን የራሱ የፋይናንስ ካፒታል መንግሥት ነው::

## III - የፋሽዝም በጀርመን ድል መምታት ታሪካዊ ሥር መሠረትና ምንጩ

### መግቢያ:

በክፍል አንድና ሁለት ውስጥ ለማሳየት የሞከርነው የፋሽዝምን ምንነት በአጠቃላይ ለመርዳት እንችል ዘንድ ነው:: ይህ አጠቃላይ ትንተና የፋሽዝምን ትርጉም የማን አገዛዝ እንደሆነ እንዴትና በምን ዓይነት ሁኔታ እንደሚመጣ ያሳየናል:: በዚህ ብቻ መወሰን ግን አይበቃም በአጠቃላይና በልዩ ትንተና መካከል ያለውን የትንተና ዲያሌክቲካዊ ግንኙነት በመጠበቅ ልዩ ሁኔታ ውስጥም መግባት አስፈላጊ ነው:: ሲሆን ፋሽዝም በክላሲካል መልኩ የተመሠረተባቸው ሃገሮች ውስጥ በጣሊያንና በጀርመን ታሪካዊ አመጣጡን ቀደም ብለው የነበረትን የመደብ ትግሎች በዝርዝር መመርመር ባስፈለገ ነበር:: የፋሽዝም አደጋ ከየትና እንዴት ሊመጣ እንደሚችል ለመረዳት ያስችል ነበር:: ለዚህ ታሪካዊ ደኩማንቶቸንና ስለፋሽዝም በተለይ በዝርዝር የተረዱትን ማንበብ ይጠቀማል:: በዚህች በአጭር ጽሁፍ ውስጥ ይህን ሁሉ ለመዘርዘር አንችልም:: ሆኖም በዚህ ክፍል ውስጥ በተከበለና ገጹ ፋሽዝም የታየበት ሃገር ጀርመን ውስጥ ታሪካዊ ቅደም ሁኔታዎችን ለመዘርዘር እንፈልጋለን::

በጀርመን ውስጥ የፋሽዝም መንሰራራትና በመጨረሻም ድል የመምታት ሥረ መሠረት ምን እንደሆነ ለመረዳት ጀርመን ውስጥ የካፒታሊዝም ማደግ ከዚያም ወደ ሞኖፖል ካፒታሊስትነት እየ ተቀየረች ስትመጣ የነበረውን የመደብ ትግል ማወቅ ጠቃሚ ነው:: ፋሽስታዊ እንቅስቃሴዎች ከየት አቀጣጫ እንዴት ለምን እንደሚሠራረ ማሳየት አሁን በኢትዮጵያ ውስጥ ለምናደርገው ትግል ከፍተኛ ትርጉም ይኖረዋል::

### የጀርመን ፋሽዝም ታሪካዊ ቅደመ ሁኔታዎች፣

የጀርመን ፋሽስታዊ እንቅስቃሴ ታሪካዊ ቅደመ ሁኔታዎችን ለመመርመር ይህ ጽሁፍ ሦስት መሠረታዊ ጥያቄዎችን ለመመለስ ይሞክራል::

1ኛ/ ፋሽዝም እስከሰፈነ ድረስ በነበረው ዕድገት ውስጥ የትኞቹ የተለዩ ድርጅታዊ መደባዊና ርዕዮተዓለማዊ ንጥረ ነገሮች /ኤሌሜንትስ/ በፈላጭ ቆራጭ ዘውድ አገዛዝ /ሞናርኪ/ ጊዜ ተፈጥረው ነበር?

2ኛ/ እነዚህ ንጥረ ነገሮች በምን መልክ የጀርመን ዘውድ አገዛዝ ከተገረሰሰ በኋላ ቫይማረር / Weimar Republic / ውስጥ እራሳቸውን እንዳቀዩና ለምንስ ሊቀዩ ቻሉ?



3ኛ/ ከአንደኛ ዓለም ጦርነት በኋላ ጀርመን ውስጥ ከነበረው የኢኮኖሚ ዕድገትና ቀውስ የተነሳ እንዴት እነዚህ ንጥረ ነገሮች አዲስ መልክ ያዙ ከዚያም ፋሽስታዊ እንቅስቃሴ እንዴት አስከተሉ?

### 1. ከዘውዱ የጀርመን አገዛዝ የተዋረደ ፣ የተወረሰ ርዝራዥ፣

እስከ 1918 በጀርመን የተካሄደውን ዕድገት ዓይነተኛ የሚያደርገው በፍጥነት በተራመደው ከፍተኛ የኢኮኖሚ ዕድገትና /በተይ በኢንዱስትሪው ክፍል/ ወደኋላ በቀረ የፖለቲካ አገዛዝ ዓይነት መካከል የነበረው ቅራኔ ነው:: ማለት በጣም "የሰለጠነው" እንዱስትሪያል የሆነ አንዱ የአውሮፖ ክፍለ ሃገር በከፊል መሳፍንታዊ አገዛዝ ሥር ነበር:: ይህ ሊሆን የቻለው የፊውዳል ርዝራዦችን ሁሉ የደመሰሰ ዲሞክራቲክ አብዮት ባለመካሄዱ ወይንም ዝኅላሽቶ በተለየ መንገድ ከዘውዱ የፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ በከፊል ብቻ በመሳቀቁ ነው:: የከበርቴ ዲሞክራሲያዊ አብዮት በመሠረቱ ሳይኮላሽ ከተካሄደ ማንኛውንም በአጥንት ቀጠራ ላይ የተመሠረተ የፊውዳል ርዝራዥ ተጠቃሚነት /ፕሪቪሌጅ/ ማስወገድ ነበረበት የከበርቴው አብዮት ግን እንደፈረንሣዩ ሥር ነቀል ስላልነበር የከበርቴው ከመሳፍንቶች ጋር መስማማት አብዮትን ከወገቡ ላይ ቆርጠት ነበር:: ታሪካዊ ምክንያቶች አሉት:: የጀርመን ከበርቴን ዲሞክራሲያዊ አብዮትን ያስከደው ዋናው በወዘ አደሩ እንቅስቃሴ ላይ ያለው ፍራቻ ነው::

ውጤቱ ከፈላጭ ቆራጭ ዘውዱ አገዛዝ የተወረሰው መንግሥታዊ መዋቅር በብዛት እንዳለ መቀየቱና የተወሰነው የከበርቴ ክፍል በተለይም ከነጋዴው ጋር ስምምነት ላይ የደረሰው ከሌላው ከበርቴ ይበልጥ ለመበዝበዝ የሚያስችለው ልዩ ጥቅም /ፕሪቪሌጅ/ ማግኘቱ ነው:: የመንግሥቱን መዋቅር ከመሳፍንቶች ጋር በቁጥጥሩ ውስጥ ሊያደርግ ችሏል:: የነበረው ቅራኔ ውጤት ፋሽዝም እስከተንሰራራበት ጊዜ ድረስ በልዩ መልክም ቢሆን ታይቷል::

### ሀ. በፈላጭ ቆራጩ የዘውዱ አገዛዝ ጊዜ የነበረው የሃይል አሰላለፍ

የፈላጭ ቆራጩ የዘውዱ አገዛዝ ደጋፊ ህብረተሰባዊ ሃይሎች የፕሮይስ ዩንከር /የሰሜን ጀርመን የፊውዳል መደብ/ ተጠቃሚው የከበርቴ መደብ እንደኛው ክፍልና የከተማው ንዑስ ከበርቴ ነበሩ:: የፕሮይስ ዩንከር ከፊውዳል መደብነት ቀስ በቀስ ወደ ግማሽ ከበርቴነት በመቀየር ላይ ነበር:: ይህ የሆነው ግን በተለየ መልክ ነበር:: የፊውዳል አገዛዝ በጀርመን ውስጥ የተንኮታኮተው ፈረንሳይ እንደተካሄደው በዲሞክራቲክ አብዮት ወይንም እንደ እንግሊዝ መሳፍንቱ እራሱን ወደ ከበርቴነት ቀይሮ ከከበርቴው የላይኛው ረድፍ ጋር የኢኮኖሚ

አንድነት ፈጥሮ አልነበረም:: የጀርመን ፊውዳል መደብ የፊውዳል ጥቅሙን ከተወ በኋላ በፈላጭ ቆራጩ አገዛዝ ውስጥ የነበረውን ቢሮክራሲያዊ ጥቅሙን በመመልከት ጠቅላላ የፖለቲካ አገዛዙን በዕጁ ውስጥ እንዲያዝ በመቀየት ነው::

ይህ ሁኔታ በኢኮኖሚው ዕድገት ላይ ተጽዕኖ ነበረው:: ዩንከሩ በህብረተሰቡ ውስጥ በአደጉት የካፒታሊስት የኢኮኖሚ ግንኙነቶችና ህጎች አይተዳደርም:: እንደማናቸውም ከበርቴ በትግል ውስጥ ያደገ የህብረሰብ ክፍል ሳይሆን ቀውስ ውስጥ ሲገባ ያለውን የፖለቲካ ሃይል በመጠቀም ካለበት ችግር በአገዛዙ ዕርዳታ ወደፊት ለመራመድ ይጣጣር ነበር:: በ19ኛው ክፍለ ዘመን ላይ የነበረው የገጠር ቀውስ ጥሩ ምሳሌ ነው::

የፖለቲካው አገዛዝ ወደኋላ መቅረት ባንድ በኩል የሃገር ውስጥ ገበያ ዕድገትን ወስነው በሌላ በኩል ግን ይህ ሁኔታ የኢኮኖሚውን አጠቃላይ ዕድገት ሊያፍነው አልቻለም ምክንያቱም የዩንከሩ መንግሥት ባለው የወታደር ሃይልና ወታደራዊ አገዛዝ የዓለምን ገበያ በቁጥጥሩ ሊያደርግ ችሎ ነበር:: የሃገር ውስጥ የገበያ ዕድነት በውጭው ሊጠጣ ችሎ ነበር:: ስለዚህም ማንኛውም የፖለቲካዊ ወደኋላ መቅረት ንጥረ ነገሮች ለታዳጊው የጀርመን ከበርቴ ምንም አደጋ አልፈጠረበትም:: የዩንከሩ አገዛዝ ባለው የሚሊተሪ ሃይል የውጭ ገቢያን/ለከበርቴው/ ለማስፋት ችሎአል:: ስለሆነም የዩንከሩ አገዛዝ ከመጀመሪያውም የሚከተለው ፖለቲካ ኢምፔርያሊስት ነበር::

የከባድ ኢንዱስትሪ ከበርቴ ከመጀመሪያው አንስቶ ሙሉ በሙሉ በፈላጭ ቆራጩ ዩንከር ጉን ነበር:: ቅራኔ አልነበራቸውም:: የዚህ ዋና ምክንያት ለወታደራዊው ሃይል መሣሪያ የከባድ ኢንዱስትሪ መስፋፋት አስፈላጊ በመሆኑ ነው:: የአንድነታቸውም መሠረት የወታደራዊው ሃይል ነበር:: በዚህ ሁኔታ የከባድ ኢንዱስትሪው ከበርቴ ዕርባታውን ሊያስፋፋ ይቻላል::

በፈላጭ ቆራጩ የዘውድ አገዛዝ ውስጥ አመራሩ በትላልቅ ባለመሬቶችና /ፊውዳሉ/ በከባድ የኢንዱስትሪ ባለቤቶች ዕጅ ውስጥ ነበር:: የአንድነታቸው መሠረት የወታደራዊው ሃይል ነበር:: ሌላው የፈላጭ ቆራጩ አገዛዝ ወገን የከተማው ንዑስ ከበርቴ ነበር:: የፈላጭ ቆራጩ አገዛዝ እየቆየ በሄደ ቁጥር የሊበራል ከበርቴው ተቃውሞና ትግል በከተማው ንዑስ ከበርቴ የድጋፍ እጥረት ይከማ ነበር::



እንደሚታወቀው የንዑስከበርቴው ወገን ኢኮኖሚያዊ አንድነት ያለው ሃይል አይደለም:: በትናንሽ ሃብት ላይ የተመሠረተው ንዑስ ከበርቴ ትናንሽ ነጋዴዎች የቢሮ ሠራተኛው ወዘተ. ናቸው:: ሆኖም ታሪካዊና አንድ የተወሰነ ህብረሰባዊ ትርጉም ያለው ክፍል ነው:: እስከ በፈላጭ ቆራጩ አገዛዝ ዘመን በኋላ ለተከተለው ፖለቲካዊ ወዘተ ዕድገት በተለይ በንዑስ ከበርቴው ውስጥ የዲሞክራሲያዊነት ለምድ /ዲሞክራቲክ ትራዲሽን/መጉደል ለዲሞክራሲ መደረግ የሚገባውን ትግል ማገዱ ነበር::

ተበዝባዥ መደቦችና የህብረሰብ ክፍሎች ሰፊው ደሃ ገበሬ የወዝአደሩ መደብ ወዘተ ጀርመን ውስጥ ከተካሄደው የኢኮኖሚ ዕድገት ያገኙት አንዳችም ነገር አልነበረም:: እንዲያውም የብዙውን ቀውስ ውጤት መሸከም በእርሻ መካከል በከተማና በባላገር መካከል በተፈጠረው ቅራኔ በመጣው ቀውስ ገበሬው መሰቃየት ነበረበት:: የጀርመን ወዝ አደር እንቅስቃሴ ፍጹም ከባድ በሆነ የፖለቲካ አካባቢ ያደገ ነበር:: መሠረታዊ ሰብዓዊ መብቶች በተገፈፉበት ሁኔታ በየጊዜው በተደነገጉ እስቸኳይ አዋጆች ወዘተ ያደገ ነበር:: የፖለቲካ ድርጅቶቹ ለረጅም ጊዜ ከፍተኛ ጭቆና እየደረሰባቸው በጀርመን ውስጥ በሚካሄደው የፖለቲካ ህይወት ውስጥ ህጋዊ ሰውነት እንዳያገኙ እየተደረጉ ያደጉ ናቸው:: የወዝ አደሩ መደብ ጀርመን ውስጥ ከነበረው የኢኮኖሚ ዕድገት ያገኘው አንዳችም ነገር የለም:: በዝበዛው ከልክ ያለፈ ነበር::

ለማጠቃለል ከጦርነቱ በፊት ዘውድ አገዛዝ ውስጥ በነበረው የሃይል ክፍፍል ተስማምቶ አብሮ ይገዛ የነበረው የከበርቴው ክፍል ያለው ህዝባዊ መሠረት ፍጹም አነስተኛ ነበር:: ባንድ በኩል በጣት የሚቆጠሩ የገዢው መደቦች የመንግሥት መሣሪያውን የያዙት በሌላ በኩል ደግሞ ተበዝባዡ ሰፊው ህዝብ ነበር:: በህብረሰቡ ውስጥ ያለው ቅራኔ በጣም ጠንካራ ነበር:: ታፍኖም ተይዞ ነበር:: በሰፊው ሕዝብ ውስጥ አንድ የሆነ ብሄራዊ ንቃተ ሀሊና እንዳይኖር ካደረጉት ምክንያትም ይህ አንዱ ነው:: የመንግሥቱ መሣሪያ ጠንካራነት ባለው ጠንካራ ወታደራዊ ሃይል በየጊዜው በሚገኘው ድል ያለው ፕረስቲጅ / prestige /ና የነበረው የኢኮኖሚ ዕድገት እንዲሁም አልፎ አልፎ ይታይ የነበረት የዲሞክራሲያዊ መብቶች ጥላንጥል ዘውድ አገዛዝ ከሥሩ ፈንቅሎ ከነርዝራዡ የሚያጠፋ አብዮታዊ ዲሞክራቲክ ሃይል እንዲኖር አላደረገውም:: ዘውድ አገዛዝ ተቃዋሚ በተለይም የከበርቴው መደብ የተገኙትን የዲሞክራሲያዊ መብቶች ጥላንጥሎች ብቻ በመጠቀም ከነገስታቱ አገዛዝ ጋር አንድነት በመፍጠር ቀስበቀስ ወደ ከበርቴው የፖርላማ ሥርዓት ለመቀየር ይመኝ ነበር::

በህብረሰቡ ውስጥ ታፍኖ ቆይቶ የነበረውን ቅራኔ እንዲፈነዳና ሥርዓቱ እንዲሰባበር ምቹ ሁኔታ የፈጠረው፣ የመጀመሪያው የኢምፔሪያሊስት ጦርነት ላይ የጀርመን ድል መመታትና ያስከተለው ሁኔታ ነው።

ለ/ የመንግሥቱ መሣሪያ ሚና

የ"ጀርመን ፕሮይስ ኢምፖየር" የተገነባው በብሔራዊ አብዮት ሳይሆን በወታደራዊ ሃይል ድሎችን በማግኘትና በመስፋፋት ነበር። "መንግሥቱ የብሄራዊ ዕድገት ውጤት ሳይሆን የጀርመን ብሄር የመንግሥቱ ውጤት ነበር"። ይህም ማለት የከበርቴው መንግሥት በፊውዳሉ ሥርዓት ላይ ብሄራዊ የከበርቴ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ተካሄዶ የተገነባ አይደለም። በሰፊው ህዝብ ውስጥ የነበረው ብሄራዊ ንቃተ ሕሊና ማነስ፣ ከዚያም በሰፊው ህዝብ ውስጥ ሊኒኖየቱ ቢያንስ የቢሮክራሲው ሚና ይበልጥ እያደገ በፊውዳላዊ አሠራር የተበከለ ማህከላዊነት እየከረረ መሄዱ ነበረበት።

በዩንከሩ፣ በከበርቴውና በከተማው ንዑስ ከበርቴ መሃል የነበረው አንድነት የተመሠረተው በወታደራዊው ሃይል ነው። የከባዱ እንዱስትሪው ከበርቴ የጦር መሣሪያ ዕርባታ ውስጥ ባለው ቦታ፣ "ዩንከሩ" በጠቅላላው በመንግሥት "ማሽነሪ" /መሣሪያ/ ውስጥና በቢሮክራሲው ውስጥ ባለው ቦታ፣ ንዑስ ከበርቴው ደግሞ በቢሮክራሲው ውስጥ ወይንም በወታደርነት ከፍ ለማለት ባለው "ተስፋ" የተያያዙ ነበሩ። የዚህ ሁሉ ውጤት መንግሥቱ የወታደራዊ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ መልክ መያዙና ቢሮክራሲው በህብረሰቡ ውስጥ የተለየ ሶሽያል ስታተስ ማግኘቱ ነው።

በጀርመን የዘውዱ አገዛዝ ውስጥ ይህ ሁኔታ በጣም ትልቅ የቢሮክራሲያዊና ወታደራዊ ስትራተስ እንዲፈጠር አድርጓል። የመንግሥቱ መሣሪያ ከላይ ወደታች በተመሠረተ ፍጹም ፀረ ዲሞክራሲያዊ የፊውዳል አሠራር በጣም የተሞላ ሊሆን ችሏል። በኢኮኖሚው ዕድገት በኩል የጀርመን ባንክና የእንዱስትሪው ካፒታል ከፍተኛ የመጠራቀም ደረጃ ላይ መድረስ ጀምሯል። ባንድ በኩል የመንግሥቱ መሣሪያ አደረጃጀት ይህን ሂደት አቀሉታል። በሌላ በኩል የኢኮኖሚው አካሎች አደረጃጀት የመንግሥቱን መሣሪያ አቅፎ ደገፍ ይዞት ሊቆይ ችሏል።

ሐ/ የጀርመን ኢምፖየር /ግዛት/ አመሠራረት ርዕዮተ ዓለማዊ ውጤት

የጀርመን ኢምፖየር አመሠራረት ከሌሎች የከበርቴ አብዮት ከተደረገባቸው ብሄሮች መለየት የጀርመን ብሄራዊ ንቃተ ህሊና የተለየ ጠባይ እንዲኖረው አድርጓል።



የአንድ ብሄር መንግሥቱ የእራሱ ትግል ውጤት በማይሆንበት ወቅት፣ አንዳች የማይደፈር የተለየ ሃይል አድርጎ መቁጠርን ያስከትላል። የጀርመን ብሄር በወታደራዊ ሃይል በመስፋፋት ላይ የተመሠረተ እንጂ እንደተቀሩት ካፒታሊስት አገሮች በከበርቴ አብዮት አማካይነት፣ ከከበርቴው የካፒታል አገዛዝን ለማስፋፋት ያስተጋባ በነበረው በ"ነፃነት፣ ወንድማማችነት፣ ዲሞክራሲ" ስም የተገነባ አልነበረም። የከበርቴው ዲሞክራቲክ አብዮት መክሸፍና የጀርመን የነገሥታት አገዛዝ የተጫወተው የመስፋፋት ሚና ውጤት ነው። የዚህ ርዕዮተ ዓለማዊ ውጤት የመንግሥት ሃይልን "የማይደፈር የማይበገር" የበላይ ኃይል አድርጎ መቁጠር፣ የመንግሥት ኃይል "የሚከበር የተቀደሰ" በእርሱ አማካይነት ብቻ ታሪክ የሚሰራ መሆኑን የሚያስማን ንቃተ ህሊና መስፋፋት ነበር። ስለዚህም የካፒታል አገዛዝ መስፋፋትን መደገፍና እንደ "ብሄራዊ ተልዕኮ" መቁጠርና መጻገፍ ሊከተል ችሏል።

ይህ በከፍተኛ ደረጃ በተከከለና ገጽ ሊታይ የቻለው፣ ኢምፔሪያሊስቶች ዓለምን ለመከፋፈልና የካፒታል አገዛዝን ለማስፋፋት በሚያደርጉት ወረራ ጦርነት ወቅት ነው። ህዝቡ እንደ "ብሄራዊ ልዩ ተልዕኮ" እንዲቀበለው ከበርቴው የሚያደርገው የሚያስፋፋው ፕሮፓጋንዳ ነው። በጀርመን ውስጥ ልዩ ብሄራዊ ትርጉም ሊሰጠው ይቀጥር ነበር። በሌሎች ኢምፔሪያሊስት አገሮች ግን፣ በጊዜው አብዮታዊ ትርጉም የነበረውን የጥንቱን የከበርቴ ርዕዮተ ዓለምን በመጠቀም "ለዲሞክራሲ ለነፃነት ለዕድገት" ወዘተ.. የሚል ሽፋን በማለበስ የአሁኑን የዘረፋ ዓላማቸውን ያራምዱ ነበር። በጀርመን ውስጥ በተለይ ግን ይህ እንደ "ልዩ ብሄራዊ ተልዕኮ" ብቻ በመቁጠር ይህን ሃሳብ በማስፋፋት ወረራውን ከበርቴው ያካሂድ ነበር።

በካፒታሊስቶች መሐል ያለው ውድድር፣ ይህም የሚያስከትለው በብሄሮች መካከል ያለው የዘረፋ ውድድር የሚከተለው የኢምፔሪያሊስት ጦርነት መሠረት ነው። ፋሽዝም የተገለገለበት በ"ሶሽያል ዳርዊኒዝም" ስም የታወቀው አስተሳሰብም መሠረት ይሸው ነው።

2/ ፀረ አብዮት በ"ቫይማር" / Weimar /ሪፐብሊክ ውስጥ

ሀ/ የፀረ አብዮት ኃይሎች መጠናከርና እንደገና መስፋፋት

በጀርመን ታሪክ ውስጥ ተከሻሽቶ የነበረው ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት በ1918 ከጦርነቱ በኋላም ፍጻሜ ሊያገኝ አልቻለም። ጦርነቱ የፈጠረውን ምቹ ሁኔታ አብዮታዊ ሃይሎች እስከ መጨረሻው ተጠቅመው ድሉን በመጨረሻ ሊቀዳጁ አልቻሉም።

ጦርነቱ በመሳፍንቶቹ ርዝራዦች፣ በከባው ከበርቴና በሰፊው ሕዝብ መካከል ያለውን ቅራኔ አፈንድቶት ነበር:: በጣም ወደኋላ የቀረውን /የፊውዳል ርዝራዦች የተከለውን፣ ሳዕላይ መዋቅርን ለመደምሰስ የሚያስችል ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር:: የቆየው መንግሥት በሰበሰ ፍጹም ተበባበሮ የመውደቅ አፋፍ ላይ ነበር::

ከጦርነቱ ወቅትና በኋላ በተካሄደው ትግል የወዝአደሩና የሰፊው ሕዝብ ሃይል የበሰበሰውን መንግሥት ከሥር መሠረቱ ፈነቃቅሎት በመጨረሻም የወዝአደሩና የወታደር ሶቪየት ኃይል ተቋቋሞ ነበር:: ነገር ግን ብዙ ጊዜ ሊቆይ አልቻለም:: ስለሆነም ይህ የተፈጠረው የህዝብ ኃይል በጀርመን ህዝብ ውስጥ የማይፋቅ ጠንካራ ቅርስ በሰፊው ጥሎ ሊሄድ አልቻለም::

የ1918 አብዮታዊ እንቅስቃሴ እስከ መጨረሻው ድል አለመምታትና አብዮታዊው የህዝብ ኃይል ሊቆይ ያልቻለበት ሁለት ምክንያቶች አሉት፣
1ኛ/ በቀደሞው አገዛዝ በተያያዥ ይታገሉ የነበሩት የአድርባይ ከበርቴ ኃይሎች ሰፊው ሕዝብና ወዝአደሩ በቀጥተኛ የሃይል ትግል የፖለቲካ ሃይል እንዳይጨብጥ "ሕጋዊ ቅዝት" ውስጥ ስለአስገቡት፣ 2ኛ/ የቀደሞው የመንግሥት መሣሪያ ሃይል ድል ለመምታት የካፒታሊስት ዕድገት ከፍተኛ ደረጃ በደረሰበት ጀርመን ውስጥ ያለው ለረጅም ጊዜ በሰፊው የተገነባው የመንግሥቱ የጭቆና መሣሪያ ጠንካራነት /ምንም እንኳን ቢበሰብስም/ ከመጠን በላይ የነቃ የተደራጀና የታጠቀ አብዮታዊ ሃይል ይጠይቅ ስለነበር ነው::

የነጋዴውና ከባተኛው የከበርቴ አንዱ ክፍል የመንግሥት መሣሪያ፣ ቢሮክራሲው፣ የሚሊተሪ ሃይል፣ በአብዮታዊ ኃይል ፍጹም የሥር መሠረቱ መሰባበር ነበረበት ለዚህ የአብዮት ፈላጊነት ብቻ፣ የተወሰኑ አብዮታዊ ኃይሎች ግላዊ ምኞት ብቻ፣ ያውም በዚያን ጊዜ በነበረው ችግርና የፖለቲካ ሥልጣን ለመጨበጥ ሙሉ በሙሉ አስፈላጊውን ዝግጅትና ንቃት ባልፈጸመው የወዝአደሩ እንቅስቃሴ ብቻ መተው በቂ አልነበረም:: በጠነከረ አንድነት ላይ የተመሠረተ የነቃ አመራር ያስፈልገው ነበር:: የአድሃሪውን ግንብ ፍጹም መሰባበር፣ ከሰባበሩም በኋላ በርሱ ፋንታ ብቅ ብሎ የነበረውን የወዝአደር ኃይል፣ የወዝአደር ወታደር ሶቪየት በከፍተኛ ንቃት ድርጅትና ትጥቅ ላይ በተመሠረተ በቋሚነት አስፈላጊውን የኢኮኖሚ ዕርምጃ ሲወስዱ፣ በሥራ ላይ ሊያውል የሚችል የጭቁኖች መንግሥት መመሥረት ያሻ ነበር::

የጀርመን ወዝአደር እንቅስቃሴ እኒህን ተግባሮች ሊያሟላ አልቻለም:: ስለዚህም የቀደሞው አገዛዝ ዋና ዋና መሣሪያዎች በፀረ አብዮቱ እጅ ውስጥ ሊቆዩ ቻሉ:: የፀረ አብዮቱን ሰንሰለት ከሥር መሠረቱ ለመበጣጠስ የወዝአደሩ እንቅስቃሴ አልቻለም::



በዚህም የተነሳ ፀረ አብዮቱ ኃይል እንደገና ከደረሰበት ጥቃት ሊያንሰራራ የሚችልበት አካባቢ ነበረው፣ ኃይሉን በዚሁ የጥንት የአገዛዙ መሣሪያዎች አካባቢ እንደገና ሊሰበስብ ችሏል:: ይሁን እንጂ በመጀመሪያ ክፉኛ ተዳክሞ ነበር:: ከድካሙ ሊያንሰራራ የሚችልበት ምቹ ሁኔታ ይጠብቅ ነበር::

በ"ቫይማር ኮሊሽን / coalition /" የታወቀው የጀርመን ሪፑብሊክ የተመሠረተው፣ የበፊቱን ዘውድ አገዛዝ የተካው "ብሄራዊ ሸንጎ" /ናሽናል አሴምብሊ/ በአድርባይ ሶሻል ዲሞክራቶችና የቀድሞ ሊበራል ከበርቴና የ"ካቶሊክ" የህብረተሰብ ክፍል "ወኪዎች" ከተቋቋመ በኋላ ነው:: ይህ የሆነው የወዝአደሩ እንቅስቃሴ መሥርቶት የነበረው የሕዝብ ኃይል ከተደመሰሰ በኋላ ነው:: የፀረ አብዮቱ ወገን የጥንቱ የዘውዱ አገዛዝ ወገን ያለው ኃይል አነስተኛ ነበር:: ከበርቴው ለተወሰነ ጊዜ ያይል ነበር:: ሆኖም ለአድሃሪው ኃይል እንደገና መንሰራራት ብዙም ጊዜ አላሻውም:: የጥንቱ ሥርዓተ ማህበር ምሰሶ ቢሮክራሲው የፀረ አብዮቱን ወገን ያገለግል ነበር:: የኢኮኖሚው ኃይል ሙሉ በሙሉ እጃቸው ውስጥ ነበር::
በከባድ እንዱስትሪና በትላልቅ ባለመሬቶች አካባቢ በመደራጀት በአጠቃላይ የግል ንብረትን በመከላከል፣ በሌላ በኩል ደግሞ እስከተወሰነ ደረጃ ድረስ አጊስ ከተደረሰበት ደረጃ የፖለቲካ ኃይላቸውን በማጣጣም ሊሰበስቡ ቀስ በቀስ ሊጠናከሩ ችለዋል::

ጀርመን ከጦርነቱ በኋላ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ቀውስ ውስጥ ገባች:: በተጨማሪ የጦርነት ከፍተኛ ካሣ ወዘተ..መክፈል ነበረባት:: የጥንቱ "ተለቅነት" የጥንቱ የጀርመን "ሃያልነት" ወዘተ..ም አብሮ ቀረ:: በጥንቱ አገዛዝ ሥር ጀርመን ትልቅ ኢምፔሪያሊስት ሃይል ነበረች:: በምታደርገውም ዘረፋ በዚያን ጊዜ የኢኮኖሚ ዕድገት አይታ ነበር:: በከበርቴው ሪፑብሊክ ዘመን ከጦርነቱ በኋላ ከተፈጠረው አጠቃላይ ቀውስ፣ የህዝቡ የኑሮ ደረጃ በጣም ወደታች አሽቆለቆለ:: ያልነቃው የህዝብ ክፍል በተለይም የከተማው ንዑስ ከበርቴ የዚህን ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ምክንያት ምን እንደሆነ ሊረዳ አልቻለም:: ንዑስ ከበርቴው /ይበናው ወገን ውስጥ ጥንትም የዘውዱ አገዛዝ መሠረት እንደነበረው ይታወሳል/ ጀርመን የገባችበት ሁኔታና በዓለም ላይ ያላት ቦታ "ዝቅተኛነት" ምክንያት የከበርቴው ኃይል ላይ መውጣት፣ በአጠቃላይ የተካሄደው የፖለቲካ ኃይል ለውጥ አድርጎ ወሰደው:: ፀረ አብዮቱ ይህን ሁኔታ በተቀናበረ ቅስቀሳና ፕሮፓጋንዳ ተጨማሪ የኢኮኖሚ አሻጥር ወዘተ.. ሊጠቀምበት ቻለ:: የፀረ አብዮቱ ኃይል በ"ብሄራዊ ተቃዋሚነት" /ናሽናል ኦፖዚሽን/ ስም እራሱን አደራጀ:: የጀርመን ህዝብ "ብሄራዊ" ጥቅም ተቆርቋሪ በመምሰል ተደራጅቶ እንደገና መሠረት የሚያገኝበት ሁኔታ ተፈጠረ፣ ሊያገኝም ቻለ::

ፕሮፓጋንዳውን በተለይም ያመቸለትና አርዕተ ዓለማዊ መሠረት አድርጉ የወሰደው የ "ቨርሳዩን ውል" ነበር::በዚህም ላይ በመመሥረት የጀርመን ሕዝብ ብሔራዊ ጥቅም ተሟጋች ግንባር ቀደም መስሉ ፀረ አቢዮቱ ይቀርብ ነበር::

ከዚህ በሃላ የፀረ አቢዮቱ ሃይል ቀስ በቀስ መሠረት አገኘ:: የጦር ሃይሉን ቀስበቀስ የጠነከረ ፀረ አቢዮታዊ ድርጅታዊ መልክ ሰጠው::ይህን የፀረ አቢዮት ሃይል መገሰራራት ለመቋቋም — በተሰበጣጠረም ሁኔታ ቢሆን — ወዝ አደሩ ብዙ ተጋድሎዎች አድርጓል::በ "ኪንጊቶች" የታወቀው የፀረ አቢዮት መንግሥት ገለበጣ ጊዜ፣የወዝ አደሩ እንቅስቃሴ ለዲሞክራሲ ያደረገው ተጋድሎ ፍጹም ወደር የሌለው ነበር::የቀሩት የከበርቴ ሃይሎች ግን ከፍተኛ ማወላወል አሳዩ:: ንዑስ ከበርቴዉ ጠቅለሉ ወደ ፀረ አቢዮቱ ካምፕ ገባ::ወዝ አደሩ ለዴሞክራሲ በሚያደርገው ትግል ብቻውን ተነጠለ::ከዚያም በከበርቴው "ብሔራዊ ሸንጎ" ውስጥ የቀኙ /አድሃሪው፣ከፀረ አብዮት ጋር የተሻረከው/ ክንፍ መጠናከር ጀመረ::ፀረ አብዮት ሃይሎች በዲሞክራሲያዊ ሃይሎች ላይ ጥቃት ሲፈፅሙ ብሔራዊው ሸንጎ እንዳቸም እርምጃ አይወስድባቸውም ነበር::ከፍ ብለን እንዳልነው፣በጦር ሃይሉ አካባቢ የፀረ አብዮቱ ሃይል ከፍተኛ መሠረት መጣል ያዘ::ከበርቴው "ሬፓብሊኩን ለመከላከል" እያለ በሰበሰበው ቢሮክራሲ አማካይነት የሚፈጸሙትን አሻጥሮች ለመቋቋም አንዳንድ ድንጋጌያች አውጥቶ ነበር::ነገር ግን በሥራ ላይ የዋለበት ጊዜ አልነበረም::

ከ1920 — 23 ባለው ጊዜ ውስጥ የጀርመን ወዝ አደር ለዲሞክራሲ ከፍተኛ ተጋድሎ ሲያካሂድ፣ ከበርቴው /"ሬፓብሊካን"/ የተከተለው ፖለቲካ ባንዱ በኩል ሬፑብሊኩን ከመላሽ ሃይሎች ለመከላከል የወዝ አደሩን ሃይል መጠቀም፣ በሌላ በኩል የወዝ አደሩ ሃይል ሲያይል ከፀረ አብዮት ሃይሎች፣ከነገሥታቱ ርዝራዦች ጋር በመዳበል፣ በ "ከነ ሥርዓት" ስም ለዲሞክራሲ የሚደረገውን ትግል መግታት ነበር:: የለየለት አድርባይነት::የጀርመን ወዝ አደር ምንም እንኳ ከፍተኛ ቆራጥ ተጋድሎ ቢያደርግም፣በነበረው ንቃታዊ፣ድርጅታዊና ትጥቃዊ ጉድለት፣በ1918 "በእጁ ላይ ወድቃ" የነበረውን ለጋ የሕዝብ ሃይል ለመከላከልና በቀጠሉት ዓመታት ውስጥ በደረሰበት ጥቃት የተነሳ በፀረ አብዮት ሃይሎች ላይ አሸናፊ ሆኖ ሊወጣ አልቻለም:: የፀረ አብዮቱን ኢኮኖሚያዊ መሠረት ለመደምሰስ አልቻለም::በዚህ ውስጥ የከበርቴው መወላወል፣በተለይም የመሬትና የእርባታ መሣሪያዎች የግል ንብረትነት እንዳይነካ ከበርቴው ከፀረ አብዮት ጋር ያደረገው ትብብር ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል::አድርባዮቹ ሶሻል ዲሞክራቶች በብሄራዊው ሸንጎ ውስጥ በነበራቸው ሃይል አማካይነት በአብዮታዊው ወዝ አደር ላይ የፈጸሙት ክህደት /ከከበርቴው ጋር ያደረጉት ትብብር/ከፍተኛ ቦታ ይሰጠዋል::



ይወዝ አደሩ እንቅስቃሴ ያደረገው ተጋድሎ ሊሳካ ያልቻለበት ዋና ዋና ምክንያቶች፣

1ኛ/ሬፓብሊካኑ ከበርቴ በፀረ አብዮትና በዲሞክራሲያዊ አብዮታዊ ሃይሎች መሃል በመዋለል ፀረ ወዝ አደር የፖለቲካ መሥመር መከተሉ፣ ከዚያም አድር ባዮቹ ሶሻል ዲሞክራቶች ከዚሁ ጋር ተስ ተብ ማለታቸው፣

2ኛ/ የወዝ አደሩ እንቅስቃሴ የፖለቲካ ነፃነትን የጠበቀ የነቃ፣ የተደራጀና የታጠቀ በቂ ብሔር አቀፍ አብዮታዊ ሃይል ሊሆን ባለመቻሉ ፣

3ኛ/በዚህ ላይ የወዝ አደሩ ፓርቲ ውስጥ የነበሩት ከፋፋይና ፑቺስት የፖለቲካ አዝማሚያዎች ለወዝ አደሩ እንቅስቃሴ ድካም ቀላል ሚና አልተጫወቱም:: የወዝ አደሩ ፓርቲ አንድ አንድ የጠነከረ ግንባር ቀደም የታጠቀ የነቃ የወዝ አደር የፖለቲካ ሃይል እንቅስቃሴውን ለመራ አልቻለም ነበር::በዚህ ሁኔታ ከወዝ አደሩ ፓርቲ የተገነጠለው አንደኛው ክንፍ ክህደት፣ከአድር ባዮቹ ሶሻል ዴሞክራቶች ጋር መግጠምና የሬፓብሊካኑ ከበርቴ ተቀጥያ መሆን /የሬፓብሊካኑ ከበርቴ ፀረ ወዝ አደር የፖለቲካ መሥመር የታወቀ ነው/ ወዝ አደሩ ታሪካዊ ተልዕኮውን አፍጻሜ እንዳያደርስ አድርጉታል::

የዚህ ሁሉ ውጤት ከበርቴውና የፀረ አብዮቱ ሃይል /የዘውዱ አገዛዝ ርዝራዦች/ ተስማምተው በሕዝቡ ጫንቃ ላይ መግዛት፣መበዝበዝ ሆነ::በተለየ መልክና ሁኔታም ቢሆን የቀየው "የተቀደሰ አንድነታቸው" እንደገና ሰፈነ ማለት ነው::

በዚህን ጊዜ የፀረ አብዮቱ ሃይል ውስጥ አንድ የመከፋፈል ሂደት ተካሄደ::በ "ብሔራዊ ተቃዋሚነት" ተጠራቅመው የነበሩት —ከንዑስ ከበርቴው አንስቶ፣በትልቁ ከበርቴ አድርጉ እስከ የመሳፍንቱ ርዝራዥ ድረስ— የህብረሰቡ ክፍሎች ውስጥ ሁለት አጠቃላይ የ "ፖለቲካ" አዝማሚያዎች ይታዩ ነበር::የፀረ አብዮቱ አንድ መሠረት የከተማው ንዑስ ከበርቴ እንደነበር የሚታወስ ነው:: ይህ በሚንሰራራው የከበርቴ አገዛዝ ላይ በፀረ አብዮቱ አማካይነት በ "ፀረ ካፒታሊስትነት" ተቀስቅሶ ነበር::በከባድ ኢንዱስትሪ አካባቢ የተደራጀው ከዚያም ትላልቅ ባለመሬት ከአዲሱ የእርበታ ስርዓት ጋር እራሱን ሲያጣጥምና ከሬፑብሊካን ከበርቴው ጋር ሊስማማ ቻለ::በፀረ አብዮታዊው ትግል ውስጥ በ "ፀረ ካፒታሊስትነት" ተጠራቅሞ የነበረው ንዑስ ከበርቴ ግን ይህን ስምምነት እንደ ክህደት ቆጥሮት ነበር::ይህ ሁኔታ ሁለቱን አዝማሚያዎች እስከተለ፣ጊዜያዊ ቅራኔ በመሃከላቸው ፈጠረ::የፀረ አብዮቱ አንደኛው ክንፍ ከሬፓብሊካኑ ከበርቴ ጋር መስማማቱን ሌላው ክንፍ እንደ ክህደት በመቁጠሩ እራሱን ለጊዜው ገንጥሎ በማደራጀት "እራሱን የቻለ" እንቅስቃሴ ሆነ::ይህ የጀርመን ፋሽስታዊ እንቅስቃሴ እንጭጭ አድገት የጀመረበት ነው ለማለት ይቻላል:: የኋላው የናሂትለር ፓርቲ "ሥር ነቀልነት" ብሔራዊነት" መሰካዊ "ፀረ ካፒታሊስትነት"

ር ዑተዓለማዊ መሠረትና የፖለቲካ አዝማሚያ የተፈለፈለውም በዚህ ነበር:: የነዚህ ሁለት አዝማሚያዎች አንድነት እንደገና የተመሠረተበት ጊዜ ላይ ዝቆ በለን እንመጣለን::

ለ/ የ"ህጋዊ ተቃዋሚነት" /ሌጋል ኦፖዚሽን/ ጊዜ

የጀርመን ዘውድ አገዛዝ ከወደቀ በኋላ፣ሪፐብሊኩ ከተመሠረተ በኋላ የነበረው የከረረ የመደብ ትግል ምን መልክ እንደነበረው አይተናል::ጀርመንን አጥለቅልቆት የነበረው የኢኮኖሚ ቀውስ፣ኢንፍሌሽን እንዳበቃ የተለያዩት የፖለቲካ ሃይሎች መደላደል ጀመሩ::የፀረ አብዮቱ ሃይል አንደኛው ክንፍ ከተፈጠረው አዲስ ሁኔታ ጋር እራሱን አጣጣመው::የከበርቴው የፓርላማ ዲሞክራሲያዊ አገዛዝ መሠረት ያዘ::የፀረ አብዮት ሃይሎችም በዚህ የከበርቴው ሥርዓት ውስጥ በ"ህጋዊ መንገድ" መንቀሳቀስ ያዙ::የመንግሥትን ጊዜያዊ መደላደል ሊገቱት እንደማይችሉ በመገንዘብ፣ከዚያ ወዲያ የነበረው የጥንቱ ፀረ አብዮት ሃይል ትግል "ህጋዊ ተቃውሞ" መልክ በመውሰድ ያተከረው የተደላደለውን የመንግሥት መሣሪያ /ሥረመሠረቱም አልተነካም ነበርና/ጠቅላላ በቁጥጥራቸው ስር ለማድረግ ነበር::

ከ1924 — 29 ባለው እድገት ውስጥ አዳዲስ የፖለቲካ ፓርቲዎች በመመሥረት አድሃሪው ሃይል መደላደል ጀመረ::በሪፓብሊካኑ ከበርቴ ውስጥ አመራሩን የያዘው በ" ኬሚካል ኮንዘርን" አካባቢ የተደራጀው ነበር::ከዚህ ጋር ጠቅላላ የኢንዱስትሪ ከበርቴው ከፍተኛ ሚና መጫወት ጀመረ::በዓለም የጠነከረውም የከበርቴ መደብ ክፍል ይኸናው ነበር::በዚህ ጊዜ ውስጥ የነበረው የኢኮኖሚ እድገት ግን በዙ አልቆየም::ጠቅላላ ኢኮኖሚው እንደገና ታላቅ ቀውስ ውስጥ ገባ::

3. የተከተለው ቀውስ

ጀርመን በዚህ ወቅት የገባችበት ቀውስ አንደኛ የዓለም ጦርነት እንዳበቃ የነበረትን ቀራኒዎችን በሙሉ ለየት ባለም መልክና ይዘት ቢሆንም እንደገና እንዲወጡ አደረጋቸው::ጊዜያዊው የኢኮኖሚ እድገት ማሽቆልቆል ጀመረ::ይህ ቀውስ በገዥው መደብ ረድፎች ውስጥ ከፍተኛ ቅራኔ ፈጠረ፣በተለይም ከቀውሱ የተነሳ በከሰረው የከበርቴ ወገንና የጠነከረ መሠረት ባለው መሃከል ያለው ቅራኔ ተፋፋመ::በየጊዜው የ"አገዛዝ" ለውጦች ተደረጉ::

በቀውሱ የተነሳ በአድሃሪው የገዥ መደብ አመራር ሥር ያለ ማህከላዊ የኢኮኖሚ ቁጥጥር ተደረገ::ይህ ማህከላዊ የኢኮኖሚ አስተዳደር ያስከተለው በወዝ አደሩና በተጨቆኑት የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ የቀውሱን ውጤት መጫን ነበር



እንጂ አንዳቸም መሻሻል አላስከተለም:: የወዝ አደሩ እንቅስቃሴ በዚህ ሁኔታ ውስጥ፣ምንም እንኳን ከፍተኛ ትግል ቢያካሄድም፣አስፈላጊውን ያህል እርምጃ ሊያደርግ አልቻለም::ጠቅላላ የኑሮ ዋስትና አጥቶ ነበር::ያለበት የኢኮኖሚ ሁኔታ ታላቅ አዘቅት ውስጥ ነበር::ስለሆነም የወዝ አደሩ እንቅስቃሴ ከአድሃሪዎች ጥቃት እራሱን ለመከላከልና አንድ ያልተከታተነ የጠነከረ የፖለቲካ ሃይል ሊሆን አልቻለም::በአድርባዩ ሶሺያል ዲሞክራቲክ አመራር ስር ያለው ከተቃናቃኝ /አከቴፓ/ ትግል ተገለሉ ነበር::ይህም አመራር ከጀርመን ኮሙኒስት ፓርቲ ጋር ፀረ አብዮት ሃይልን የሚቋቋም የትግል አንድነት ለመመሥረት የተደረገውን ጥረት እጅግ አደናቀፍ ነበር::

ከፍ ብለን እንስተን የነበረው፣ከፀረ አብዮት አብራክ የወጣው አንደኛው "ብሄራዊ" የፖለቲካ ሃይል ቀውሱ ከመምጣቱ በፊትና አጠቃላይ "ጤናማ" የኢኮኖሚ ሁኔታ በነበረበት ጊዜ እራሱን ሊያቆይ ችሏል::በዚህን ጊዜ ውስጥ "እራሱን የቻለ" አንድ ሰፊ ሕዝባዊ መሠረት ያገኘ ፋሽስታዊ እንቅስቃሴ ሆኖ ወጣ::ይህ ሃይል በቀውሱ ከተነኩት የህብረተሰብ ክፍሎች ውስጥ በተለይ በንዑስ ከበርቴው ውስጥ በሙሉ መሠረት ሊያገኝ ቻለ::የፋሺስቱ እንቅስቃሴ እንዴት ከጥንቱ የፀረ አብዮት ሃይል እንደተፈለፈለና እንዳደገ ከሞላ ጉደል ለመመልከት እንችላለን::ጀርመኒ የሞኖፖሊ ካፒታሊዝም እድገት ደረጃ ደርሳ ቀውስ ውስጥ ስትገባ የጥንቱ ፀረ አብዮት ሃይል ምን የፖለቲካ መልክ ይዞ እንደመጣ የፋሺስታዊው እንቅስቃሴ ምንጭና እድገት ያሳየናል::በጥሩ የታለፈውን የዕድገት ሂደትና መጨረሻውን እንመልከት::

በዘውዱ አገዛዝ ውስጥ አመራረን ይዘው የነበሩት የገዥው ክፍሎች — ጁንከሮቹ /ታላላቅ የመሬት ከበርቴዎች/ የከባድ ኢንዱስትሪ ከበርቴና የጦር ሃይል የበላይኛው ረድፎ—ች ናቸው::ባለፈት አሥር አመታት ውስጥ ልዩ ልዩ ለውጦች አድርገዋል::የጀርመን ኢምፓየር ሲስፋፋ የአንድነት መሠረት ጣሉ፣ጀርመን ታላቅ ኢምፔሪያሊስት ሃይል መሆን እንደጀመረች ከፍተኛ እድገት አደረጉ::የ1918—21 አብዮታዊ እንቅስቃሴ ማዕበል ከተሻረቸው ወዲህ አንዳንድ የአሰላለፍ ለውጥ በማድረግ ዕድገታቸው ለጊዜው ተገታ::ከሪፐብሊኩ መመሥረት በኋላ የተዳከመው ፀረ አብዮት ቀስበቀስ እንደገና ተጠናከረ:: ከመጀመሪያው የአለም ጦርነት በኋላ የተፈጠረው ቀውስ ገብ እንዳለና ጀርመኒ ከፍተኛ እድገት ባደረገችበት ወቅት ካለው የፖለቲካና የኢኮኖሚ ሁኔታ ጋር ሃይላቸውን በማጣጣም እንደገና ሊገነቡት ቻሉ::ከዚያ በተከተለው ቀውስ ወቅት፣ጥንት ከነበረው አብራክ ወጥቶ የነበረው "የንዑስ ከበርቴ" "ብሔራዊ" እንቅስቃሴ ጋር እንደገና አንድነት ፈጠሩ::ይህ ፋሺስታዊ እንቅስቃሴ በተከተለው ታላቅ የፖለቲካና ኢኮኖሚ ቀውስ ወቅት ሰፊ ሕዝባዊ መሠረት በቀላሉ ሊያገኝ ስለቻለ ጠቅላላ ሥርዓቱ በደረሰበት መንኮታኮት ሊያድነው የቻለው ይኸው ብቻ ነበር::ባለፉት ዓመታት ውስጥ ጀርመን በፋይናንስ ካፒታል አገዛዝ ጠንከር ወጥቶ ነበር::ፋሺስታዊ እንቅስቃሴም ታቅፎ ተደግፎ የተያዘው በዚህ በፋይናንስ ካፒታል ነበር::ፋሺዝምም እነዚህ ሲወርዱ ሲዋረዱ የመጡት ሦስት የፀረ አብዮት ሃይሎች ሙሉ አንድነታቸው የሰፈነበት የፋይናንስ ካፒታል እጅግ አድሃሪው አገዛዝ ነው::

ተጨማሪ

## ቦናፓርቲዝም ምንድን ነው?

### መግቢያ

ከአንዳንድ "ምሁራን" አካባቢ በኢትዮጵያ ያለው መንግሥት፣የፖለቲ
ካ ስልጣን የጨበጠው ደርግ ቦናፓርቲስት ነው ለማለት የቃጣቸው አሉ፡፡ለምሳሌ
አንድ "አዲስ ሕይወት" በሚል በአር ስም ስለ ኢትዮጵያ ሁኔታ የተጻፈ ጸሑፍ
አለ፡፡ የዚህ ጸሑፍ ይዘት ትችትም ሆነ ሌላ መስጠት እዚህ ቦታው አይደለም፡፡
ጊዜያችንንም አናጠፋም፡፡ይሁን እንጂ /እዚሁም እንደገና/ የቦናፓርቲዝምን ምን
ነት ለመግለጽ ብዙ ዓመታት ወደ ኋላ ተመልሰን ማርክስ በለዚሁ አርእስት የሰ
ጠውን ትምህርት ለማቅረብ ልንገደድ ነው፡፡አለበለዚያ በፋሺዝም ጸሑፋችን መግ
ቢያ ላይ ያለነው ውዝንብር ሊፈጠር ነው፡፡ የኢትዮጵያ ንዑስ ከበርቴ "ምሁራን"
በተለይም ደንፊያቹ ያገኙትን ፅንስ ሀሳብ /ኮንሴፕት/ ያገኙበት መለጠፍ ነውና
ሁሉንም እያስተካከልንላቸው አንዘልቀውም፡፡ንዑስ ከበርቴ ቀውስ ውስጥ ስትገባና
ከፀረ አብዮት ጋር ስትዳበል የምትይዘው የምትጨብጠው ስለሚጠፋት መድሃኒቷ የ
አብዮት ለምጭ ብቻ ነው፡፡ያምሆነ ይህ ማርክስ ስለ ቦናፓርቲዝም የሰጠው ትምህ
ርት ከፍተኛ ትርጉም ስላለው ይህን አጋጣሚ በመጠቀም ስለ ቦናፓርቲዝም ያለ
ንን እናቀርብ፡፡

በታዳጊው የካፒታል አርባታ ሃይልና ወደ ኋላ በቀረው የአርባታ ግን
ኙነት መሃከል ያለው ቅራኔ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሶ፣ፈንድቶ፣ ፈረንሳይን መ
ቀላሳ ያናወጣት የፈረንሳይ ከበርቴ ዲሞክራቲክ አብዮት በታሪክ ውስጥ ታላቅ
ቦታ ያለው ነው፡፡ይህ አብዮት ከሌሎች የከበርቴ አብዮቶች አይነተኛ የሚያደር
ገው የከበርቴ ዲሞክራቲክ አብዮት በንፁህ መልኩ የተካሄደበት፣በፊውዳሊዝም የ
ተጨቆኑት የሰፊው ሕዝብ ክፍሎች በአብዮታዊ እንቅስቃሴያቸው ፊውዳሊዝምን ከነ
አውታሮቹ ያንኮታኮተ ስለ ሆነ ነው፡፡ከበርቴው ይህን አብዮት በመምራት ታሪካ
ዊ ተራማጅ ግዴታውን የፈጸመበት አብዮት ነበር፡፡

ገበሬው በዲሞክራቲኩ አብዮት ውስጥ በከበርቴው በመመራት የፊውዳሉን
ሥርዓት ደምስሶ ነበር፡፡ የከበርቴው መደብ የፖለቲካ ሃይል በእጁ አስገብቶ ረ
ፓብሊኩን መሥርቶ ነበር፡፡ የፖለቲካ ሃይል በእጁ ካስገባ በኋላ በፊውዳሉ ሥር
ዓት ታፍኖ የነበረት የካፒታሊስት የአርባታ ሃይሎች እያደጉ መጡ፡፡በፊውዳሉ
የዐርባታ ግንኙነት መታፈናቸው አከትሟልና፡፡ገበሬው መሬትን በጉልበቱ እያለማ
ምርትን እያባደገ ራሱን ወደ ነፃ ገበሬ /ፋርመር/ እየቀየረ መጣ፡፡ይህ ያለ



ሆነለት መሬትን እየሸጠ ወደ ከተማ እየሄደ ወይንም እዚያው ገጠር የሥራ ሃይ
ሉን እየሸጠ የካፒታል አገዛዝ ባጠቃላይ እየተስፋፋ ሄደ፡፡ገበዩ ተስፋፋ፡፡ካ
ፒታሊስቶቹ ከመሰሎቻቸው ጋር እየተወዳደሩ፣ይበልጥ ወዝ አደሩን ለመበዝበዝ የ
ቻለው፣ለዕቃው ገቢያ ሊያገኝ የቻለው፣ወዘተ ሌላውን እየጣለ፣እንደገና እየወደ
ቀ እየተነሳ ቀየ፡፡ባጠቃላይ በህበረ ሰቡ ውስጥ ያሉት አዲስ የአርባታ ሃይሎ
ቹ በታላቅ ፍጥነት አደጉ፡፡ የውድድር ካፒታሊዝም በንፁህ መልኩ ሥራ ላይ የዋ
ለበት ጊዜ ነበር፡፡

በዚህን ጊዜ ውስጥ ግን የፊውዳሉ መደብና ቅርሶቹ ሞቱ፣አከተሙ ማለ
ት አይደለም፡፡ የጠነከረ የመደብ ትግል ነበር፡፡ የፊውዳሉ መደብ እራሱን ወደ
መሬት ከበርቴ በመቀየር፣የፖለቲካ ሃይሉን መልሶ ለመቀማት ከሬፐብሊካኑ ከበር
ቴ ጋር ሃይለኛ ትግል ያደርግ ነበር፡፡

የወዝ አደሩ መደብ በዚህ የፈረንሳይ አብዮት ዉስጥ የተጫወተው ሚና
ከሌሎች ታዳጊ መደቦች ጋር በመሆን ለዲሞክራሲ ባጠቃላይ የፊውዳሉን ስርአት
ከመታገል በስተቀር የራሱን የመደብ ጥቅም አውቆ፣የመደብ ንቃት አግኝቶ አልተ
ሰለፈም፡፡አይችልምም ነበር፡፡ የወዝ አደሩ እንቅስቃሴ ገና መጀመሩ ነበር፡፡
የከበርቴው ወይንም የንዑስ ከበርቴው ተቀጥያ በመሆን በመደብ ትግል ውስጥ ለ
ኢኮኖሚ መብቱና ጥቅሙ በቆራጥነት ከመሳተፍ በስተቀር ነፃ የራሱ የፖለቲካ ድ
ርጅት ኖሮት አልታገለም፡፡

ከዚህ የፈረንሳይ አብዮት አንስቶ እስከ ማርክስ በ18ኛ ብሩሜር
ጸሑፍ ዉስጥ ስለሚያወሳው የመደብ ትግል ድረስ በፈረንሳይ ያሉት መደቦችና
የህብረሰብ ክፍሎችን በሙሉ ያጥለቀለቀ ከፍተኛ የመደብ ትግል እንደነበረ
ግልጽ ነው፡፡ቦናፓርቲዝም በማርክሳዊ ጸሑፎች ውስጥ እንደ ፅንስ ሀሳብ /ኮን
ሴፕት/ መውሰዱ የተጀመረው ማርክስ በ18ኛ ብሩሜር ውስጥ ቦናፓርት እንዴት
አድርጎ ሃይል እንደጨበጠና ምን ትርጉም እንዳለው፣ማንን እንደሚወክል፣ወዘተ
ካብራራ ወዲህ ነው ፡፡ስለ ቦናፓርቲዝም ለመረዳት ይህ የማርክስ ጸሑፍ ያዘላቸ
ው ፍሬ ነገሮች የማይታለፉ ናቸው፡፡ስለሆነም በዚህ የማርክስ ጸሑፍ ላይ በመ
መርኮዝ የተዋቸውን ዋና ዋና ትምህርቶቸ ባጭሩ እንመለከት፡፡

### የነበረው የመደብ ትግልና የመደቦች አሰላለፍ ባጭሩ

ማርክስ በዚያን ጊዜ ስለነበረው የመደብ ትግል ሲያወሳ በጸሑፉ መጀ
መሪያ ላይ ያስጠነቀቀ የነበረው የቦናፓርትን ሃይል መጨበጥና እራሱ ቦናፓርቴ

ዝም የተባለውን ፀገሰ ሀባበ ለመረዳት የነበረውን የመደበ ትግለ በደገበ ማጥ
ናትና የፈጠረውን ሁኔታና ግንኙነቶቹ በሚገበ መመርመር ማበፈለጉን ነበር::በ
ደፈናው የአንድ "ሃይለኛ ሰው" ድርጊት ወይንም መንግሥት ገለበጣ /ኩዴታ/
አድርጉ መውሰዱን ከፍተኛ ስህተት መሆኑን ሲያስረዳ "አቢበቱር ሁጉ ጠቀላላ
ድርጊቱ/የበናጀርት ሃይለ መጨበጥ/የሚታየው ከንፁህ አየር ውስጥ እንደወጣ
መበረቅ ነው::የአንዱ ግለሰበ የሃይለ ሥራ በቻ ነበር የሚታየው" ይላለ ማ
ርክስ::

> "He does not notice that he makes this individual great instead of little by inscribing to him a personal power of initiative such as would be without parallel in World History. Proudhon for his part, seeks to represent the coup d'état as the result of an antecedant historical development. Unnoticeably however, his historical construction of the coup d'état becomes a historical apologia for its hero. Thus he falls into the error of our so called objective historians. I on the contrary demonstrate how the class struggle in France created circumstances and relationships that made it possible for a grotesque mediocrity to play a hero's part."

ማርክስ ይህንን ማስጠንቀቂያ የጻፈው በማንኛውም ጊዜ የተካሄደን ድ
ርጊት መመርመር የሚገባው የገዱ ከነበረው የመደበ ትግለ በመነሳትና ያለውን
የመደበ ግንኙነትና የፈጠረውን ሁኔታ በመመለከት መሆኑን ለማሳየት ነው::ወደ
ፊት አንድ የፖለቲካ ለውጥም ሆነ ድርጊት ሲካሄድ የአንዱን ሁኔታ አሊሳው ሳ
ይ መለጠፍ እንዳይከተለም ነበር:: አንዱ የፖለቲካ ለውጥ ለመረዳት አንዱ
ሕበረሰበ ያለበትን ታሪካዊ፣ ኤኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ያሉትን መደቦች፣ አሰላለፋ
ቸውን፣ ትግላቸውን ወዘተ.. ሳይመረምሩ ባንዳንዱ ትርዐይቶች ላይ በቻ ከተ
ወሰኑ ፍሬ የሌለው መደምደሚያ ላይ ይወደቃለ::

ማርክስ፣ ከ24 የካቲት 1848 እስከ ታህሣሥ 1851 /እ.አ.አ./
የተካሄደውን የፈረንሣይ አበዮታዊ እንቅስቃሴ በሶስት ዋና ዋና ክፍሎች ይመዱ
ባቸዋለ:: 1/ የየካቲት ወቅት 2/ የኮንስቲቱሽናለ በሄራዊ ሸንጎ ወቅት
3/ የኮንስቲቱሽናለ ሬፐብሊክ ወይንም የሌጂስሌቲቭ በሄራዊ ሸንጎ ወቅት::
በነዚህ ጊዜ ውስጥ የተካሄደውን የመደበ ትግለ አንዱ ባንዱ ለመተንተን አን
ሞክርም:: በዋና ዋናዎቹ ድርጊቶች ላይና በተበጡት ፍሬ ነገሮች ላይ በቻ
እንወሰናለን::



1/ የየካቲቱ የትግለ ፋናት፣ ከየካቲት 24 እስከ ግንቦት 4
1848 ባለው ጊዜ ውስጥ የምርጫ ሪፎርም ሊደረግ የታሰበበት፣ የገዢው
መደበ በየበታው ያለውን ተጽዕኖ ጠቀላላ የፋይናንስ አሪስቶክራሲውን አገ
ዛዝ ለማስወገዱ የታሰበበት ጊዜ ነበር:: በዚህን ጊዜ ወዝአደሩ የሪፖብ
ሊክ ማስፈለገና በዱርው ገቢያዎች ላይ መዝመት አስፈላጊነትን ተረዱቶ ስለ
ነበር በመሣሪያ ኃይለ በየ" ባሪካዱ" ቁራጥ ትግለ አካሄደ ነበር::
ሆኖም የሪፖብሊክ አስፈላጊነት ገለጸ የነበረው ለወዝአደሩ በቻ ባይሆን
ለከበርቴው ለንዑስ ከበርቴውም ነበር:: ፋይናንስ አሪስቶክራሲውም ይህን
መቀበለ የተገደደበት ጊዜ ነው:: ምን ዓይነት ሬፐብሊክ መሆን እንዳለ
በት ለወዝአደሩ ገለጸ አለነበረም::

ትግሉ እየተፋፋመ እንደሄደ የመናርኪስት ኃይሎች እራሳቸውን
ለመሰበሰብና፣ ትግሉን ወደፊት ለመግፋት በሚሻው በወዝአደሩ ላይ በመ
ዝመት ከቀረት ዝቅተኛ መደቦች፣ ከገበሬውና ከንዑስ ከበርቴው ሊነጥሉት
ቻለዋለ::

2/ ከ4 ግንቦት እስከ ግንቦት መጨረሻ 1848 እንዲሁም
የሰኔው የወዝአደር ተጋዱሎ ሁለተኛው የትግለ ወቀትን ያጠቃለላለ::
ምንም እንኳን ወዝአደሩ በመጀመሪያው የትግለ ወቀት አሸናፊ ሆኖ ባይ
ወጣም ያስገኘው አንዳንዱ ዱለ ነበር:: ከዚሁም ዋናው፣ በጠቀላላው
ህበረሰቡ ውስጥ የሬፐብሊክ መመሥረት አስፈላጊነት ገለጸ መሆኑ ነበር::
ከበርቴው የራሱን ሬፐብሊክ የመሠረተው በዚህ ጊዜ ነው:: በዚህን ጊዜ
በከበርቴውና በወዝአደሩ መሃከለ ቅራኔው ከመከረሩም በላይ ከበርቴው
ወዛደሩን ከገበሬውና ከንዑስ ከበርቴው ለመነጠለ ቻሎ ነበር:: ይህ
ሁኔታ ለወዝአደሩ የሰጠው ትምህርት፣ የፖሪስ ወዝአደር በተለይ የተመ
ሠረተው ሬፐብሊክ የርሱ እንዳለሆነ መረዳት ነው:: የከበርቴው ሬፐ
በሊክ በሃይለ ለማጥፋት የሰኔን የታጠቀ ትግለ /ኢንሰራክሽን/ ያደረ
ገውም ለዚሁ ነበር::

በዱርጅት አመራርና ገቃት ጉዱለት ከዚያም በህበረሰቡ ውስጥ
ካሉት የትግለ ደጋፊዎቹ ሊሆኑ ከሚቸሉት ከገበሬውና ከንዑስ ከበርቴው
ወዝአደሩ ተነጥሎ ስለነበር የመደበ ጦርነቱ አሸናፊ ሆኖ የመጣው ከበ
ርቴው ነበር:: የሃይለ አሰላለፋ፣ ባንዱ በኩለ ወዝአደሩ በሌላ በኩለ
ፋይናንስ አሪስቶክራሲው ከነጠር ኃይሉ፣ ከበርቴውና የከተማው ንዑስ
ከበርቴ እንዲሁም ቦዘኔው ሎሎ ባይቀር፣ በመሆኑ ወዝአደሩ እንደሚሸነፍ
የተገመተ ነው:: ወዝአደሩ በዚህ ቁራጥ ትግሉ በዙ ታጋዮቹን አጣ፣
በዙው ያለ ፍርዱ ታሰረበት፣ ወዘተ.. ከትግሉ ግን አንዱ ታላቅ ትም
ህርት አገኘቷለ::

የሞናርኪው አገዛዝ የርሱ እንዳልሆነ፣ የከበርቴውም ሪፐብሊክ የከበርቴው
ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ እንደሆነ፣ ስለሆነም ወዝአደሩ የራሱን መንግሥት
ወደፊት ማቋቋም እንዳለበት ነው:: እንኳን ለፈረንሣይ ወዝአደር ቀርቶ ለጠ
ቅላላው አውሮፓ ይህ በሰኔ ወራት የተደረገው የወዝአደር ተጋድሎ ታላቅ አር
አያነት የተመላበት ነበር ይላል ማርክስ::

የወዝአደሩን ተጋድሎ ለመቋቋም አንድነት ፈጥረው የነበሩትም አድሃሪ
ያቹ፣ በተለይም የሪፖብሊኩ /ቡርዧዊ/ ከበርቴና ፋይናንስ አሪስቶክራሲው
ከፍተኛ የፖለቲካ ቅራኔ በመሃላቸው ስለነበረ የሰኔው ትግል እንዳበቃ ይህ
ቅራኔ ፈነዳ:: የወዝአደሩ ወገን የነበሩትን ሁሉ በአንድነት ከአባረሩ በኋላ
ሪፐብሊክ ከበርቴው የ" የሕግ አስፈጻሚው" አካሉን ሙሉ በሙሉ በቁጥጥሩ ሥር
አደረገ:: ይህን ያደረገው ፋይናንስ አሪስቶክራሲውንም ዱል በመምታት ነው::
የርሱን ከባዱ ተቃውሞን በመቋቋም ነው:: የመደብ ትግል ላይ የፖለቲካ ሃይ
ልን በማመልከት ዋዛ የለምና ማንም በፈቃዱ አሳልፎ አይሰጥም::

የሪፐብሊኩ ከበርቴ ከሌሎቹ አድሃሪ መደቦችና የህብረሰብ ክፍሎች
ጋር በመሆን የፓሪስን ወዝአደር ከፖለቲካ መድረክ ካስወጣ በኋላና፣ የፋ
ይናንስ አሪስቶክራሲውን ተጽዕኖ ካስወገደ ወዲህ የራሱን አገዛዝ መሠረተ::
ኮንስቲቱሽናል ብሄራዊው ሸንጎ ጠቅላላ በርሱ ቁጥጥር ሥር ነበር:: የእርሱ
ፍፁም አገዛዝ የነበረው ከ24 ሰኔ እስከ ታህሣሥ 1948 ብቻ ነበር::
ከዚያ በኋላ በገዥው መደብ ረድፎች ውስጥ ኃይልና ቀውስ ነበር:: ይህንን
ዝቅ ብለን የቦናፖርት ኃይል አጨባበጥና ትርጉሙን ስንመለከት እንመጣበታ
ለን::

የሪፐብሊክ ከበርቴው አገዛዝ በነበረበት ወቅት የብሄራዊ ሕገ
ረቂቅ ወጣ፣ የከበርቴ "ዲሞክራሲያዊ" ነፃነቶች ተሰጡ:: ዝቅ ብለን
ስለ ቦናፖርት የፖለቲካ ኃይል መጨበጥና "ቦናፖርቲስት ሬዥም" /ቦናፖ
ርቲስት አገዛዝ/ የተባለውን ምንነት እንረዳ ዘንድ፣ አስቀድመን እዚህ ላይ
በወጣው ኮንስቲቱሽን ውስጥ ያለውን ኃይል አከፋፈልና የጠቅላላው የሕጉን
አሠራር በቀላሉ በአጭሩ እናስቀምጥ::

እንደሚታወቀው በዘው የከበርቴ ኮንስቲቱሽን ውስጥ ያለ መሰካዊ
የኃይል ክፍፍል ሁለት አጠቃላይ አካሎችን የያዘ ነው:: "የኮንስቲቱሽናል
የኃይል ክፍፍል ጨዋታ" ይለዋል ማርክስ:: ሀ/ ሕግ አውጭው አካል/ሌጂ
ስላቲቭ/ ፖርላማውንና ከእርሱ ጋር የተያያዙትን ኢንስቲትዩሽኖችን ያጠቃ
ልላል:: ለ/ ሕግ አስፈጻሚው በሕግ አውጭው "የሚወጣውን" የሚያስ
ፈጽምና ጠቅላላ ሃገሪቷን የሚመራው አካል ፕሬዚዳንቱ /በየቦታው የተለያየ
ስም ይሰጠዋል/ና ሚኒስቴሪው ጠቅላላ ከዚህ ጋር የሚያያዙት ኢንስቲትዩሽኖች
ናቸው:: እንደ ጦር ኃይል፣ ቢሮክራሲው ፖሊሱ ወዘተ..ያሉትን ሁሉ ያጠ
ቃልላል::



በፈረንሣይ ያኑ የወጣውም በመሠረቱ ይህንን መልክ የያዘ ነው::
ሀ/ ሕግ አውጭው /ኃይል/ አካል ፣ ብሄራዊ ሸንጎ፣ ለ/ ሕግ አስፈጻሚው
የብሄሩ ፕሬዝዳንት:: ከነዚህ በሁለቱ አካሎች መሃል ያለው ግንኙነት በጣም
የተወሳሰበና የሚያረገ፣ ነገር ግን ግንኙነቱ የተወሰነው፣ ሥርዓቱ የመንከታ
ከት አደጋ ላይ በሚደርስበት ጊዜ፣ /ለምሳሌ የጭቆት ትግል ሲያይል/
ከዚህ መንከታከት አንደኛው ኃይል ሥርዓቱን ለማዳን እንደሚቆከር ተደርጉ ነው
ለማለት ይቻላል::

ብሄራዊ ሸንጎ የተባለው፣ ሕግ አውጪው አካል "የሕዝብ ወኪሎች"
ከተመረጡ በኋላ በምንም ዓይነት ዘዴ በሕዝቡ ቁጥጥር ሥር የማይውሉ፣ ቢፈ
ልጉ በጦርነት፣ በሰላምም ሆነ በማንኛውም የሃገር ጉዳይ ላይ ሊወስኑ የሚችሉ
ናቸው:: ሕግ አስፈጻሚው አካል፣ የብሄሩ ፕሬዝዳንትም እንደ ብሄራዊው ሸንጎ
ይመረጣል::"ንጉሣዊ" ኃይል አለው ለማለት ይቻላል:: ከብሄራዊው ሸንጎ
ቁጥጥር ውጭ በሆነ መንገዱ በጠቅላላው ቢሮክራሲው፣ የጦር ኃይሉ፣ በሚኒስትሩ
ወዘተ.. ሊገለገል ይችላል:: በነዚህ ሁለት አካሎች መሃከል ያለውን ግንኙነ
ትና ቅራኔ ሲያሳይ ማርክስ "ብሄራዊ ሸንጎው ፕሬዚዳንቱን ሕጋዊ በሆነ መን
ገዱ ብቻ ሊያስወግዱ ይችላል፣ ፕሬዝዳንቱ ግን ብሄራዊ ሸንጎውን ሕገ ወጥ
በሆነ መንገዱ ከሥራ ወጭ ሊያደርገው ይችላል፣ ይህም እራሱ ሕጉን በማስወገዱ፣
በመሰረዝ ነው" ይላል::

<u>የቦናፖርት ኃይል አጨባበጥ</u>

ቦናፖርት "ሕጋዊ" በሆነ መንገዱ በታህሣሥ 10 1848 ተመረጠ::
ይህ ምርጫ የተካሄደው ኃይለኛ የመደብ ትግል ከአከተመ በኋላ ነው::በሪፖብ
ሊካኑ ከበርቴ መሪነት ከፍ ብለን የጠቀስናቸው መደቦችና የህብረሰብ ክፍሎች
/ከፋይናንስ አሪስቶክራሲው እንስቶ እስከ ገበሬው ድረስ ያሉት/ የወዝአደሩን
የሰኔ ተጋድሎ ከአከሸፉ በኋላ ነው:: ከዚህ ወዲህ በሕግ አውጪው አካል ውስጥ
የነበሩት የገዥ መደቦች ወኪሎች ውስጥ ጠንካራ ትግል ነበር::ሪፖብሊካኑ ከበ
ርቴ የራሱን ሪፐብሊክ እንደመሠረተ በብሄራዊው ሸንጎው ውስጥም ሆነ በህብረሰቡ
ውስጥ ያለው ተፅዕኖ እየወደቀ ሄደ:: ከዚያ የነበረው ዋና ትግል በኦርሊያኒ
ስቶች/ Orleanists /፣ሌጂትሚስቶች/ Legitimists /በተባሉት የከበ
ርቴ ኃይሎች ውስጥ ነበር:: ኦርሊያኒስቶች የኦርሊያን ዲናስቲ ደጋፊዎች ነበ
ሩ:: አሁን ግን የሚወክሉት የፋይናንስ አሪስቶክራሲውንና የኢንዱስትሪ ትልቁ
ከበርቴን ነው:: ሌጂትሚስቶች የቡርቦን ዲናስቲ ደጋፊዎች ነበሩ:: የሚወክሉት
የትላልቅ ባለመሬቶችን ጥቅም ነው:: የቦናፖርት ደጋፊዎች የሚባሉት እሉ::
እዚህ የወኪል ዝርዝር ውስጥ መግባት አያስፈልገም:: የየትኛው ገዥ መደቦች
ክፍሎች ጥቅም እንደተወከለ መጥቀሱ ነው የሚያስፈልገው::

ከሰኔው የወዛደር ትግል በኋላ፣ የትልቁ ከበርቴ /በኦርሊያኒስቶችና ሌጂቲሚስቶች የተወከሉት/ የሚቀጥለው ሊጎማ ሪፐብሊካኑ ከበርቴ ነበር:: የህብረተሰቡ የዕድገት ደረጃ እዚህ ከደረሰ በኋላ፣ ሪፐብሊኩ ከተመሠረተ ወዲህ የመሬት ከበርቴውና ትልቁ የኢንዱስትሪ ከበርቴ በአንድነት ሊገዙ የሚችሉበት የመንግሥት ዓይነት አገኙተዋል:: ማርክስ የነዚህን አንድነት ሲያወሳ "ሁለቱንም አንድ የሚያደርጋቸው የካፒታል አገዛዝ ነው" ይላል::

በብሄራዊው ሸንጎ ውስጥ የነበረው ትግል ከዚያም በጠቅላላ በገዥው መደቦች ውስጥ የነበረው ቀውስ በመጀመሪያ የሪፐብሊካኖችን መውጣት አስከተለ:: ሪፐብሊካን ከበርቴው ከብሄራዊው ሸንጎ ከተወገደ በኋላም ግን የነበረው ቀውስ አለጠፋም:: ሊጠፋም አይችልም ነበር:: ጠቅላላው ከበርቴ በብሄራዊው ሸንጎ ውስጥ በሁለት ትላልቅ የጥቅም አካሎች ተከፍሎ ነበር:: የመሬት ከበርቴውና የኢንዱስትሪ ካፒታል:: እነዚህ ሁለት የጥቅም ኃይሎች በአንድነት ሊገዙ የሚችሉበት የከበርቴው ሥርዓት መሆኑን አውቀዋል:: በማሃላቸው ግን ኃይለኛ የጥቅም ግጭት አለ:: በውስጣቸው ያለው ቀውስና ግጭት ደግሞ ጠቅላላ ሥርዓቱን "አደጋ" ላይ የሚጥለው ሆነ:: ይህ በሕግ አውጭው አካል ውስጥ ያለው የጥቅም ቅራኔ ከሕግ አስፈጻሚው ጋርም ቅራኔ ውስጥ አስገባቸው:: በሕግ አስፈጻሚውና በሕግ አውጭው አካል መካከል ያለው ቅራኔ እየከረረ መሄዱ ከፍ ብለን እንዳሳየነው እራሱ ሕጉ "በሚፈቅደው መሠረት" የሕግ አስፈጻሚው አለቃ ፕሬዝዳንቱ ሕግ አውጭው አካልን ከሥራ ውጭ አደረገው::

ቦናፓርት በጥር 30 1849 ጠቅላላ ብሄራዊ ሸንጎውን በተነው:: የመጀመሪያው ዐርምጃ ነበር:: ከዚያ የምርጫ መብት በጠቅላላው ተወገደ:: ብዙ ሌሎችም ሕጎች ተከታተሉ:: በሁለቱ አካሎች መካከል የነበረው መለኪያ የኃይል ክፍፍል እየተወገደ፣ ሕግ አስፈጻሚው ሕግ አውጭም ሆነ::በህብረተሰቡ ውስጥ "ሰላም" እንዲሰፍንና ሥርዓቱ "አደጋ" ላይ እንዳይወድቅ፣ /ፓርላማው፣ ሕግ አውጭው አካል/ ብሄራዊው ሸንጎ ውስጥ ባሉ በገዥ መደብ ረድፎች መካከል ያለው ቀውስ ሲከር፣ ፓርላማውን ፀጥ የሚያሰኝ ማስፈለጉን ሁሉም ያምናሉ:: የከበርቴውን አጠቃላይ የኤኮኖሚ ጥቅም የሚያስጠብቅ፣ የተለያዩ ገውስ ጥቅሞችን ግን በኃይል የሚያስማማ መገኘቱ ለጠቅላላው የከበርቴ መደብ ጥቅም መሆኑ ለሁሉም ግልጽ ነው::

<u>ቦናፓርትና ድርጅቱ</u>

የቦናፓርትን ትግል ዋና የሚያንቀሳቅስ የነበረው "Society of Dec. 10" የተባለው፣ ቦናፓርት ከተመረጠበት ጀምሮ ይሠራ የነበረው ድርጅት ነው:: ይህ ድርጅት በየአካባቢው በቦናፓርት ሰላዮች አማካይነት የተደራጁ አካሎች ነበሩት:: የዚህ ድርጅት ደጋፊዎች በዝነውና ከዚያም በህብረተሰቡ ውስጥ ያሉት መደቦችና የህብረተሰብ ክፍሎች ዝቃጭን / Declassed Elements / ሁሉ ያጠቃልላል:: በማርክስ አነጋገር:-



"...the lumpenproletariat of Paris had been organised into secret sections, each section being led by Bonapartist agents, with a Bonapartist general at the head of the whole. Alongside decayed roués with dubious means of subsistence and of dubious origin, alongside ruined and adventurous offshoots of the bourgeoisie, were vagabonds, discharged soldiers, discharged jailbirds, escaped galley slaves, swindlers, mountebanks, lazzaroni, pickpockets, tricksters, gamblers, maquereaus, brothel keepers, porters, literati, organ-grinders, ragpickers, knife grinders, tinkers, beggars — in short, the whole indefinite, disintegrated mass, thrown hither and thither, which the French term la bohême; from this kindred element Bonaparte formed the core of the society of December 10...This Bonaparte, who constitutes himself chief of the lumpenproletariat, who here alone rediscovers in mass form the interests which he personally pursues, who recognises in this scum, offal, refuse of all classes the only class upon which he can base himself unconditionally, is the real Bonaparte, the Bonaparte sans phrase."

የቦናፓርት ድርጅት "ከቢፃቱ ት ዲብ ዲባንበር" የሚባለው ከየመደቡ ሁሉ የተወጣጡ የየመደቡ ዝቃጮች ናቸው ማለት ነው::ይህ ድርጅት ጠቅላላ የቦናፓርትን ዝናና ትልቅነት የሚያስፋፋ መካከላዊ አካል ነው እንጂ ቦናፓርት ሃይሉ ቢጨብጥ ሌሎች የደገፉት የሉም ማለት አይደለም::ለምሳሌ ቦናፓርት በብሔራዊው ሸንጎ ጋር ያለው ቅራኔ —በህግ አስፈጻሚውና አውጭው አካል መካከል— ቢፋፋም ህግ አስፈጻሚው አካል /ቦናፓርት/ ሃይሉን እንዲጠቀልል የ"ሥነ ሥርዓት ፓርቲ" የሚባለው ደግፎት ነበር::በብሄራዊው ሸንጎና በህግ አስፈጻሚው አካል ያለው ቅራኔ በከረረበት ወቅት፣ጠቅላላ በገዥ መደቦች ውስጥ የነበረው ቀውስ በተፋፋመበት ጊዜ፣ባላቸው ቅራኔና የጥቅም ግጭት ለመገዛት ባቃታቸው ወቅት፣ሥርዓቱ ከመውደቅ እንዲድንለት የከበርቴው መደብ እንዳለ ደግፎታል::ዝቅ ብለን እንመለከታለን::ሆኖም ይህ declassed የሆኑ የህብረተሰቡ ንጥር ነገሮችን የሚያጠቃልለው የምስጢር ድርጅት መካከላዊ ቦታውን ይዟል::

በአጠቃላይ በከበርቴ ሥርዓት ውስጥ ስለአለው መለካዉ የሃይል ክፍፍልና ግንኙነት ስናወሳ ህግ አስፈጻሚው አካል —ፕሬዚዳንቱ— ጠቅላላ የጦር ሃይሉና ቢሮክራሲው በቀጥተኛ ስር እንደሆኑ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች እንደሚያዝ አይተናል፡፡ቦናፓርት ከበጤራዊ ሸንጎው ጋር ባለው ቅራኔ ጦር ሃይሉንና ቢሮክራሲውን በጣም ሊገለገልበት ችሏል፡፡ጦር ሃይሉብጥም ሆነ ቢሮክራሲው ውስጥ የሮሙ ሃይሎች ስር ገው እንዲገቡ በማድረግና፣በቱጫሪም ሊያዘባቸው ስለሚችል /ህጋዊ በሆነ መንገድም በቀጥተኛ ስር ስለአሉ፣ህጉ ራሱ ስለሚፈቅድ/ በራሱ ድርጅት አካባቢ ሊሰበስባቸው ችሏል፡፡ህግ አውጭውና አስፈጻሚው አካሎች እሳትና ጭድ በሆኑበት ሰዓት ፡በጦር ሃይሉና በቢሮክራሲው አማካይነት፣በ"ሶሲዬቴ ዱ ዲስ ዲሳንበር" አደራጅነት፣"ህጉን ኢገወጥ በሆነ መንገድ" ለማጥፋትና ህግ አስፈጻሚውን ከጠቅላላው ህብረ ሰብ ለመገንጠል ማገናውም የፖለቲካ የስሽልና የኢኮኖሚ ውሳኔዎች ቦናፓርት ለብቻው ለመውሰድ ችሏል፡፡

ቦናፓርትና የገዢው መደቦች

ፓርላማ ውስጥ በገዢ መደቦች መካከል ያለው ትግልና ቅራኔ ቢፋፋም "ሰላም ማጣቱ" ጠቅላላ ከበርቴውን ከመጠን በላይ ስለአስጨነቀው ጥሪውን "አንድ ጠንካራ" መንግሥት ይምጣና ሰላምና ስርዓት ሰጥቶን እንገላገል ነበር፡፡ ቦናፓርት ፓርላማውን ከስራ ውጭ ካደረገ በኋላ፣ያ ሁሉ በገዢ መደቦች መካከል የነበረው ውጥንቅጥ ተወግዶ ሁሉም ድጋፋቸውን ለእርሱ ሰጡ፡፡በፋይናንስ አሪስቶክራሲውና በኢንዱስትሪ ከበርቴው መካከል የነበረው ቅራኔ ጠፋ ማለት አይደለም፡፡ሆኖም ባላቸው ቅራኔ ለመግዛት ባለመቻላቸው፣ሁሉም የቆመበት ስርዓት እንዳይሰበር የሚጠብቃቸው ሃይል ማስፈለጉን በመረዳት ቦናፓርትን ደገፉ፡፡በህግ አስፈጻሚው አካል ፈላጭ ቆራጭነት መግዛትን መረጡ፡፡

የቦናፓርት ድልና የህግ አስፈጻሚው ፈላጭ ቆራጭ መሆን እራሱን ከህብረሰቡ መገንጠል ምን ትርጉም አለው? ምንም እንኳን በመሃላቸው ሃይለኛ ቅራኔ ቢኖራቸው ገዥ መደቦች ባንድነት ይህን ሂደት መደገፍ ምን ትርጉም አለው?

ጠቅላላ ህብረሰቡ የደረሰበት ደረጃ ሆነ ከዚያም በፊትና በኋላ በጭቁን መደቦችና የህብረሰብ ክፍሎች የተደረገው ትግል ውጤት፣የባላባታዊው መደብ ርዝራዦችና ከበርቴው በከበርቴው ሥርዓት ላይ እንዲስማሙ አድርጓቸዋል፡፡ለምሳሌ የሰኔውን የወዛደር ትግል በአንድነት ሆነው ከደመሰሱ ወዲህ ተስማምተው የነበሩበት የሥርዓት አይነት የከበርቴው ሬፑብሊክ ነበር፡፡ሌላም ምርጫ አልነበራቸውም፡፡ሬፑብሊኩን ከመሠረቱ በኋላ የፋይናንስ አሪስቶክራሲውና የትልቁ ከበርቴ ወገኖች ይታገሉ የነበሩት ሬፑብሊክ ከበርቴውን ነበር፡፡ከዚህ በኋላ ግን በመካከላቸው ይታይ የነበረውን ቅራኔ "በአንድ በኩል በመሬት ካፒታልና በሌላ በኩል በኢንዱስትሪ ካፒታል" መካከል ያለውን ያንጸባርቅ ነበር፡፡አንድ የሚ



ያደርጋቸው ነገር ግን ሁሉም በካፒታል አገዛዝ ላይ መስማማታቸው ነው፡፡በዚህ አገዛዝ ላይ "አደጋ" ሲመጣ አንድነታቸው የጠበቀ ነው፡፡በመሃላቸው ባለው የጥቅም ግጭት እሳትና ጭድ ቢሆኑ ለመግዛት ሲሳናቸው፣እንደ ቦናፓርት አይነት እንዲገዛቸው ሃይላቸውን አሳልፈው ይሰጣሉ፡፡ይህ ባለው ሃይልና ጉልበት /ጦር ሃይል ወዘተ/ በገዢ መደቦች መካከል "ሰላም" አሰፍኖላቸው የተስማሙበት የከበርቴ ሥርዓት እንዲሠራ ያደርጋል፡፡በዚህ የቦናፓርት ሃይል ስር የሚንቀሳቀሰው ሥርዓት የከበርቴው ሥርዓት አንደኛው አይነት ነው፡፡በአንዳንድ የቦናፓርቲዝም ተርጓሚዎች እንደሚባለው፣ቦናፓርቲዝም፣ወደ ኋላ የቀረውን የፊውዳል ሥርዓትን ከታዳጊው የከበርቴው ሥርዓት ጋር የሚያዳብል ወይንም ሁለቱን ጎን ለጎን የሚያኖር ሊሆን አይችልም፡፡ለዚህም ነው ማርክስ:—

> **"The bourgeoisie is always inclined to sacrifice its general interest of his class interest (political interest)for this or that private interest."**

ያለው፡፡ የ"ግል ጥቅሙን" ደግሞ የሚጠበቅለት የከበርቴው ሥርዓት ማህበር ካልሆነ ሌላ ሊሆን አይችልም፡፡በየብቻው ማርክስ የሚያነሳው የፖለቲካ ጥቅም —በህግ አውጭውና በህግ አስፈጻሚው መካከል ባለው ትግል ውስጥ— ከበርቴው የህግ አስፈጻሚውን ፈላጭ ቆራጭነት መቀበሉንና ለእነ ቦናፓርት አይነት ሃይል ተገዢነቱን ለመጥቀስ ነው፡፡

የግል የኢኮኖሚ ጥቅም የሚነካ የፖለቲካ ሃይል ቢነኖቀው፣የካፒታል አገዛዙን የሚደመስስ ሃይል ከፖለቲካ መድረክ ሊያባርረው ቢነሳ ግን እስከ መጨረሻው የደም ጠብታ ድረስ ከበርቴው ለመታገል እንደሚፍጨረጨር ግልጽ ነው፡፡ የቦናፓርት ሃይል መጨበጥ ከዚህ ጋር እንደ ሰማይና ምድር የተራራቀ ነው፡፡ የካፒታል አገዛዝ ለማውደም ሳይሆን እንዲያውም የከበርቴውን አገዛዝ ከውድቀት ለማዳን ነበር፡፡ የካፒታል አገዛዝ ላይ አንድነት ያላቸው ሃይሎች በሙሉ /ከፋይናንስ አሪስቶክራሲው እስከ ኢንዱስትሪ ከበርቴው/ የወዝ አደሩን እንቅስቃሴ በተለይ የሰኔውን ትግል ከደመሰሱ በኋላ፣በራሳቸው ውስጥ ያለው ቀውስ፣የጥቅም ቅራኔ በአንድነት እንዲገዙ አላደረጋቸውም፡፡ይህ ቀውስ ግን የጠቅላላ አገዛዙን መቀየት "አደጋ" ላይ ጥሎት ስለነበረ የፖለቲካ ሃይላቸውን የሚደመስስ፣የህብረሰባዊ የኢኮኖሚ በዝበዛቸውን ግን የሚያጸድቅላቸው ሃይል ላይ መስማማት ተገደው ነበር፡፡ ይህ ሃይል ከጠቅላላው ቢሮክራሲው፣በጦር ሃይሉ ላይ የሚያዘው ህግ አስፈጻሚው አካል ሆኖ አገኙት፡፡ይህ አካል ከህግ አውጭው አካል እራሱን ነፃ ለማድረግና በፈላጭ ቆራጭነት እንዲገዛ በመጨረሻ ሊያደርገው ያስቻለው ይኸው በገዢ መደቦች ውስጥ ያለው ሃይለኛ ቀውስ ነው፡፡

## የቦናፓርት መንግሥት ህብረሰባዊ መሠረት /ሶሸል ቤዚስ/

ማርክስ ገና በጽሑፉ መግቢያ ላይ ቢጸፍ በበዙዎቹ ላይ ያየው ስህተት ሌሎች ስለፈረንሳይ ሁኔታ ሲዘረዝሩና ሲጻፉ ከነበረው የመደብ ትግል አንጻር ህብረሰቡ ያለበትን ታሪካዊ ደረጃ በመመርመር የቦናፓርትን ህዝባዊ መሠረትንም አለማሳየት ነበር::ከፍ ብለን እንዳየነው ለቦናፓርት ሃይል መጨበጥ መካከሳዊ ሚና የተጫወተው፣ከመደቦቹ ሁሉ ዝቃጭ የሆኑትን የሚጠቀልለው "ሶሲዬቴ ዱ ዲስ ዴሳንበር" የተባለው ሚስጥራዊ ድርጅት ነው::በተለይ በተጨቆኑ መደቦችና የህብረሰብ ክፍሎች ውስጥ ለቦናፓርት ድጋፍ ለማስገኘት የተጫወተው ሚና እጅግ ከፍተኛ ነበር::በወዝ አደሩ፣በንዑስ ከበርቴው በተለይ ደግሞ በገበሬው ውስጥ:: የቦናፓርትን መንግሥት ህዝባዊ መሠረት እንመለከት::ከማርክስ ሁለት ነገር በመጀመሪያ እንጥቀስ:—

> "The french bourgeoisie balked at the domination of the working proletariat,it has brought,with the chief of the Society of December 10 at the head."

ማርክስ ያኔ የነበረውን የመደብ ትግል፣ከዚያም በህግ አስፈጻሚውና በህግ አውጪው አካል መካከል የተካሄደውን ትግል የመንግሥትን /ስቴት/ ከህብረሰቡ ፍጹም ነፃ መሆኑን እንዳስከተለ /the state machine consolidating its position and becoming independent from the Civil Society/ ከገለጸ በኋላ:—"...And yet the state power is not suspended in

> mid air.Bonaparte represents a class,and the most numerous class of french society at that, the small holding pesants"

ይላል::

ከነዚህ ነጥቦች ሁለት—ሦስት ፍሬ ነገሮች ለማውጣት ይቻላል::

ሀ/ የፈረንሳይ ከበርቴ—ሥርዓተ ማህበሩ ከውድቀት እንዲድንለት— የኢኮኖሚው ዘረፋ በህብረሰቡ ውስጥ ያለው የበዝባዥ ጥቅም እንዲቀይለት፣በውስጡ ባለው ቅራኔ እርሱ ራሱ ለመግዛት ባይችል ቢቀር ሊገዛ የሚችል "አስታራቂ" ሃይል እንዲጨብጥ ማድረግ ነው::

ለ/ ይህን የሚያደርገው አሁኑ ገዢ የከበርቴውን መሠረታዊ የመደብ ጥቅም የፖለቲካ አገዛዙን እንደማይጋፋ በመረዳቱ ነው:: የ"ለምፔን ፕሮሌታሪያት አገዛዝ" ይለዋል ማርክስ::ስካራሙ፣ሌባው ወዘተ ከሁሉም መደብ የተተፉ ዝቃጮችን የሚያጠቃልል ድርጅት እንኳን በቀላሉ የፖለቲካ ሃይል ለመጨበጥ የቻለበት ምክንያት አለው:: የመንግሥት መዋቅራዊው —ከነቢሮክራሲው — የጦር ሃይሉ ወዘተ ከህብረሰቡ እራሱን ገንጥሎ ስለ ነበር ነው:: ቀደም ሲል በህግ አስፈጻሚው አካልና በህግ አውጭው መካከል የነበረው የትግል ውጤት ነው::



ሐ/ በዚህ ሁኔታ የፖለቲካ ሃይል የጨበጠው ቦናፓርት የሚወክለው የህብረሰብ ክፍል አለ:: የቦናፓርት መንግሥት ህብረሰባዊ መሠረት፣በመጀመሪያው የፈረንሳይ አብዮት ያገኘው "መሬቱ ይነጠቀብናል" ብሎ የሚለፍፈው አድሃሪው "ባለ ትናንሽ መሬት" ገበሬ ነው::

ከላይ ያመለከትናቸው ነጥቦች የሚቃረኑ ይመስላሉ::ባንድ በኩል የቦናፓርት መንግሥት የካፒታል አገዛዝን ያፀና ነው:: የከበርቴ አገዛዝ አንድ አይነት ነው::በሌላ በኩል ደግሞ የዚህ መንግሥት ህብረሰባዊ መሠረት ባለትናንሽ መሬት ገበሬ ነው::ይሄ የሚቃረን ይመስላል::ግን ፍጹም አይቃረንም:: የቦናፓርት መንግሥት የከበርቴ አገዛዝን፣የካፒታል አገዛዝን ያፀና መሆኑ በነበር የዚህን ጥቅም መጠበቅ ህብረሰቡ እራሱ የደረሰበት ታሪካዊ ደረጃ ነው::አንድ ህብረሰብ የካፒታሊስት ሥርዓተ ማህበር ከደረሰ በኋላ ወደ ኋላ ወደ ባላባታዊ ሥርዓት ሊመለስ አይችልም::እርግጥ ተፀዕኖዎች ርዝራዦች ሊቀሩ ይችላሉ:: የዐርባታ ሃይሎች ግን፣ወይ የእድገታቸው ፍጥነት ይቀንሳል፣ወይ ከዐርባታ ግንኙነቶች ጋር ባለው ቅራኔ ዕድገታቸው ይታፈናል እንጂ፣በአጠቃላይ ወደ ኋላ አይመለሱም:: የመጀመሪያው የሚያበየው /የካፒታል አገዛዝን ቦናፓርት ማፅኑ/ ይኸንን ነው::

ፈረንሳይ ያኔ ስለደረሰችበት ታሪካዊ ደረጃ ማርክስ ሲናገር:—"በመጀመሪያው የፈረንሳይ አብዮት፣ መሬት ለገበሬዎች መከፋፈል /በናፖሊዮን/፣በገጠር ነፃ ውድድርን /የውድድር ካፒታሊዝም/፣በከተማ ደግሞ የተሳሰቀ ኢንዱስትሪዎች ብቅ ብቅ ማለትን አስከትሉ ነበር::መሬት ለገበሬው መከፋፈሉ ትርጉም የፊውዳል አገዛዝን ደም ስሮች መበጠስ ነበር::" ይላል::በቦናፓርት ጊዜ ግን የካፒታል አገዛዝ የባላባቶን አገዛዝ ተክቶት ነበር::ገበሬው ግን የጥንቱ ናፖሊዮን ትዝ እያለው /መሬት የሰጠው/ የአሁኑ ቦናፓርት ደግሞ የተሰጠውን መሬት የሚከላከልለት ይመስለው ነበር::ባለትናንሽ መሬቶቹ በካፒታል አገዛዝ ስር መሆናቸውን ቦናፓርትም የገበሬዎቹን መበዝበዝ የሚያካሄድ አለመሰላቸውም::አይረዱም::

እንግዲህ በዚያን ጊዜ ከህብረሰቡ /ሲቪል ሶሳይቲ/ እራሱን የገነጠለው የመንግሥት ሃይል ህብረሰባዊ መሠረት ገበሬው ያውም አድሃሪው ነው ሲባል የነዚህን የመደብ ጥቅም የሚጠብቅ ሃይል ነው ማለት ሳይሆን የቦናፓርቲዝም ህብረሰባዊ—ተሸካሚ ሃይል ነው ማለት ነው::እዚህ ላይ ደግሞ ከሁሉም ይበልጥ መታየት ያለበት ህብረሰቡ የደረሰበት ታሪካዊ ደረጃ ነው::

<u>ማጠቃለያ</u>

ስለ ቦናፓርቲዝም ምንነት ለማወቅና አንድን መንግሥት ቦናፓርቲስት ነው ለማለት ከማርክስ የምናገኘው ትምህርት:—

1ኛ/አንድ ህብረሰብ ያለበትን ስርዓተ ማህበር መመርመርና በጨቋኝና በተጨቋኝ መደቦች ሆነ በራሳቸው በገዥ መደቦች ውስጥ ያለውን ትግል ማየት፣

2ኛ/ የዚህ የሚመረመረው መንግሥት ህዝባዊ መሠረት ምን እንደሆነ ህብረተሰቡ ከደረሰበት ታሪካዊ ደረጃ ጋር በማዛመድ ማወቅ፣

3ኛ/ይህ መንግሥት የማንን መደብህብረሰባዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም እንደሚጠብቅ ጠቅ ማስፈለጉን ነው::

እዚህ ላይ ትልቅ ልዩነት ማድረግ የሚያስፈልገዉ የፊውዳል ሥርዓተ ማህበርን ለማጥፋት የተነሳ የከበርቴ ሃይልንና የከበርቴ ሥርርዓት ማህበርን ከመንኮታኮት ለማዳን የተነሳ ሃይልን መለየት ነው::

አንድን መንግሥት ቦናፓርቲስት ነው ለማለት የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች:—

1ኛ/ አንድ ህብረሰብ የከበርቴ ሥርዓት ማህበር ደረጃ የደረሰ መሆኑ፣ የፊውዳል አገዛዝን የሰባበረበት ደረጃ መድረሱንና የውድድር ካፒታሊዝም ሰርጉ መግባትን፣

2ኛ/ ከፍተኛ የመደብ ትግል —በተለይ በወዝ አደሩና በከበርቴው ተካሄዶ— ወዝ አደሩ በገጠሙት የንቃትም ሆነ የድርጅት ድካም የከበርቴውን ሥርዓት መሰባበር አለመቻሉንና የከበርቴውም መደብ ውስጡ ባሉት ቅራኔዎች በመወጠር ተስማምቶ ለመግዛት ያልቻለበት ሁኔታ መኖርን፣

3ኛ/ በከበርቴ ሥርዓት ማህበር ውስጥ በዘውን ጊዜ የሚኖሩት የህግ አውጭውና የህግ አስፈጻሚው አካል ቅራኔ ውስጥ ገብቶ፣ የህግ አስፈጻሚውን ከቁጥጥር ውጭ መሆንን፣ፈሊጥ ቁራጭነትን ማስከተሉ፣የፖለቲካ ሃይል ጠቅላላ በአንድ በተወሰነ ሃይል ገብቶ በገዥ መደቦች ውስጥ ተደማጭነት ኖሮት ያላቸውን ቅራኔ አፍኖ የበዝበዛ ሥርዓታቸውን የካፒታል አገዛዝን የሚያረጋግጥ መፈጠር ይጠይቃል::

እዚህ ላይ ዋና መገንዘብ የሚያስፈልገው አንድ ቦናፓርቲስት መንግሥት የከበርቴ ሥርዓትን የሚያድን ካልሆነም ቢያንስ የባላባቶ መደብ በካፒታሊስት ዕርባታ ዘዴዎች እንዲጠቀም የሚያስገድድ ሃይል መሆኑን ነው::/እዚህ ላይ የቢስማርክን ሚና በጀርመን ለመውሰድ ይቻላል/ማርክስ ስለ ቦናፓርት ሲጽፍ በየቦታው፣ከመጀመሪያው የፈረንሳይ አብዮት ጋር የሚያነፃፅረው ይህን ፍሬ ነገር ለማሳየት ነው::ምንም እንኳን የመጀመሪያዉ የፈረንሳይ አብዮት ያስከተለውም ሆነ የቦናፓርት —ሁለቱም የከበርቴ መንግሥት ቢሆኑም፣ የመጀመሪያው ከታሪካዊ



የህብረሰቡ ሥርዓተ ማህበር እድገት ደረጃ ጋር ሲተያይ ወደኋላ የቀረውን የፊውዳል ሥርዓት የገረሰሰ፣የደመሰሰ፣ ስለዚህም የነበረውን ታሪካዊ ተራማጅ በታ ለማሳየትና ሁለተኛው የቦናፓርት ሚና አድሃሪነትን ለማመልከት ነው::ቦናፓርት መውደቅ የሚገባውን የከበርቴ ሥርዓት ያዳነ ነው::

——— xxx ———

## ስለ ጊዜያዊ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሁኔታና ፋሺዝም የውይይት ነጥብ

በሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ውስጥ ካለው መሠረታዊ ቅራኔ ተነስተን ፋሺዝም በክላሲካል መልኩ ምን እንደሆነ፤ የማን ሃይል እንደሆነ ወዘተ በአጠቃላይ ለማሳየት ሞክረናል:: እንግዲህ ፋሺዝም የሚታየው ወይንም የሚወጣው በኢምፔሪያሊስት አገሮች ውስጥ ብቻ ነው ማለት ነው? የፋሺዝምስ አደጋ ያለው በኢምፔሪያሊስት አገሮች ውስጥ ብቻ ነው ማለት ነው? መልሱ አይደለም ነው:: ፋሺስታዊ መንግሥታት በግማሽ ፊውዳልና ግማሽ ካፒታሊስት አገሮች ወይንም ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ደረጃ ላይ ያልደረሱ ሥርዓተ ማህበሮች ውስጥ ሊመሠረቱ ይችላሉ:: ነገር ግን ከክላሲካል ፋሺዝም ዓይነተኛ ልዩነት አላቸው::

እዚህም ለመድገም 7ኛው የኮሙኒስት ኢንተርናሽናል ጉባዔ ስለ ፋሺዝም ምንነት ሙሉ ሳይንሳዊ ውጤት ላይ ሊደርስ የቻለው ከሁሉም ፋሺዝም በጠራ መልኩ በጀርመን ውስጥ ሃይል ከጨበጠ ወዲህ ከመረመረ በኋላ ነው:: በሌሎች የሞኖፖሊ ካፒታሊዝም የኢኮኖሚ መዋቅር ደረጃ ላይ ባልደረሱ አገሮች ውስጥ ስለ ፋሺዝም በአሁኑ የአለም ሁኔታ ስንነጋገር መሠረታዊ አድርገን የምንወስደው አለም አቀፋዊ ፋይናንስ ካፒታል ከየአገዛዙ ጋር ያለውን ግንኙነት ነው:: ግማሽ ካፒታሊስት ግማሽ ፊውዳል በሆኑ አገሮች ውስጥ ስለ ፋሺስታዊ መንግሥታት የሚነገረው በዚህ አገባብ ነው እንጂ በጀርመን ሆነ በጣሊያን የነበረው ፋሺዝም የኢኮኖሚ፤ የፖለቲካና የሶሺያል መሠረት ስለሚገኝ አይደለም:: ይህን ያልተረዳ በተለይ ስለፋሺዝም ሆነ በአጠቃላይ ስለ ታሪካዊ ማቴሪያሊዝም ሀ ሁ ያልቆጠረ ብቻ ነው::

በግማሽ ፊውዳልና ግማሽ ካፒታሊስት ሥርዓተ ማህበሮች ውስጥ ያሉት ገዢና ጨቋኝ መደቦች ፤ የፊውዳሉ መደብ ፤ ቢሮክራቲክ ከበርቴውና ኮምፕራዶር /ጥገኛ/ ከበርቴው ናቸው:: ኢምፔሪያሊዝም አለምን ተከፋፍሎ በዘበዛውን በዘረጋበት አካባቢ ከነዚህ መደቦች ጋር አንድነት መሥርቶ እንደሚጨቁንና እንደሚገዛ የታወቀ ነው:: በተለያየ ሁኔታና ጊዜ ከነዚህ ሦሥት ገዢ መደቦች ውስጥ አንዱ የበላይነትን ይይዛል:: ይህ የሚወሰነው ባላቸው የኢኮኖሚ ሃይል ፤ ህብረሰቡ ውስጥ ባሉት ቅራኔዎች ፤ የመደብ ትግል ወዘተ ነው:: ከኢምፔሪያሊዝም ጋር በጥብቅ የተሳሰረው የጋራ የኢኮኖሚ ጥቅምና ግንኙነት ያለው ኮምፕራዶር /ጥገኛ/ ከበርቴ ፤ ሁሉም በስምምነት ባንድነት ይገዛሉ:: ስምምነታቸው የሚጠነክረው ሰፊው ሕዝብ ከጭቆናው ለመላቀቅ አብዮታዊ ትግሉ በሚያደርግበት ወቅት ነው:: የሠፊው ሕዝብን አብዮታዊ ትግሉ ለመግታት ኢምፔሪያሊዝም ከነዚህ አድሃሪ መደቦች ጋር በመመሳጠር ፋሺስታዊ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝን ይጭኑበታል:: የዚህ ፋሺስታዊ አገዛዝ ዋና ተሸካሚና አንቀሳቃሽ ቢሮ ከበርቴው ነው:: በኢምፔሪያሊዝም ዋና አገልጋይነት የበሰበሰውን የመንግሥት መሣሪያ በመጠቀም የበሰበሰው ሥርዓት እንዲቆይ፤ የህብረሰቡን ታሪካዊ እድገት ለማፈን፤ ፋሺስታዊ አገዛዝን ያንቀሳቅሳል::



ስለፋሺስታዊ መንግሥት በ "ሦሥተኛ አለም" ውስጥ ሲነገር ከዚህ ከኢምፔሪያሊዝም ጋር ካለው ግንኙነት አንጻር ብቻ ነው:: ይህን ነጥብ በሰፊው ማብራራት የጥናታችን ክፍል ሁለት ይሆናል:: ጊዜና ሁኔታ ሲፈቅዱልን ወደፊት ለማቅረብ እናስባለን::

ይህ ጥናት ባጠቃላይ በሁለት ይከፈላል::

1ኛ/ የፋሺዝም ትርጉም በግማሽ ፊውዳልና ግማሽ ካፒታሊስት ሥርዓተ ማህበሮች ውስጥ በአሁኑ የዓለም ሁኔታ፤

2ኛ/ የኢትዮጵያ ጊዜያዊ ሁኔታና የፋሺስታዊ አገዛዝ አደጋ ከየትና በምን ዓይነት ሁኔታ::

ስለ አንደኛው ነጥብ ባጠቃላይ ቢሆን ፋሺስታዊ የሚባሉት አገዛዞች በምን ምክኒያት እንደሆነና እንዴት በቢሮ ከበርቴው አመራር ስር ጥገኛ ከበርቴውና የፊውዳሉ መደብ በሰፊውሕዝብ ላይ የሚጭኑት የጭቆና አገዛዝ /የሚሊቴሪ አገዛዝ ወይንም የሲቪል መልክ ሊወስዱ ይችላል — የኖርዶ ጥያቄ ነው/ እንዲሆን፤ ከክላሲካል ፋሺዝም ልዩነት እንዳለው ከፍ ብለን ጠቁመናል፤ እዚህም በዚህ እናበቃለን:: በደቡብ ቬየት ናም የነበረውን የቲዩ አገዛዝን፤ በኢንዶኔዢያ ፊሊፒን የመሳሰሉ አገሮች ውስጥ አሁን ያለውን ሁኔታ እንደምሳሌ መውሰድ ይቻላል::

ስለ ሁለተኛው ነጥብ ለጊዜው ለውይይት የሚሆኑ አንዳንድ ነጥቦች እዚህ ለማቅረብ እንፈልጋለን:: በዚህ በኩል ስለኢትዮጵያ ጊዜያዊ ሁኔታ የሚደረጉ የውይይት መነሻ ቢሆኑ ይጠቅማሉ::

I- * የየካቲት አብዮታዊ እንቅስቃሴ ኢኮኖሚያዊ መሠረት ምንድን ነው?
- * በየካቲት እንቅስቃሴ ወቅት የነበረው የመደብ ግንኙነት? የነቃ የተደራጀና የታጠቀ አብዮታዊ ሃይል ሳይኖር፤ የየካቲቱ እንቅስቃሴ በድሮው ሥርዓት ከልክ በላይ መበስበስ የተነሳ የፊውዳሉንና የከበርቴውን ቁንጮዎች አሽቀንጥሮ ለመጣል መቻሉ
- * የእንቅስቃሴው ውስንነትና ሰፊው ሕዝብ እንዴትና ለምን የፖለቲካ ሃይል ለመጨበጥ እንዳልቻለ
- * የደርግ ሃይል መጨበጥና ያደረገው እድገት? ደርግ ያደረገውን የእድገት ሂደት በሦሥት መክፈል:—
  - ሀ/ እስከ አማን አንዶምና የዱሮ ባለስልጣኖች መረሸን፤
  - ለ/ ከዚህ በኋላ ያለው ደርግና በውስጡ ያሉት ሃይሎች _ ከዚያ ያደረገው እድገት፤
  - ሐ/ ከመለስተኛ ፕሮግራም መታወጅ በኋላ ደርግ የሚኖረው ሚና::

II- ደርግና ቦናፓርቲዝም

* በመጀመሪያ ደረጃ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ሥርዓት በመፈረካከስ ላይ ያለ ፊውዳሊዝምና ግማሽ ከበርቴ ሥርዓት እንደሆነ ማወቅ፣

* ቦናፓርቲዝም የፊውዳል ሥርዓተ ማህበርን የሚያውን ወይንም በከፊል የሚያጠቃ ሳይሆን፣ የፊውዳል የኢኮኖሚ መሠረት ከተከባበረ በኋላ ዲሞክራሲያዊ አብዮታዊ እንቅስቃሴ በከፍተኛ ቆራጥነት ሲራመድ፣ የከበርቴ ሥርዓት ኢኮኖሚያዊና ህበረሰባዊ መሠረትን ለማደን የሚታይ እንደሆነ መረዳት፣

* በኢትዮጵያ ያለው ሁኔታ ገና የፊውዳል ሥርዓት ማህበርን ለመደምሰስ የሚራመድ ዲሞክራሲያዊ እንቅስቃሴ እንጂ ካፒታሊዝም ሙሉ በሙሉ ስር ገብቶ የካፒታልን አገዛዝ አደጋ ላይ የጣለበት አይደለም፣

* ደርግ በወሰዳቸው እርምጃዎች የማንን ጥቅም ይጠብቃል? በተለይ የመሬት አዋጅ መሬት የሌለውን መሬት እንዲኖረው የሚያደርግ ነው እንጂ /ከመጀመሪያው የፈረንሳይ አብዮት ጋር _ ከናፖሊዮን ጋር ይመሳሰላል እንጂ / ፣ የአንድ ቦናፓርቲስት "ረኝም" ህዝባዊ መሠረት የሚሆኑትን የ"ቁራጭ መሬት" ባለቤቶችን "ጥቅም የሚጠብቅ" አይደለም::

* በዚህ ሁኔታ ደርግ ቦናፓርቲስት መንግሥት መሥርቷል ለማለት ይቻላል ወይ? አይቻለም::

ሀ/ ኢትዮጵያ ገና የቡርዥዋ ዲሞክራቲክ አብዮት ደረጃ ላይ ናት:: አሁን ያለው ትግል እንቅስቃሴውን በወዝ አደሩ አመራር ከፍጻሜ ለማድረስ ነው::

ለ/ የደርግ ህበረሰባዊ መሠረት "ካለትናንሽ ቁራጭ መሬት" ባለቤቶች ባይሆኑ መሬት ለማግኘት የሚታገሉ "መሬት የለሾች" ሊሆኑ ይችላሉ:: እነዚህ መሬት የለሾች ደግሞ በዲሞክራሲያዊ አብዮት ውስጥ የወዝ አደሩ ዋና አጋር፣ የአብዮቱ ተሸካሚ ናቸው::

* ቦናፓርቲስት መንግሥት አሁን በኢትዮጵያ አለ የሚባለው ምንም ትርጉም የለውም:: ስለ ቦናፓርቲዝም ሲነገር የአንድ ሰው "ሃይለኛነት" መለኪዊ ትርጉም ብቻ አለው እንጂ ዋናው ይዘት አይደለም:: ዋናው የየትኛውን መደብ ጥቅም ይጠብቃል? ህዝባዊ መሠረቱ የትኛው የህብረሰብ ክፍል ነው? የሚለውን መመለስ ነው:: እንደያውም ባሁኑ ዘመን የኢምፔሪያሊዝም ጭቆና በተዘረጋባቸው ሥርዓቶች ውስጥ እንዳቸም ትርጉም አይኖረውም:: የቦናፓርቲስት መልክ የሚኖረው የፋሺስታዊ አገዛዝ ተሸካሚ የሆነው የቢሮ ከበርቴ አገዛዝ ይሆናል:: በኢትዮጵያ ያለው እንቅስቃሴ በወዝ አደሩ አመራር ስር ሳይሆን ቀርቶ፣ ከበርቴው የራሱን ሬፐብሊክ መሥርቶ፣ ትግሉ ግን ሲቀጥል የቦናፓርቲስት መልክ ያለው መንግሥት ሊመጣ ይችል ይሆናል:: ከአሁኑ ይህን አቀጣጫ ግን አይዘም ለማለት ይቻላል::



III- ፋሺስታዊ አገዛዝና ደርግ

* በ"ሦሥተኛው ዓለም" ውስጥ የፋሺዝም ዋና ተሸካሚ ቢሮ ከበርቴው ነው ብለናል:: ይህ አገሪቷ ውስጥ ካለው የፖለቲካ፣ ኢኮኖሚና የሶሺል ሁኔታ ጋር ሊጣጣም የሚችል፣ ፋይናንስ ካፒታልን የሚያገለግል ሥርዓት ይመሠርታል:: ነፃ ብሔራዊ ኢኮኖሚ አይገነባም:: ከኢምፔሪያሊዝም ቁጥጥር ውጭ የማይንቀሳቀስ ጥገኛ ኢኮኖሚ ይኖረዋል::

* ደርጉ አሁን ባለበት ሁኔታ፣ በተለይም ከቢሮው ከበርቴው ጋር ባለው ቅራኔ ከዚያም ከኢምፔሪያሊዝም ጋር ባለው ቅራኔ ፋሺስታዊ ሊያሰኘው ፍጹም አይቻልም:: በውስጡ ይህ አዝማሚያ ያላቸው ሃይሎች ሊኖሩ ይቻላሉ:: የ"ቀኙ ክንፍ" ለዚህ የሚበቃ ሃይል /ፖቴንሺያል/ ሊሆን ይቻላል::

* ይህን ለመረዳት ካለው ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት፣ ደርግ የወሰዳቸውን እርምጃዎች በሙሉ መመርመር ነው:: የመሬት አዋጁ መሃከላዊ ትርጉም ይኖረዋል:: ይህን የመሬት አዋጅ አስቀድመው ተቃውመው የነበረት የደርግ ሃይሎች በመሠረቱ በቢሮ ከበርቴው ጋር አንድነት ለመመስረት ፖለቲካዊ ፖቴንሺያል አለ::

* አንዳንድ ጥያቄዎች:: ደርግ ዲሞክራቲክ መብቶች ስለከለከለ ፋሺስታዊ ያሰኘዋል ወይ? ደርግ በሕዝብ ሃይሎች ላይ አለፍ አለፍ ቴሮሪስቲክ እርምጃዎች ስለ ወሰደ ፋሺስታዊ ሥርዓት መሠረት ያሰኘዋል ወይ? እርምጃዎቹ በተለይ ደግሞ በሁለት አቀጣጫ ሲሆኑ ማለት በለየላቸው የቢሮ ከበርቴና የፊውዳል መደብ ወኪዮች ላይ ሲወሰዱ ምን ትርጉም አለው? ደርግ ሾቪኒስት ፖሊሲ ስለአለው /ያውም ይህ አሁን በመቀየር ላይ ነው/ ፋሺስታዊ አገዛዝ መሠረት ያሰኘዋል ወይ?

* መልሱ:— ስለ ፋሺስታዊ እርምጃዎች፣ ስለ ፋሺስታዊ ድንጋጌዎች ልንናገር እንችላለን፣ ነገር ግን ፋሺስታዊ አገዛዝ ተመሠረተ ከማለት እጅግ የተለየ ነው:: ፋሺስታዊ ሥርዓት ተመሠረተ የሚባለው እርምጃዎች ተደርድረው፣ አንዳንድ ፖሊሲዎች ስለተመረመሩ ብቻ አይደለም:: ዋናው ባሉት አድሃሪ መደቦች —በሦሥተኛው ዓለም ውስጥ— ከቢሮ ከበርቴው ከጥገኛውና የፊውዳል መደቦች ጋር ያለውን ግንኙነት መመርመር:: የህብረሰቡ፣ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና ሶሺያል መሠረትን በመመርመር ነው:: የነሂትለር አይነቱ ፋሺስታዊ ሥርዓት መመሥረት መቀባጠር ደግሞ ከሁሉም የበለጠ የሶሻል ሳይንስ ሀ ሁን አለማወቅ ነው:: ጥያቄ ውስጥ አይገባም::

IV- የፋሺዝም አደጋ በሩቁ ወይንም በቅርቡ በሚፈጠር ሁኔታ አኳያ ሲታይ

* በሩቁ የሚፈጠርን ሁኔታም /የጀርመን ፋሺስት እንቅስቃሴ አፈጣጠር ለምሳሌ መመልከት ነው / ሆነ በቅርቡ ሊፈጠር የሚችል ሁኔታ በአሁኑ ኢትዮ

ጽያ ዋናው–የብሄራዊ ዲሞክራቲክ አብዮቱን ሙሉ በሙሉ በቆራጥነት ፍጻሜ ማድረስ ነው፡፡መሃከላዊ ቦታ የሚሰጠው የመሬት አዋጅ — የገጠሩ ማድረግና የጥገኙ አውጃርችን ከነኢኮኖሚ መሠረታቸው መደምሰስ ነው፡፡ የበሰበሰውን ቢሮክራሲ በህዝባዊ አስተዳደር መተካት ፣ የጦር ሃይሉን በአዲስ ህዝባዊ የጦር ሃይል መተካት፣ የፀጥታ ድርጅቶችን መደምሰስና በአዲስ ህዝባዊ ቁጥጥር መተካት ወዘተ፡፡ይህም በወዝ አደሩ አመራር የገጠሩን አብዮት ፣ ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮትን በቆራጥነት ማድረግ ማለት ነው፡፡

* የፋሽስታዊ አገዛዝ አደጋ —በሩቅ አቢያ ሲታይ ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ከላይ ባለነው መንገድ ፍጻሜ ሳያገኝ ቀርቶ፣ የፊውዳል ርዝራዦች አዲስ ከተፈጠረው ሁኔታ ጋር እራሳቸውን አጣጥመው ሊሰናበቱ የቻሉና ሃይላቸውን ቀስ በቀስ የገነቡ እንደሆነ፣በቅርብ አቢያ ሲታይ፣ ደርግ ከቢሮው ከበርቴ ጋር አንድነት የፈጠረ እንደሆነና የዲሞክራቲክ አብዮትን መራመድን የገታ እንደሆነ፣የተወሰነ የደርግ ክፍል /የ"ቀኝ ክንፍ" ለምሳሌ/ ከመላሽ ሃይሎች ጋር ገጥሞ ከኢምፔሪያሊስቶች ጋር ተስማምቶ መንግሥት ገለበጣ /ኩ ዴታ/ ያደረገ እንደሆነ /የሃምሌው የገለበጣ ሙከራዎች ምሳሌና ቸው/፣ወይንም የተወሰነ የደርግ ሃይል ከጥንቶቹ በዝባዥ መደቦች ጋር "ዴቀር" ተብለው "ኢዲህ" እንደጠየቁው "የብሔራዊ እርቅ መንግሥት" ያቋቋሙ እንደሆነ ለፋሺስታዊ ሥርዓት ምቹ ሁኔታ ወይንም ፋሺስታዊ ሥርገት ይመሠረታል፡፡ይህ ሁሉ ሳይሆን ደርግ ያመጣውን መለስተኛ ፕሮግራም በምንም አይነት ያላሰናከለ እንደሆን ግን ምቹው አብዮታዊ ሁኔታ ይቀጥላል፡፡ ተራማጆች ይጠቀሙበታል፡፡ደርግ ከእንቅፋትነት ወደ አጋዥነት ይቀየራል፡፡

* ይህ ሁሉ የሚወሰነው በሚመጣውና አሁን በሚካሄደው የጠነከረ የመደብ ትግል ነው፡፡ የወዝ አደሩ መደብ በራሱ ፓርቲ አማካይነት፣የነቃ የተደራጀና የታጠቀ ትግሉን በማካሄዱ፣ከገበሬው ጋር የጠበቀ የትግል አንድነት መመስረትና መምራት፣ተራማጁ ንዑስ ከበርቴውንና የተጨቆኑ የህብረሰብ ክፍሎችን ሁሉ የሚጠቀልል የአንድነት ግንባር ማደራጀትና ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮትን ማካሄድ የግዜው አብይ ጥያቄ ነው፡፡

ለወዝ አደሩ ፓርቲ መደራጀትና ታሪካዊ ግዴታውን መፈጸም የመላኢትዮጵያ ሶሺያሊስት ንቅናቄ መቋቋም አንድ ከፍተኛ እርምጃ ነው፡፡ የገበሬው እንቅስቃሴ በሺህ በሚቆጠሩ የገበሬ ማህበራት መደራጀቱ አንድ ከፍተኛ እርምጃ ነው፡፡ዐውነተኛ ተራማጆች በአሁኑ ወቅት አንድነታቸውን በማጠንከር የወዝ አደሩንና የገበሬውን የትግል ህብረት መሥርተው የተጀመረው ዲሞክራሲያዊ እንቅስቃሴን በአደሱ ዴሞክራሲያዊ አብዮት አቅጣጫ እንዲራመድ ማድረግ ይገዘው ታላቅ ተግባራቸው ነው፡፡ ለዚህም ንቃታዊ፣ድርጅታዊና ትጥቃዊ ድርጅትን ማፋፋም፣ የሰፊው ህዝብን ሃይል ከአሁኑ ማቀነባበርና የህዝባዊ ሃይል መሠረት በየቦታው መጣል ለማገናውም ለሚመጣ ሁኔታ ማረጋገጣ ነው፡፡ዐውነተኛ ተራማጆች ለማገናወም የፀረ አብዮት አደጋ አንድነታቸውን በማጠንከር ለነቃ ለተደራጀና ለታጠቀ አብዮታዊ ህዝባዊ አመጽ መዘጋጀት እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር
መጽሔት አዘጋጅ ቦርድ
The Ethiopian Students' Union in Europe
Editorial Board

## ማሳሰቢያ

ውድ አንባቢያቻችን፣

የውጭን ንቅናቄ ከውስጥ ሆኖ ቦርቡሮ ለማዳከም ያደረገው ሙከራ ስላልተሳካለት እርሱን ከንቅናቄያችን ያገለለው ፀረ ሕዝብ ቡድን ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ፣ከአስር ዓመት በላይ ሰፊው ሕዝብ ጎን በመሰለፍ ያለማቋረጥና ያለመታከት ፀረ ኢምፔሪያሊስትና ፀረ ፊውዳሊስት ትግል ሲያካሂድ በኖረው ማህበራችንና በነዚህም አስር ዓመታት ያልተሰጣቸውን ነፃነት በመንጠቅ የሰፊውን ሕዝብ ድምፅና ትግል ሲያስተጋቡ በኖሩት ፣ከየትኛውም የተማሪ ማህበራት መጽሔት በላይ የሰፊው ሕዝብ ማስተማሪያና መቀስቀሻ ሆነው በቆዩት በታጠቅና በትግላችን ስም መጠቀም ጀምረዋል:: የዚህ ፀረ ሕዝብ ቡድን ዓላማ ማህበራችን እንዲሁም ታጠቅና ትግላችን በአስር ዓመት ቆራጥ ትግል ባተረፉት ስም ተጠቅሞ ፀረ ሕዝብ ፖለቲካውን ለመሸፈን ነው::እንዲሁም ከውጭ ሆኖ ያቃተውን የኢትዮጵያ ተማሪያችና ተራማጆች አንድነት የማፍረስ ሙከራ ከውስጥ ሆኖ ውዥንብር በመንዛት ለማፋፋም ነው::ይህም እንደማይሳካ የተረጋገጠ ነው:: ለማንኛውም፣የተለመደው የመጽሔት አዘጋጅ ቦርድ አድራሻ/ማለትም P.O.BOX 3198 10364 STOCKHOLM - SWEDEN ያለ ያዙ፣ የዓለም ዓቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪያች ማህበር አባልነትን የማይመለከቱ ግን የማህበራችን መጽሄቶች ስም የያዙ መጽሄቶች ወዘተ በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪያች ማህበር መጽሄቶች አለመሆናቸውን እንድታውቁልንና እንድታስታውቁልን እንጠይቃለን::ለእነዚህ አይነት መጽሄቶች ተመያዥ ''ዓለም ዓቀፍ ፌዴሬሽን'' በሚባል ስም የታወቀው የነ እሰፋወሰን — መንገሻ ሥዎ የወጣቶች ድርጅት ነው::

ከፋፋዮችና አወናባጆች ከፊውዳሊዝምና ከኢምፔሪያሊዝም ጋር ይውደሙ!
የእውነተኛ አብዮታዊያንና ተራማጆች አንድነት ይኑር!
ድሉ የሰፊው ሕዝብ ነው!

በአኢተማ የመጽሄት አዘጋጅ ቦርድ